# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ
## የመምህር መምሪያ
## መጽሐፍ



## ፯ኛ ክፍል

# የአማርኛ

## እንደ መጀመሪያ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ መጽሐፍ

## ፮ (6)ኛ ክፍል


አዘጋጆች

ዐፀደማርያም ሲሻው ወግደረሰኝ

ዳንኤል ገላነው ምህረት

ጉድብ ንጉሴ ካሳ

ገምጋሚና አርታኢዎች

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድኅን

ትንቢት ግርማ ኃይሉ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

የጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ

ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

አቀማመጥ እና ሥዕል

እንጦጦ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ(TMS)

© መብቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተጠበቀ ነው።
2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል።

ለሥራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል።

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን።

# ማውጫ


ገጽ

መግቢያ.....VI

ምዕራፍ አንድ

ባህላዊ አለባበስ.....1

ምዕራፍ ሁለት

ታዋቂ አትሌቶች.....11

ምዕራፍ ሶስት

ቃላዊ ግጥም.....22

ምዕራፍ አራት

ዘመናዊ ግብርና.....31

ምዕራፍ አምስት

ቱሪዝም.....45

ምዕራፍ ስድስት

ጸረ- አደንዛዥ ዕጾች.....56

ምዕራፍ ሰባት

የጥላቻ ንግግር.....65

ምዕራፍ ስምንት

ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ.....77

ምዕራፍ ዘጠኝ

ባህላዊ ልማዶች.....90

ምዕራፍ አስር

ሴቶችን ማብቃት.....106

ዋቢ መጽሐፍት

አባሪዎች

# መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያና ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄደው የ6ኛ ክፍል የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ አማርኛን በመጀመሪያ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ፤ በተጨማሪም በቃላትና በሰዋሰው እውቀት እንዲያገኙ ለማድረግ የተዘጋጀ የሥርዓተ ትምህርት አካል ነው።

የመምህር መምሪያው በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ በመመሥረት በአዳዲሶቹ የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎች ውስጥ በጥቅም ላይ ስለዋሉት የማስተማር አቀራረቦችና ስለአዲሱ መርሃትምህርት (ሥርዓተትምህርት) መነሻ ሀሳቦች መሠረታዊ መረጃ ይሰጣል። በአንድ ምዕራፍ ሥርም ለቀረቡት የትምህርት ይዘቶች ግልጽ መመሪያ ያቀርባል። በተጨማሪም ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ለመከታተልና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ተገቢውን ድጋፍና ማጠናከሪያ ለመስጠት ተከታታይ ምዘናን መተግበር የሚቻልበትን መርህን ይዟል። በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሥርዓተ ፆታንና የአካቶ ትምህርትን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚገባ ድጋፍ ይሰጣል።

በመጨረሻ ለ6ኛ ክፍል የተዘጋጀው አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ) መርሃ ትምህርት በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተያይዟል። ይህ መርሃ ትምህርትም በየደረጃው በእያንዳንዱ ወሰነ ትምህርት ተማሪዎች ሊያዳብሯቸው ስለሚገቡ የቋንቋ ብቃቶችንም ያሳያል።

# የማስተማር መርሆዎች

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) እንዲሁም በቃላትና በሰዋስው የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች የማንበብንና የመጻፍን ችሎታዎች ይበልጥ በሚያዳብሩበት መልክ ተደራጅተዋል፡፡

አዳምጦ (አንብቦ) መረዳት የሚዳብረው በቅድመ ማዳመጥ(ማንበብ፣ በማዳመጥ) በማንበብ ሂደትና በድኅረ ማዳመጥ(ማንበብ) ተግባራት ነው፡፡ ተማሪዎች ስለጽሑፉ (በቅድመ ማዳመጥ(ማንበብና በማዳመጥ) በማንበብ ሂደት ወቅት) እንዴት መገመት እንደሚችሉ፣ መረዳታቸውን በራሳቸው እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉና ያዳመጡትን ወይም ያነበቡትን እንዴት መገምገም እንደሚችሉ መማር አለባቸው፡፡

መናገርና መጻፍ በተገቢ ሁኔታ ራስን መግለጽን ይመለከታል፡፡ ይኸውም ቋንቋውን በትክክል መጠቀምንና ሀሳብን ለሌላ አካል በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በግልጽ ማስተላለፍን ይጨምራል፡፡ በመሆኑም የንግግርና የጽሑፍ ክሂል የሚዳብረው ተማሪዎች በተቻለ መጠን ራሳቸውን እንዲገልጹ በርካታ ዕድሎች ሲመቻቹላቸውና ወቅታዊ ግብረመልሶችም ሲያገኙ ነው፡፡

የቃላት ዕውቀት፣ ቃላትን የመለየት የመረዳትና ፍቻቸውን የመገንዘብ ችሎታ ነው፡፡ የተገደበ የቃላት ዕውቀት ያላቸው ተማሪዎች የሚያነቡትንም ሆነ የሚያዳምጡትን ጽሑፍ መልእክት ይበልጥ ለመረዳት በጣም ሲቸገሩ ያስተውላል ፡፡ ስለዚህ የቃላት እውቀት በስፋት እንዲኖራቸው ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የቃላት እውቀት የሚዳብረው አዳዲስ ቃላትን ከነፍቻቸው በማስተማር፣ ተማሪዎች እነዚህን ቃላት በንግግርም ሆነ በጽሑፍ እንዲጠቀሙባቸው በማበረታታትና ከሚያነቡት ወይም ከሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ የቃላትን ፍቺ የሚያገኙበትን ብልሃት (ስልት) በማስተማር ነው፡፡

ሰዋስው፡- በመርሃ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ ለደረጃው በተዘጋጀው የትምህርት ወሰንና ተለጣጥቆነት መሠረት የተለያዩ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በመማርና በትክክል በመጠቀም ላይ ያተኩራል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የዘረዘርናቸው የትምህርት ይዘቶች ማዕከል ያደረጉት በየምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ዓላማዎች ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ ( ፩ )

## ባህላዊ አለባበስ

ክፍለ ጊዜ (18)

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ✓ ትክክለኛውን አገላለፅ ተጠቅመው በተገቢው ፍጥነት ያነባሉ፡፡
- ✓ የቃላትን አገባባዊ ሥርዓት ተከትለው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- ✓ ከምንባቡ ውስጥ ለወጡ ውስብስብ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ✓ ቃላትን እያጣመሩ ያነባሉ፡፡
- ✓ በጽሑፍ ውስጥ ያሉ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው መንገድ ይጠቀማሉ፡፡

የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች፡-

- ➢ አድምጦ ሀሳብ መግለፅ
- ➢ አቀላጥፎ ማንበብ
- ➢ አዳዲስ ቃላት
- ➢ አንቀጽ መፃፍ
- ➢ የተፀውዖና የወልስም

# ክፍል አንድ

## ማዳመጥ:- የሀገር ባህል ቀሚስ

## የትምርቱ አቀራረብ

- መምህር ወደተግባር ከመግባትዎ በፊት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ ወደፊት እንዲቀመጡ በማድረግ የአካል እንቅስቃሴዎን በመከታተል እንዲሳተፉ ያድርጉ፡፡
- ለማዳመጥ የቀረበውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተዘረዘሩትን የምዕራፍ ዓላማዎች እንዲረዱ ያብራሩላቸው፡፡
- ወደቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በመሻገር ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ስዕል ተመልክተው እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- በውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ እንዲገልፁ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠልም በጥሞና እያዳመጡ ጭብጡን ለማወቅ ማስታወሻ እንዲጽፉ በመግለጽ ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ ያንብቡላቸው፡፡

ኢትዮጰያውያን ከአካባቢያቸው፣ ከአጥቢያቸው ከለመዱት ትውፊታቸው አንጻር አለባበስ አንዱ አንዱ መገለጫቸው ነው፡፡ ከነዚህ አለባበስ መካከልም ሀገረኛው ቀሚሳቸው ነው፡፡ ከሀምሳ አመታት በፊት ታትሞ በወጣው የአለቃ ደስታ ተክለወልድ ‹‹ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት›› ባህላዊ ቀሚስን በየፈርጅ በየፈርጁ ይበይነዋል፡፡ በሐር የተጠለፈና የተዘመዘመውን ጥልፍ ቀሚስ ሲለው፤ ጥበብ ያለበትን ደግሞ ጥበብ ቀሚስ ይለዋል፡፡ ባህላዊ አለባበስ አንድን ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ በቀላሉ የትአካባቢ እንደሆነ ለማወቅ ያስችላል፡፡ ለአብነት ያህልም በጎጃም ማህበረስብ የልጃገረዶችና የሴቶች አለባበስን ከአጊያጌጥ ጋር እንደሚከተለው ገልፆታል፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት የጎጃም ልጃገረዶች ባህላዊ አለባበስ በተለይም በዓል ሲሆን ለብሰውት የሚወጡት ልብስ ሙሉ በሙሉ የሀበሻ ቀሚስ ነበር፡፡ የሀበሻ ቀሚስ ጉንፍ፣ ሽብሽቦና ጥልፍ ቀሚስ እንዲሁም ፍቅር ቁርጥ የተባለ ነበር፡፡

አሁን ላይ ግን በተለያዩ አጋጣሚዎች ይህንን አለባበስ ሳይሸራረፍ ሙሉውን ለብሳ የምትወጣ ልጃገረድ ማግኘት ባይቻልም በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ልጃገረዶች ባህላዊ አለባበሳቸውን ያዘወትራሉ፡፡ በእለት ከእለት እንቅስቃሲያቸው የሀበሻ ቀሚሱ ቀስበቀስ ዘመን አመጣሽ በሆኑ ከብትን ጨርቆች በሚዘጋጁ ልብሶች ቢተካም በበዓላት፣ በቤተ እምነት ሲገኙና በሌሎች ማህበራዊ አጋጣሚዎች (በሰርግ፣ ዘመድ ጥየቃ፣ ዘመን

መለወጫና ህዝባዊ ስብሰባዎች…) ላይ አሁንም ድረስ ባህላዊ የሀበሻ ቀሚስ መልበስ የተለመደ ነው፡፡ ባህላዊ ቀሚሶች በአይነታቸውና በቅርፃቸው የተለያዩ ናቸው፡፡

1. ተማሪዎች እስካሁን ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ ?
2. ምንባቡ ምን ምን የቀሚስ አይነቶችን የሚጠቅስ ይመስላችኋል?

ለአብነት ያህልም

## ሀ. ሽብሽቦ ቀሚስ

ሽብሽቦ ቀሚስ የተለያዩ ቀለማት ካላቸው ጥለቶች ከክር፣ ከማግና ከዝሃ የሚዘጋጁ ባላገቡ ወጣት ሴቶችና በእናቶች ሊለበስ የሚችል የልብስ አይነት ነው፡፡ ሽብሽቦ የተባለበት ምክንያት እንደጉንፍ ቀሚስ ልቅ ባለመሆኑና ወገቡ ላይ ገመድ በማስገባት የሚሰፋ ስለሆነ እና ቀሚሱ ከወገቡ ጀምሮ እስከታች እስከጥለቱ ድረስ የሚሸበሸብ በመሆኑ ነው፡፡

## ለ. ጉርድ ቀሚስ

ጉርድ ቀሚስ ከጊዜ በኋላ ነባሩን የማህበረሰቡን ባህል በማሻሻል የተገኘ እንደሆነ ይገመታል፡፡ የተለያዩ ቀለም ካላቸው ጥለቶች ከማግና ከዝሃ የሚዘጋጅ ሲሆን ጉርድ የተባለበትም ምክንያት እስከወገቡ ድረስ ባዶ ሆኖ ከወገቡ በታች ልቅ ስለሆነ ነው፡፡ ቀሚሱ ከወገቡ ጀምሮ እስከ ጥለቱ ድረስ የሚሸበሸብ መሆኑ ከሽብሽቦ ቀሚስ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ያላገቡ ልጃ ገረዶች ፣ እናቶች እና ህፃናት ይለብሱታል፡፡

## ሐ. ጉንፍ ቀሚስ

የጎጃም ማህበረሰብን ከሚወክሉና ባህሉን ከሚያንፀባርቁ ሀገረሰባዊ አለባበሶች መካከል አንዱ ጉንፍ በመባል የሚታወቀው የቀሚስ አይነት ነው፡፡ ጉንፍ ከጥጥ የሚዘጋጅና በአካባቢው ሽማ ሰሪዎች የሚሰራ የሴቶች ባህላዊ ልብስ ሲሆን በአብዛኛው በተለያዩ በዓላትና ክብረ በዓላት ላይ ይለበሳል፡፡

ምንጭ (ከሪፖርተር ጋዜጣ ሚያዚያ 11/2009ዓ/ም ለስድስተኛ ክፍል እንዲሆን ተሻሽሎ የቀረበ)፡፡

የቅድመ ማዳመጥ፣ የማዳመጥና የድህረ ማዳመጥ ሂደቶችን በተግባር ላይ በማዋል ተማሪዎቹ የአዳምጦ መናገር ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያግዟቸው።

- ❖ በተግባር አንድ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ።
- ❖ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ እየሰጡ እንዲጽፉ ይግለጹላቸው።
- ❖ በመጨረሻም ስለአንድ ባህላዊ ልብስ ከሰዎች ጠይቀው በክፍለ ውስጥ ንግግር እንዲያደርጉ ይግለጹላቸው።
- ❖ ጠይቀው የመጡትን በንግግር እንዲያቀርቡ ጊዜውን ያመቻቹላቸው።
- ❖ ባቀረቡት ሀሳብ እንዲወያዩና አስተያየት እንዲሰጣጡ ያበረታቷቸው።
- ❖ ተማሪዎቹ ያዳመጡትን የምንባብ መልዕክት በትክክል መረዳት መቻላቸውን በድህረ ማዳመጥ ተግባራት ስር ላሉት ጥያቄዎች በሰጡት መልስ ያረጋግጡ።
- ❖ በሌላ ጊዜ ሬዲዮና ቴሌቪዥን እያዳመጡ ያዳመጡትን ለጓደኞቻቸው በመተረክ የማዳመጥ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያስረዷቸው።

## ክፍል ሁለት ንባብ

- ❖ የማንበብ ተግባር ከመጀመሩ በፊት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን በርዕሱና በምስሉ መካከል ያለውን ዝምድና፣ርዕሱን አይተው ምንባቡ ስለምን ሊገልጽ እንደሚችል እንዲገምቱ ጊዜ ይስጧቸው።
- ❖ ግምታቸውን ይቀበሏቸውና ወደቀጣዩ ቃላትን በመነጠልና በማጣመር ንባብ ያምሩ።
- ❖ ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ውስብስብ ቃላትን በመነጠልና በማጣመር እንዲያነቡ ይግለጹላቸው።
- ❖ ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ያሉ በመሆናቸው በአንብቦ መረዳት ላይ እንቅፋት እንዳይሆንባቸው በትክክል እንዲያነቡ ያድርጉ።
- ❖ በመቀጠልም ተማሪዎቹ በለሆሳስ እንዲያነቡና በንባብ ሂደት የሚያጋጥማቸውን ግልጽ ያልሆነ ሀሳብ በማስታወሻ እንዲጽፉ ያስረዷቸው።
- ❖ የንባብ ሂደቱን ገታ በማድረግ የንባብ ጊዜ ጥያቄን እንዲመልሱ ያድርጓቸው።
- ❖ የማንበብ ሂደቱን ሲያጠናቅቁ ሲያነቡ ያጋጠማቸው ግልጽ ያልሆነ ሀሳብ ካለ እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው።

- ላቀረቡት ጥያቄ በራሳቸው መልስ መስጠት እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡ በተማሪዎቹ ያልተመለሰ ጥያቄ ካለ ትክክለኛውን መልስ እርስዎ ይስጧቸው፡፡
- በተግባር ሶስት የቀረቡትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት በጽሁፍ እንዲመልሱና ለሚሰጡት መልስ ምክንያት እንዲያቀርቡ ይግለጹላቸው፡፡
- የሰጡትን መልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መመለሳቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በተጨማሪም ከምንባቡ ለወጡ አዳዲስ ቃላት ፍቺ በጽሁፍ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- የቀረቡትን ጥያቄዎች በትክክል መመለስ መቻላቸውን ለማረጋገጥ የሰሩትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በትክክል ያልሰሩት ጥያቄ ካለ ትክክለኛውን መልስ ይግለፁላቸውና እንደገና አስተካክለው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- መምህር የአንብቦ መረዳት ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ ለአቀላጥፎ ንባብ ባህላዊ አለባበስ ከሚለው ምንባብ ውስጥ ተቀንጭቦ የተወሰደ ምንባብ ቀርቧል፡፡
- በጥንድ ሆነው ደቂቃ እየያዙ በተገቢው ፍጥነት እንዲያነቡ ያዘጋጇቸው፡፡
- እያንዳንዱ ተማሪ ንባቡን ያጠናቀቀበትን ደቂቃ እንዲመዘግቡላቸው ንባቡን ሲጨርሱ እንዲያሳውቅዎት ያስረዷቸው፡፡
- ምን ያህሉ ተማሪ በተሰጠው ደቂቃ አጠናቆ እንዳነበበና ምን ያህሉ ደግሞ ማንበብ እንዳልቻለ ይለዩ፡፡
- ማንበብ ያልቻሉትን ተማሪዎች በድጋሜ ለብቻ ደቂቃ ይዘው ያስነብቧቸው፡፡
- በዚህም ያሳዩትን መሻሻል ይመዝግቡና መሻሻል ያላሳዩ ተማሪዎችን ለይተው ይመዝግቡ፡፡ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ተጨማሪ ተግባር በመስጠት ንባብን ያለማምዷቸው፡፡
- በመጨረሻም ተማሪዎቹ የንባብ ክሂላቸውን ለማሳደግ ይረዳቸው ዘንድ የተለያዩ ጽሁፎችን እንዲያነቡ በመግለጽ ትምህርቱን ያጠናቁ፡፡

# ክፍል ሶስት   ቃላት

መነጠልና ማጣመር

- ❖ የቃላት አውዳዊ ፍቺ ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖረውን ፍቺ የሚመለከት መሆኑን በማስረዳት እንዴት መረዳት እንደሚችሉ ከቀጥተኛ ፍቺ እንደሚለይ በምሳሌ በማስደገፍ አጭር ገለፃ ይስጧቸው፡፡
- ❖ ለምሳሌ አሻራ የሚለውን ቃል ወስደን በቀጥተኛ ፍቺ ብንመለከት ምልክት የሚል ፍቺ ይሰጠናል፡፡
- ❖ ይህንኑ ቃል በአውዳዊ ፍቺ ብንመከተው ኢትዮጵያውያን በአባይ ግድብ ላይ አሻራቸውን አስቀምጠዋል፡፡ ብንል አውዳዊ ፍቺው የድርሻውን አበርክቷል የሚል ይሆናል፡፡
- ❖ በተሰጠው ገለፃ መሰረት በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩባቸው ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በማዛመድ የቀረበውን የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ጨምረው ያሰሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ በማድረግ ለቃላቱ ትክክለኛ መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ❖ የፈጸሙት ስህተት ካለ  እርማት በመስጠት እንዲያስተካክሉ ያበረታቷቸው፡፡

ለናሙና የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

ከዚህ በታች በ‹‹ሀ ›› ስር ለቀረቡት ቃላት እና ሐረጋት በ ‹‹ለ ›› ስር ከተዘረዘሩት በፍች ተመሳሳይ የሆኑትን እየመረጣችሁ አዛምዱ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ረ | 4. ለ |
| 2. ሰ | 5. ሠ |
| 3. መ | 6. ሀ |

ተግባር ሶስት

ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት በፍቺ ልዩ የሆነውን አውጡ፡፡

1. ሀ
2. መ
3. ሐ
4. ለ
5. መ

## ክፍል አራት ጽሕፈት

አንቀጽ

ማስታወሻ፡-

የቢጋር (የአስተዋፅኦ) ምንነትና አዘገጀት

ቢጋር (አስተዋፅኦ) አንድን አንቀጽ ለማዘጋጀት፣

ከተዘጋጀም በኋላ በተፈለገው መንገድ ሀሳቡ በትክክል መስፈሩን የሚያሳይ ንድፍ ነው፡፡ ቢጋር አብዛኛውን ጊዜ አንቀጽ ከመፃፋችን በፊት የሚዘጋጅ ሲሆን ጽሁፉ ከዋናው ሀሳብ ሳያፈነግጥ፣ በቅደም ተከተል እንዲቀመጥ ያግዛል፡፡

ቢጋር ለጀማሪም ሆነ ልምድ ላላቸው ጸሐፊዎች ወሳኝ ነው፡፡ ቢጋር(አስተዋፅኦ) ለማንኛውም ጸሐፊ የጽሑፉን መነሻና መድረሻ በመጠቆም ትልቅ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ እንዲህ አይነቱ ድጋፍ በጽሑፍ ውስጥ የሀሳብ ቅደም ተከተል መፋለስ እንዳይኖር በእጅጉ ያግዛል፡፡ ቢጋር በዝርዝር (ፍሬሀሳቡን) በአጭሩ በሚጠቁም መልኩ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የአንቀጹን መነሻና መድረሻ ቅደም ተከተል ይዞ እንዲቀርብ በዝርዝር ቢቀርብ የተሻለ ይሆናል፡፡ በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ከርእሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሃሳቦች በወረቀት በአጭር በአጭሩ ማስፈር ስራውን የበለጠ ያቀለዋል፡፡ ቢጋርን በሁለት አይነት መንገድ ልናዋቅር እንችላለን፡፡ እነሱም በርዕስ መልክና በአረፍተ ነገር መልክ ሊሆን ይችላል፡፡

ሀ. ቢጋር በርዕስ መልክ ሲዋቀር

ለምሳሌ፡- አንቀጽ ለመፃፍ ያሰብነው የአየር ብክለትና መንስኤዎቹ በሚል ርዕስ ቢሆን ርዕሱን አስመልክቶ ከዚህ የሚከተሉትን መሰል ሀሳቦች በወረቀት ላይ ማስፈር ይቻላል፡

## የአየር ብክለትና መንስኤዎቹ

1. የኢንዱስትሪዎች ጭስ

1.1. የቀላል ኢንዱስትሪዎች ጭስ

1.2. የከባድ ኢንዱስትሪዎች ጭስ

2. ጦርነት

2.1. የከባድ ፈንጂዎች ጭስ

2.2. የኑክሌር ፍንዳታ

2.3. የቀላል መሳሪያዎች ጭስ

3. የተሽከርካሪዎች፣የአውሮፕላኖችና የሮኬቶች ጭስ

3.1. የቀላልና የከባድ አውሮፕላኖች ጭስ

3.2. የቀላልና የከባድ ተሽከርካሪዎች ጭስ

3.3. የሮኬቶች ጭስ

4. የተፈጥሮ አደጋዎች የሚፈጥሩት ከፍተኛ ጭስ

4.1. የእሳት ገሞራ ፍንዳታ

4.2. ከፍተኛ የደን ቃጠሎ

ለ. ቢጋር በዓረፍተ ነገር መልክ ሲዋቀር

ምሳሌ፡- ክረምት ሲጠባ

1. አካባቢው በሙሉ ይጨልማል፡፡

1.1. ፀሀይ በደመና ትጋረዳለች፡፡

1.2. ጨረቃና ከዋክብት ይጋረዳሉ፡፡

1.3. ጋራ ሸንተረሩ በጉም ይሸፈናል፡፡

1.4. ሰማዩ ይጠቁራል፤ በደመና ይሸፈናል፡፡

2. ሰዎች በስራ ይጠመዳሉ

2.1. ገበሬው በእርሻ ስራ ይጠመዳል፡፡

2.2. የገበሬ ሚስቶች በጉልጓሎ ስራ ይጠመዳሉ፡፡

2.3. ሰዎች ከመዝናናት ይታቀባሉ፡፡

3. የእርሻ ስራ  ግብዓቶች በጣም ተፈላጊ ይሆናሉ፡፡

3.1. የዘር እህል ፍላጎትና ዋጋ ይጨምራል፡፡

3.2. የማዳበሪያ ፍላጎት ይጨምራል፡፡

3.3. የእርሻ ስራ መሳሪያዎች ዋጋ ይጨምራል፡፡

4. መዝናናት መደሰትና መፈንጠዝ ቀዝቀዝ ይላል፡፡

4.1. ሰርግና ድግስ ጎልቶ አይታይም፡፡

4.2. ደምቆ የሚከበር በዓል አይኖርም፡፡

4.3. ጭፈራ ሆታና እልልታ እምብዛም አይታይም፡፡

- በጽህፈት ተግባር ላይ የቀረበውን የአንቀጽ አጻጻፍ ክሂል ከማሰራትዎ በፊት በአምስተኛ ክፍል ስለአንቀጽ ምንነትና የአንቀጽ አጻጻፍ ስልቶች በተመለከተ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠል በመምህሩ መምሪያ የቀረበውን የቢጋር አፃፃፍ ምንነትና የቢጋር ንድፍ ማስታወሻ እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- ከዚያም አንቀጽ ለመጻፍ በተሰጣቸው ርዕስ ቢጋር እንዲያዘጋጁ ምሳሌውን በአግባቡ ያስረዷቸው፡፡
- በምሳሌው የቀረበውን ጅምር ቢጋር አጠናቀው እንዲጽፉ ይደግፏቸው፡፡
- በመጨረሻም አንቀጽ ለመፃፍ የሚያስችል ቢጋር ማዘጋጀታቸውን ያረጋግጡላቸው፡፡
- ከዚያም አንቀጽ ጽፈው እንዲመጡ ይግለፁላቸው፡፡ በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ የጻፉትን አንቀጽ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲቀያየሩ በማድረግ የጽሑፉን ስህተት እንዲለዩ ያግዟቸው፡፡

- ❖ ለይተው ያወጡትን ችግር እንዲያቀርቡ በማድረግ በራሳቸው ለማስተካከል እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም የተስተካከለውን አንቀጽ በመውሰድ በአርያነት እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ

ተስተካክሎ የተዘጋጀ ቢጋር በቻርት

## ክፍል አምስት ሰዋስው

የተጸውዖና የወል ስም

- ❖ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን የተጸውዖና የወል ስሞችን ማስተዋሻ በደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ በጥያቄና መልስ በምሳሌ በማስደገፍ አጭር ገለፃ ያቅርቡላቸው፡፡
- ❖ ከዚያም በመማሪያ መጽሐፉ ተደበላልቀው የቀረቡትን ስሞች የተጻውዖና የወል ስም በማለት በሰንጠረዡ ውስጥ እንዲመድቡ ያድርጉ፡፡
- ❖ የሰሩትን እንዲናገሩ በማድረግ ስህተት ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት ትክክለኛውን መልስ እንዲይዙ ያድርጉ፡፡
- ❖ ተማሪዎቹ የተጸውዖ እና የወል ስሞችን በትክክል መለየታቸውን ከሰጡት መልስ በመነሳት እርግጠኛ ይሁኑ፡፡
- ❖ መደገፍ የሚያስፈልጋቸው፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸውንና የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ካሉ በመለየት ተጨማሪ ተግባር በመስጠት እንዲለማመዱ ያግዟቸው፡፡
- ❖ ትምህርቱን ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ ተጨማሪ ተግባር ይስጧቸው፡፡

መርጃ  መሳሪያ

የተዘጋጀ የተፀውዖና የወል ስም የያዘ ሰንጠረዥ በቻርት

# ምዕራፍ ሁለት(፪)

## ታዋቂ አትሌቶች

ክፍለ ጊዜ 18

አጠቃላይ የምዕራፉ ዓላማዎች:-

- ✓ ከቃላት ውስጥ ቅጥያዎችን ይለያሉ
- ✓ ቅጥያዎችን በማጣመር ቃላት ይመሰርታሉ።
- ✓ የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ ዋናውን ሀሳብ ይገልፃሉ።
- ✓ የስርዓተ ነጥቦችን ትርጉም ተረድተው የንባብ ድምፀቱን ጠብቀው ያነባሉ።

አጠቃላይ የምዕራፉ ይዘቶች

- ➢ አዳምጦ ማስታወሻ መያዝ
- ➢ ቃላትን ማጣመርና መነጠል
- ➢ አንቀፅ ማዋቀር
- ➢ ተመሳሳይ ቃላት
- ➢ የወል ስሞች

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ‹‹ ኦሎምፒክን በባዶ እግር ››

የትምህርቱ  አቀራረብ

- ❖ ተማሪዎቹ ወደማዳመጥ ተግባር ከመሄዳቸው በፊት ለማዳመጥ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው በተማሪ መፅሀፍ ላይ የሰፈሩትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ ሁለት ሁለት እየሆኑ እንዲወያዩና ስዕሉን ተመልክተው እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡ ከውይይቱ የተረዱትን እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፡፡
- ❖ ከዚያም የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን ደጋግመው እንዲያነቧቸው በማድረግ በቀላሉ አዳምጠው እንዲመልሱ የሚችሉበትን መንገድ ይግለፁላቸው፡፡
- ❖ በተጨማሪም የሚነበበውን ታሪክ ሲያዳምጡ ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታዎሻ እንዲይዙ በማስረዳት ምንባቡን በርጋታ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡

አበበ ቢቂላ ነሐሴ 30 1925 ዓ/ም በሰሜን ሸዋ አውራጃ ደነባ ልዩ ስሟ ጆቶ ከምትባል ስፍራ ተወለደ፡፡ ብላቴናው አበበ  እንደ አካባቢው ልምድ በእረኝነትና በቄስ ትምህርት ተሰማርቶ በአስራ ሁለት አመቱ ትምህርቱን አጠናቀቀ፡፡ በዚህ በጨቅላ እድሜው ስመጥር የገና ጨዋታ ተጫዋች እንደነበረ ይነገርለታል፡፡ በ1934ዓ.ም አዲስ አበባ መጥቶ በክብር ዘበኛ በወታደርነት ይቀጠርና በገና ጨዋታ እና በስፖርት እራሱን እያዳበረ ቆየ፡፡ ወዲያው በ1936ዓ.ም የአራት ልጆች እናት  የሆነችለትን  ወ/ሪት የውብዳር ወልደ ጊዮርጊስን አገባ፡፡

በህዳር ወር 1938ዓ.ም በአስራ ስድስተኛው በሜልቡር ኦሎፒክ ላይ የተሳተፉ መለያ ስም የተፃፈበትን ልብሳቸውን ለብሰው ሀገራቸውን ወክለው የተወዳደሩትን ወጣቶች ባየ ጊዜ ምን ያህል ስሜት እንዳላቸው ተገረመ፡፡ እሱም እንደነሱ ለመሆን  እንደወሰነ ይጠቅሳል፡፡ በዚሁ ዓመት በብሄራዊ ሰራዊት የእርስ በእርስ  ውድድር ላይ ተሳትፎ በአምስት ሺ ሜትር እና በአስር ሺ ሜትር ሩጫ የብሄራዊውን ክብረ ወሰን  የያዘው የጊዜው  የስፖርት ጀግና ዋሚ ቢራቱ እና አበበ በማራቶን ውድድሩ ሲገጥሙ ተመልካቹ ዋሚ ያሸንፋል ብሎ ነበር የሚጠብቀው፡፡  ነገር ግን  አበበ ይህን ውድድር በቀላሉ ማሸነፍ ስለቻለ ተይዞ የነበረውን ክብረ ወሰን የራሱ ማድረግ ችሏል፡፡ በዚህ ድሉም ለ1942ዓ.ም ለሮም ኦሎፒክ በተወዳዳሪነት ለመመረጥ በቅቷል፡፡

1. እስካሁን ካነበባችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ?
2. ሻበል አበበ ቢቂላ ኦሎፒክን በባዶ እግር ለምን የተባለ ይመስላችኋል?

ሀገራቸውን ወክለው በዚህ ውድድር ላይ ለመሳተፍ ከአሰልጣኙ ጋር ወደ ሮም ካመሩት የኢትዮጵያ ተወዳዳሪዎች መካከል ለማራቶን ሩጫ የተመረጡት አበበ ቢቀላና አበበ ዋቅጅራ ነበሩ። አሰልጣኙም በዚያን ወቅት የጊዜውን ምርጥ የማራቶን ተወዳዳሪዎች የነበሩትን ኮከቦች አንድ ባንድ ካስተዋወቃቸው በኋላ በደንብ እንዲዘጋጁ አደረጋቸው። በውድድሩ ወቅትም አበበ ቢቂላ በሁለት ሰዓት ከአስራ አምስት ደቂቃ ከአስራ ስድስት ነጥብ ሁለት ሴኮንድ(2፡15፡16.2) በማጠናቀቅ የአለምን ክብረ ወሰን ሰብሮ የወርቅ ሜዳሊያን ማግኘት ቻለ።

አበበ ቢቂላ በተከታታይ ውድድሮችን እያሸነፈ ክብረ ወሰኖችን በእጁ እያስገባ ብቃቱንና ተደናቂነቱን ከፍ ማድረግ ቻለ። ለአብነትም ጥቅምት አስራ አንድ ቀን 1957ዓ.ም የጃፓን ቶኪዮ ኦሎምፒክ ላይ ሁለት ሰዓት ከአስራ ሁለት ደቂቃ ከአስራ አንድ ነጥብ ሁለት (2፡12፡11.2) በመግባት የራሱን ክብረ ወሰን ማሻሻል ችሏል። በዚህም ወደ ሀገሩ ሲመለስ ከንጉሰ ነገስቱ የሻንበልነት ማዕረግንና አዲስ ቮልስዋገን ቢትል መኪና መቀበል ችሏል።

ሻንበል አበበ ቢቂላ ሮምን የወረረው ብቸኛው ወታደር ከተወዳደረባቸው አስራ አምስት ውድድሮች አስራ ሁለቱን በአንደኝነት ማጠናቀቅ ችሏል። ኢትዮጵያዊ ጀግና በተወለደ በአርባ አንድ አመቱ የሜክሲኮውን ሩጫ አቋርጦ መንገድ ዳር በወደቀ በስድስት አመቱ ጥቅምት 1966 ዓ.ም የህይወት ትግሉን ጨርሶ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። የቀብር ስነ ስርአቱም ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃ/ስላሴ፣ ዘመድ ወዳጆቹና አድናቂዎቹ በተገኙበት በቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ተከናውኗል።

ምንጭ ‹‹አበበ ቢቂላ የተወለደው መቼ ነው በሚል ጋዜጠኛ ሄኖክ ያሬድ በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ነሀሴ አምስት 2005ዓ.ም ከቀረበው ፅሁፍ ለማስተማሪያነት በሚያመች መንገድ ተሸሽሎ የተወሰደ›› ።

❖ *ያዳመጡትን ታሪክ በቃላቸው በድርጊት ቅደም ተከተል እንዲተርኩ ያበረታቷቸው በመቀጠል ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በማሰራት ተማሪዎች ያዳመጡትን ምንባብ በትክክል ሀሳቡን ተረድተው መግለፅ መቻላቸውን ያረጋግጡ። ያዳመጡትን ምንባብ መልዕክት ያልተረዱት ከሆነ በድጋሜ በማንበብ መልዕክቱን እንዲጨብጡት ለማስቻል ጥረት ያድርጉላቸው።*

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

- ❖ አንብቦ መረዳት በሚለው ክፍል የቀረበውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በቡድን ሆነው ውይይት እንዲደርጉ ይግለጹላቸው:: በውይይቱ ሁሉም ተማሪዎችእንዲሳተፉ ያበረታቷቸው::የተወያዩትን ሀሳብ እንዲገልፁ ካደረጉ በኋላ ምንባቡን በግላቸው በለሆሳስ እንዲያነቡ ይግለፁላቸው:: በንባብ ወቅት በፅሁፉ ውስጥ ያሉ ስርዓተ ነጥቦችን ትርጉም ተረድተው ድምፀቱትን ጠብቀው እንዲያነቡ ያስረዷቸው::
- ❖ ተማሪዎች በግላቸው በሚያነቡበት ጊዜ ለማንበብ የሚቸገሩ (ማየት የተሳናቸው) ተማሪዎች ካሉ የሚያግዟቸውን ተማሪዎች መመደብ አይዘንጉ::
- ❖ ከንባብ በኋላ የስርዓተ ነጥብ አነባበብ ድምፀት ጠብቀው ማንበብ መቻላቸውን ለማረጋገጥ አንድ ወንድ አንዲት ሴት ተማሪዎች በተራ ድምፅ አውጥተው እንዲያነቡ በማድረግ ድምፀቱን ጠብቀው ማንበብ መቻላቸውን ይፈትሹ::
- ❖ ተማሪዎቹ በትክክል ማንበብ መቻላቸውን ካረጋገጡ በኋላ ወደ ቀጣይ ተግባር ይሸጋገሩ:: ስህተቶች ካሉ ግን እርስዎ በአርአያነት ያንብቡላቸው እና የእርስዎን አነባበብ ተከትለው በድጋሜ እንዲያነቡ በማድረግ ትምህርቱን ያጠናክሩ::
- ❖ ከምንባቡ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ማብራሪያ እንዲሰጡ፣ ለተዘረዘሩት ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ተመሳሳይ እና አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያግዟቸው:: ተማሪዎቹ ምንባቡን ካነበቡ በኋላ በጥያቄዎች ላይ ሁሉም ተማሪዎች መሳተፋቸውንና በትክክል መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ:: በሰጡት ምላሽ ላይ ስህተቶች ካሉ ተገቢውን እርማት በቡድን በቡድን ሆነው እንዲያስተካክሉ ያድርጉ::

በናሙና የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሶስት፡-

ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ::

ሀ. ሀሴት፣ፍስሃ

ለ. ጥንካሬ

ሐ. የበለጠ

መ. ምሳሌ

ሠ. በግብርና የሚተዳደር

ረ. ሁልጊዜ

ሰ. ስኬታማ

ሸ. ተቃርኖ

ቀ. ደስታ

ተግባር አራት፡-

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. የካበተ ዕውቀት፣ችሎታ

ለ. ታዋቂ፣በበጎ ስራ የሚታወቅ

ሐ. የተሻሻለ ድል

መ. ተወዳጅነት፣ተከባሪነት

ሠ. መሪ፣ ዋና

ረ. ተደጋጋሚ ስኬት

ሰ. የክብር ሽልማት

ሸ. ቦታ

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ

- በክፍል ሶስት የቀረበው ይዘት ቃላት ሲሆን ተማሪዎች ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ፣ ከቀረበላቸው ቃላት ውስጥ ዋና ቃልና ቅጥያ ለይተው እንዲፅፉ እና ከተዘረዘሩ ቃላት ውስጥ ተመሳሳይ ቃላትን ለይተው እንዲመርጡ የሚያግዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡
- በመጀመሪያ ተማሪዎቹ የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ ምንነት እንዲያስታውሱ በጥያቄ ያነቃቋቸው፡፡ ከዚያም በተማሪ መማሪ መጽሐፍ ውስጥ በተግባር አንድ ስር ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን እየመረጡ እንዲያዛምዱ ይግለጹላቸው፡፡

❖ በተግባር ሁለት ስር የቀረቡትን ቃላት ዋና ቃሉንና ጥገኛ ምእላዱን እየነጠሉ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

❖ ተግባራት ሶስት ስር ለቀረቡት ቃላት ደግሞ ይበልጥ በፍቺ የሚመስለውን መርጠው እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

❖ በመጨረሻም ዋና ቃሉንና ቅጥያውን እያጣመሩ ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

❖ የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መመለሳቸውን ያረጋግጡ፡፡ ያልመለሱት ጥያቄ ካለ ማስተካከያ መልስ ይስጧቸውና አስተካክለው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

## በናሙና የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

በ‹‹ሀ›› ረድፍ የቀረቡትን ቃላት በ‹‹ለ›› ረድፍ ከተዘረዘሩት በፍች የሚስማሙትን በመምረጥ አዛምዱ

| | |
|---|---|
| 1. መ | 6. ሀ |
| 2. ረ | 7. ሸ |
| 3. በ | 8. ሠ |
| 4. ሐ | 9. ሰ |
| 5. ቀ | 10. ለ |

ተግባር ሁለት፡-

የሚከተሉትን ቃላት በቀረበው ምሳሌ መሰረት ዋና ቃሉን እና ቅጥያውን ለይታችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ከ - ተወዳዳሪ - ዎች - ኡ

ለ. መረጥ - ኣችሁ

ሐ. ጓደኝ - ኦች - ኣቸው - ን

መ. ውጤት- ኣማ - ነት - ኣችን

ሠ. ስኬት - ኣማ - ነት

ረ. ሀገር-ኣችን

ሰ. ወታደር- ኦች-ኣችን

ሸ. ቤት -ኣቸው- ን

ቀ. ሰው -ኦች-ኡ

ተግባር ሶስት፡-

ከዚህ ቀጥሎ ከ ተራ ቁጥር ከ1- 6 ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ የያዘውን ፊደል እየመረጣችሁ መልሱ፡፡

1. መ    4. መ

2. ሐ.    5. ሀ

3. መ    6. ለ

ተግባር አራት

ቀጥሎ ተነጣጥለው የቀረቡትን ቅጥያዎች በማጣመር ቃላት መስርቱ፡፡

ሀ. ዘመናዊነት

ለ. ክብርት

ሐ. ወጣቱ

መ. ሴትዮዋ

ሠ. ሸጡት

ረ. በጥልቀት

ሰ. በአደገችበት

# ክፍል አራት ጽህፈት

## አንቀፅ መፃፍ

❖ በዚህ ክፍል የቀረበው አንቀጽ የማዋቀር ይዘት ነው፡፡ ይህንን ይዘት በምዕራፍ አንድ የአምስተኛ ክፍል የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው አንቀጽ ለመፃፍ የሚያስችላቸውን ቢጋር በማዘጋጀት አንቀጽ ለመፃፍ ሙከራ ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡በምዕራፍ አንድ ላይ የሞከሩትን የአንቀጽ አፃፃፍ ልምምድ በምእራፍ ሁለት አጠናክረው የአንቀጽ ምንነትንና ክፍሎችን ለይተው እንዲገነዘቡ ይጠበቃል፡

❖ ስለዚህ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የቀረበውን የአንቀጽ ማስታወሻ እስኪረዱ ድረስ በደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡ በተጨማሪም በጥያቄና መልስ የአንቀጽ ምንነትንና ክፍልን በሚገባ እንዲገልፁ የማጠናከሪያ አጭር ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡ ከዚህ ቀድም ስለአንቀጽ ያላቸውን እውቀት እና አሁን የተሰጣቸውን ማብራሪያ ተጠቅመው ከተሰጣቸው ርዕስ አንዱን በመምረጥ ቢጋር አዘጋጅተው አንቀጽ እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

❖ የፃፉትን አንቀጽ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተቀያይረው እንዲያነቡና ትችት እንዲሰጣጡ ይግለፁላቸው፡፡ ያቀረቡትን ትችት ትክክለኝነት ካረጋገጡ በኋላ በናሙናነት የተመረጠ አንቀጽ ከተማሪዎቹ በመምረጥ ያቅርቡላቸው፡፡ በተሰጣቸው ማስተካከያ የፃፉትን አንቀጽ ደግመው አሻሽለው እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

❖ ተማሪዎች አሻሽለው የፃፉትን በመሰብሰብ በአንቀጽ ውስጥ መካተት ያለበትን ሀሳብ ተካቶ መቅረቡን፣ በተገቢው ቦታ ስርዓተ ነጥብ መጠቀማቸውን፣ የአንቀጽ ክፍሎችን በትክክል ማዋቀር መቻላቸውን ይፈትሹ፡፡ የመፃፍ ክሂል በድግግሞሽ የሚገኝ በመሆኑ ለተማሪዎቹ ተደጋጋሚ ተግባር በመስጠት ልምምድ እንዲያደርጉ ይርዷቸው፡፡

## መርጃ መሳሪያ

የተዘጋጀ የአንቀጽ ክፍሎችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ክፍል አምስት:- ሰዋስው

## የወል ስሞች

❖ በምዕራፍ አንድ ክፍል አምስት ላይ የተጸውዖና የወል ስም መማራቸው ይታወሳል፡፡በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎቹ ቅድመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ከቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የወል ስም የሆኑትን ለይተው እንዲያሳዩ፣

በራሳቸው የወል ስሞችን ፈልገው ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ፣ ከተዘረዘሩት ስሞች ውስጥ የወል ስሞችን ለይተው እንዲያሳዩ የሚለማመዱበት ተግባር ቀርቧል፡፡

- ❖ በመጀመሪያ የወል ስምን እንዲያስታዉሱ በጥያቄና መልስ ይከልሱላቸው፡፡ ከዚያም ከቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች የወል ስም የሆኑትን ለይተው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ❖ በመቀጠል የወል ስም የሆኑ ቃላትን ፈልገው ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያስረዷቸው
- ❖ ተዘርዝረው ከቀረቡት የተለያዩ ስሞች ውስጥ የወል ስም የሆኑትን ብቻ ለይተው እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡ የሰጡትን መልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ የወል ስሞችን በትክክል መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ❖ በመጨረሻም ከዚህ በታች የቀረበውን የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎት በተመለከተ ተማሪዎች ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡ ከዚያም በምሳሌው መሰረት የተለያዩ የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎቶችን በተመከለተ የተለያዩ መልመጃዎችን በመስጠት ያሰሯቸው፡፡

## የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎት

ጥገኛ ምዕላድ የተለያየ ሰዋስዋዊ አገልግሎት ያለው ሲሆን የተወሰኑትን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

1. ባለንብረትነትን ያመለክታሉ

   ምሳሌ፡-

   ገንዘብ-ኤ- ገንዘቤ - የእኔ

   ገንዘብ-ኣችን-ገንዘባችን- የእኛ

   ገንዘብ-ሽ ገንዘብሽ -ያንቺ

2. ብዙ ቁጥርን ያመለክታሉ

   ምሳሌ፡-

| ነጠላ ቁጥር | ጥገኛ ምዕላድ | ብዙ ቁጥር |
|---|---|---|
| በሬ | ዎች | በሬዎች |
| ፈረስ | ኦች | ፈረሶች |

ከበደ　　　　　　　　እነ　　　　　　　　እነከበደ

3. ወገንን ያመለክታሉ

ምሳሌ፡-

ኬንያ　　　　　-ኣዊ　　　　ኬንያዊ

አፍሪካ　　　　　-ኣዊ　　　　አፍሪካዊ

ኢትዮጵያ　　　　- ኣዊ　　　ኢትዮጵያዊ

4. እምርነትን ያመለክታሉ

ምሳሌ፡-

ስም　　　　ጥገኛ ምዕላድ　　እምር ስም

ልጅ　　　　-ኡ　　　　　ልጁ

በግ　　　　-ኡ　　　　　በጉ

5. ጾታን ያመለክታሉ

ምሳሌ፡-

ቆንጆ　-ኢት　　ቆንጂት

ሙሽራ　-ው　　ሙሽራው

ልጅ　　-ኢት　　ልጂት

6. የአይነት ገላጭን ያመለክታሉ

ምሳሌ፡-

አሽዋ　　-ኣማ　　　አሽዋማ

ተራራ　-ኣማ　　　ተራራማ

ድንጋይ -ኣማ　　　ድንጋያማ

ለናሙናነት ለተመረጡ ተግባራት የቀረበ መልስ

ተግባር አንድ፡-

በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የወል ስሞች ለይታችሁ አውጡ፡፡

ሀ. ተማሪዎች፣ ክፍል

ለ. እድር፣ሰዎች፣አካባቢ

ሐ. መኪና፣ እንስሳት፣ሰዎች

መ. ቅርሶች

ረ. ተማሪዎች፣ ፈተና

ሠ. እፅዋት

ተግባር ሶስት

በምዕራፍ አንድ በተማራችሁት መሰረት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የስም አይነቶች የወል ስሞችን ብቻ ለይታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

| | |
|---|---|
| ዓሳ | ቅርስ |
| ልጅ | ወንበር |
| ሰው | |

መርጃ መሳሪያ

ለወል ስሞች የተዘጋጀ ሰንጠረዥ

# ምዕራፍ ሶስት (፫)

## ቃላዊ ግጥም

ክፍለ ጊዜ 18

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

- ✓ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ በመስጠት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ ግጥም ጽፈው በትክክል ያነባሉ፡፡
- ✓ ቅንፍንና እዝባርን በአረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ አዳዲስ ያወቁትን ቃላት በመጠቀም ገላጭ ፣ተራኪና ቃላዊ ግጥም በመጻፍ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያነባሉ፡፡

የምዕራፉ ይዘቶች

- ማድመጥና ግጥም መግጠም
- ግጥም አስመስሎ ማንበብ
- የግጥም ጭብጥ መጻፍ
- ቅንፍና እዝባር
- ተቃራኒ ቃል

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

# የእርሻ ጊዜ ቃላዊ ግጥም

### የትምህርቱ አቀራረብ

❖ መምህር ወደእለቱ ትምህርት ከመሄድዎ በፊት የሚከተለውን ቃላዊ ግጥም በማንበብ ተማሪዎቹን ያነቃቁ፡፡

እቴሜቴ የሎሚ ሽታ፣

እናት አባትሽ ምን አሉሽ ማታ፣

ምንም ምንም ምንም አላለኝ፣

ትምህርትሽን ተማሪ አሉኝ ፤

ለማስተማር ቃልኪዳን ገብተው፣

መለውልኛል ጋሻጦር ደፍተው ፤

ማላ ማላ የጎበዝ ማላ፣

ፉት ይላታል እንደጉሽ ጠላ፡፡

❖ ያነበቡላቸው ግጥም ምን አይነት ግጥም እንደሆነ እንዲለዩ ይጠይቋቸው፡፡ የሰጡት መልስ ትክክል ይሁንም አይሁንም ማስተካከያ ሳይሰጡ ከቀጣዩ ትምህርት በኋላ ሊያውቁት እንደሚችሉ በመንገር ወደቀጣዩ ስራ ይሂዱ፡፡

❖ በመቀጠል በመምህሩ መምሪያ ላይ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም ከማስደመጥዎ በፊት በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

❖ በመጀመሪያ የቃላዊ ግጥም ምንነት እንዲገልጹ ይጠይቋቸው፡፡ ተማሪዎቹ የሚሰጡትን መልስ ተቀብለው ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ ሳይሰጡ ወደቀጣዩ ጥያቄ ይለፉና በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረበውን ስዕል ተመልክተው የተረዱትን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

❖ በመቀጠልም ቀድሞ እርስዎ እንዳቀረቡላቸው አይነት ግጥም የሚያውቁት ካለ ለወንዶቹም ለሴቶቹም ዕድል በመስጠት ሙከራ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡

❖ ከዚያም በማዳመጥ ጊዜ ለመመለስ እንዲያግዛቸው ያዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን ቀድመው ደጋግመው እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡

❖ ተማሪዎቹ ለማዳመጥ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጡና ሲዳምጡ አዳዲስ ቃላትን እንዲጽፉ በመንገር የሚደመጠውን ቃላዊ ግጥም በዝግታ አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡

## በእርሻ ጊዜ የሚገጠም ቃላዊ ግጥም

የበሮቹ ቄስ የበሬው መምህር

አቆላላፊ ክምር በክምር፡፡

ሐምሌ ነሐሴ ያልተራብ ሰው

ሞፈር ቀንበሩን ቀሚስ ያልብሰው፡፡

ጀርጃራው ፈንዛ ባንተ አልደረስኩም

ያሽኮበኩባል ጮሌው እንደርኩም፡፡

ሚያዚያ ግው ሲል ግንቦት ሲያገሳ

አከናናቢ ጎድጓዳ ማሳ፡፡

ሆ ይላል ገበሬ

ሆ ይላል ገበሬ

ዲብ እያፈረሰ በሽልማ በሬ፡፡

በርዬ በርዬ

አንተን የቻለ ሰው

ቶሎ ቶሎ ብለህ

አንጀቴን አርሰው

እረኛህ ያለቅሳል

ምሳ እያነሰው፡፡

በሬና ገበሬ ቢጣሉም አይበጅ

እንዲያ ስተት ብሎ ይጠመዳል እንጂ

እረስ ሽልም እረስ መጋል

እንድን በላ ገብስ እንድንለሰልስ፡፡

- ሲያዳምጡ የጻፏቸው አዳዲስ ቃላት ካለ ይጠይቋቸውና በረሳቸው መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ በራሳቸው መመለስ ካልቻሉ እርስዎ መልሱን ይግለጹላቸው፡፡
- በመቀጠል ባዳመጡት ግጥም መሰረት ያልተሟሉ ስንኞችን እያስታወሱ አሟልተው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- በትክክል ያላሟሉት ስንኝ ካለ ለሁለተኛ ጊዜ ግጥሙን በማንበብ እያዳመጡ እንዲያሟሉ ያድርጉ፡፡
- ለሶስተኛ ጊዜ ያላሟሉት ካለ እያስታወሱ እንዲጽፉ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም እርስ በርስ እንዲተራረሙ በማድረግ በትክክል መስራታቸውን ለማረጋገጥ በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በዚህ ጊዜ ሁሉም ተማሪ ተግባሩን በትክክል መስራቱን ይፈትሹ፡፡
- ካዳመጡት ግጥም ውስጥ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ሰጥተው ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- በቀረቡት አዳዲስ ቃላት አረፍተ ነገር መመስረት መቻላቸውን ለማረጋገጥ የሰሩትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በመጨረሻም በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም ያዳመጡትን አነባበብ ስልት ተከትለው በማንበብ የግጥሙን ጭብጥ እንዲናገሩ ያግዟቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

- ወደማንበብ ተግባር ከመግባታቸው በፊት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ከተወያዩ በኋላ የሚያውቁትን የፍቅር ቃላዊ ግጥም ካለ በቃላቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- የቃላዊ ግጥሞች ማህበራዊ ፋይዳ ምን ሊሆን እንደሚችል በውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- ❖ የሙሾ እና የሰርግ ቃላዊ ግጥሞች የሚኖራቸውን ልዩነት ምን እንደሆነ እንዲያብራሩ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ በመጀመሪያ ምንባቡን ለማንበብ ጥንድ ጥንድ ሆነው ለማንበብ ያዘጋጇቸው፡፡
- ❖ አንዱ ሲያነብ ሌላው እያዳመጠ የሀረግ አከፋፈልንና ዜማን ጠብቀው ማንበብ መቻላቸውን እያረጋገጡ እንዲያነቡ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ በዚህ ጊዜ በምንባቡ ውስጥ የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች በክፍል አንድ ማዳመጥ ላይ ባደረጉት የግጥም ንባብ ልምምድ ድምፀቱን ጠብቀው ማንበብ መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
- ❖ በተግባር አንድ የቀረበውን የእውነት ሐሰት ጥያቄ በምንባቡ መሰረት ምክንያት እየሰጡ በጽሑፍ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ እንዲሁም በምርጫ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል እየመረጡ በደብተራቸው እንዲጽፉ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ የሰጡት ምላሽ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ እያንዳንዱን ተማሪ በመጠየቅ ይፈትሹ፡፡
- ❖ በተማሪዎች ያልተመለሰ ጥያቄ ካለ ትክክለኛውን መልስ እርስዎ ያስረዷቸውና ማስተካከያውን እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም በመጽሐፋቸው ውስጥ የቀረበውን ተራኪና ገላጭ ድርሰት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች

ተግባር ሁለት፡-

ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት የተለያዩ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሰ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ፡፡

1. ለ
2. ለ
3. ለ
4. ሐ

5. ሐ

6. ለ

7. ሐ

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### አዳዲስ ቃላት

❖ ከዚህ በፊት በምዕራፍ አንድና ሁለት የተማሩትን የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲያስታዉሱ በማድረግ በዚህ ክፍል ደግሞ ስለ ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንደሚማሩ ያስተዋውቋቸው፡፡

❖ ከዚያም የቃላት ተቃራኒ ፍቺ ምን እንደሆነ ይግለጹላቸው፡፡

❖ ተግባር አንድ በአዛምድ መልክ ለቀረቡት በ‹‹ሀ›› ስር ላሉት ቃላት ተቃራኒ በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩት እየመረጡ እንዲመልሱ ያስረዷቸው፡፡

❖ በተግባር ሁለት በምርጫ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተቃራኒ የሆኑትን እየመረጡ እንዲመልሱ ይግለጹላቸው፡፡

❖ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡

❖ ማስተካከያ መስጠት የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ ትክክለኛውን መልስ ያስረዷቸውና አስተካክለው እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች

ተግባር አንድ

በ‹‹ሀ›› ረድፍ ለቀረቡትቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ‹‹ለ›› ረድፍ በመምረጥ በትክክል አዛምዱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. ሠ | 4.ለ | 7. መ |
| 2. ሰ | 5.ሀ | 8. ረ |
| 3. ሸ | 6.ሐ | |

ተግባር ሁለት

ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ትርጉም ያላቸውን ፊደል ብቻ ምረጡ፡፡

1. ሐ
2. ለ
3. ሐ
4. መ
5. ለ

መርጃ መሳሪያ

- የቃላት ተቃራኒ ፍቺ የያዘ ሰንጠረዥ
- የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ በንጽጽር የያዘ ሰንጠረዥ

## ክፍል አራት፡- ጽህፈት

ቅንፍና እዝባር

- ❖ መምህር ስለቅንፍና እዝባር ስርአተ ነጥብ ምንነትና አገልግሎት በተማሪዉ መጽሐፍ የቀረበውን ማስታወሻ በደብተራቸው ጽፈው እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡
- ❖ አንብበው ሲያጠናቅቁ ምን እንደተረዱ በመጠየቅ፣ በሰጡት መልስ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በተግባር አንድ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እዝባር ተጠቅመው አሳጥረው እንዲጽፉ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ ከዚያም በተግባር ሁለት በተሰጣቸው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የቅንፍን ስርአተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታ ተጠቅመው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠታቸውን ይገምግሙ፡፡
- ❖ በትክክል መልስ ከሰጡ መልካም ካልሆነ ግን እርስዎ ትክክለኛውን መልስ ያስረዷቸውና እርማት እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡
- ❖ ከቀረበላቸው ርዕስ አንዱን መርጠው ግጥም እንዲጽፉና ስርአተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታ እንዲጠቀሙ ይግለጹላቸው፡፡

- ❖ የግጥም አጻጻፍና የስርአተ ነጥብ አጠቃቀማቸውን እንዲገማገሙ የጻፉትን ግጥም ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲቀያየሩ ያድርጉ፡፡
- ❖ የጓደኞቻቸውን ግጥም ገምግመው ሲያጠናቅቁ ያገኙትን ጠንካራ ጎን እና መሻሻል ያለባቸውን ሀሳቦች እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ❖ ተማሪዎቹ የሰጡትን አስተያየት መሰረት ያደረገ የማስተካከያ አስተያየት ይስጧቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም የትምህርቱን ማጠቃለያ ሰጥተው ያጠናቁ፡፡
- ❖ ተማሪዎች በሚፈልጉት ርእስ ዙሪያ ግጥም መጻፍ እንዲለማመዱ ይግለጹላቸው፡

## ክፍል አምስት ሰዋሰው

የጊዜ ተውሳከ ግስ

- ❖ በተማሪው መጽሀፍ የቀረበውን የጊዜ ተውሳከ ግስ ማስታወሻ ጽፈው እንዲያነቡ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ❖ ከዚያም የጊዜ ተውሰከ ግስ አንድ ነገር መቼ እንደተከሰተ ወይም እንደሚከሰት የሚገልጽ መሆኑን ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በማስከተል ከቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የጊዜ ተውሳከ ግስ ለይተው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ ከተዘረዘሩ ቃላት ውስጥ የጊዜ ተውሳከ ግስ የሆኑትን ለይተው በቻርት ውስጥ እንዲያሰፍሩ ያድርጉ፡፡
- ❖ በቀረቡላቸው ተውሳከ ግሶች ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎቹ የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ በማድረግ የጊዜ ተውሳከ ግስን አገልግሎት በትክክል መለየታቸውን ይፈትሹ፡፡
- ❖ በዚህ ምእራፍ መጨረሻ ላይ የሙከራ ፈተና ቢሰጣቸው መልካም ነው፡፡

ለናሙና የተመረጡ ጥያቄዎች

ተግባር አንድ

በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የጊዜ ተውሳከ ግሶች ለይታችሁ ጻፉ፡፡

1. ባለፈው አመት
2. በጧት
3. ትናንት
4. ዛሬ ጧት
5. በሚቀጥለው ዓመት
6. ባለፈው ሳምንት
7. ዘወትር

ተግባር ሁለት

ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላትና ሀረጋት የጊዜ ተውሳከ ግስ የሆኑትን ለይታችሁ በቻርቱ ውስጥ ጻፉ፡፡

| | |
|---|---|
| ወዲያውኑ | አሁን |
| ዛሬ | ያለፈው ዓመት |
| ነገ | ሌሊት |

መርጃ መሳሪያ

የጊዜ ተውሳከ ግስ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች የያዘ ቻርት

# ምዕራፍ አራት (፬)
# ዘመናዊ ግብርና

ክፍለ ጊዜ 18

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች:-

- ✓ አዳምጠው በቃላቸው ይመልሳሉ
- ✓ አከራካሪ አንቀፅ ይፅፋሉ
- ✓ ቃላትን በመገጣጠም ትርጉም ይሰጣሉ
- ✓ የጊዜ ግስን ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ

የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች:-

- ➢ አዳምጦ የቃል ዘገባ
- ➢ ቃላትን በትርጉም መመደብ
- ➢ አከራካሪ አንቀፅ
- ➢ የጊዜ ግስ

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

### ‹‹ ድሮና ዘንድሮ ››

### የትምህርቱ አቀራረብ

- መምህር በቅድመ ማዳመጥ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በጥንድ በጥንድ እንዲወያዩበት ጊዜ ይስጧቸው፡፡ ውይይታቸውን ሲያጠናቅቁ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

- የገለጹትን ሀሳብ አስደግፌው የሚደመጠውን ርዕስ ያስተዋውቋቸውና በርዕሱ **ዙሪያ አንዳንድ ጥቆማ በመስጠት ይበልጥ** ለማዳመጥ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡

- ወደማንበብ ከመሄድዎ በፊት በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የቀረበውን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄ እስኪረዱት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ምንባቡን እያዳመጡ ባዶ ቦታውን እንዲሞሉ ይግለጹላቸውና **ምንባቡን** አንድ ጊዜ በዝግታ ያንብቡላቸው፡፡

ስሜ መስታወት ተበጀ ይባላል፡፡ ተወልጄ ያደኩት እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ትምህርቴን እስከ መጨረሻው መቀጠል አልቻልኩም ነበር፡፡ እናቴ ከአከፋፋዮች አትክልትና ፍራፍሬ ተረክባ ጉልት ላይ በመቸርቸር በምታገኛት ገቢ እንተዳደር ነበር፡፡አባቴ ደግሞ በቀን ስራ ተሰማርቶ የጉልበት ስራ ይሰራ ነበር፡፡ ሆኖም ከሁለቱም የሚገኘው ገቢ ከዕለት ጉርስ የሚተርፍ አልነበረም፡፡ “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንደሚባለው አባቴ በስራ ቦታ በደረሰበት አደጋ በህክምና ቢረዳም ሊተርፍ ባለመቻሉ እኛን ተሰናብቶን ሄደ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እናቴን የማገዝ ሀላፊነቱ በኔ ጫንቃ ላይ ወደቀ፡፡ ለምን ተፈጠርኩ ብየ እስካማርር ድረስ ፈተናዎች ሁሉ አንድ በአንድ ይፈራረቁብኝ ጀመር፡፡ የማይተካው የልጅነት ጊዜዬን እንደ አቻዎቼ ተደስቼና ቦርቄ ሳይሆን በስቃይና በፈተና መግፋት ጀመርኩ፡፡ ‘‘ላያስችል አይሰጥም’’ እንደሚባለው በምችለው አቅም ሁሉ እናቴን በመርዳት ህይወታችንን መግፋቱን ተያያዝነው፡፡ ‘‘ችግር መፍትሄን ይወልዳል’’ እንዲሉ ከዕለታት በአንዱ ቀን የስራ እድል ፈጠራ ስልጠና ለመውሰድ ከተመዘገብኩበት መስሪያ ቤት ስልክ ተደወለልኝ፡፡ እንዴት ስበር እንደደረስኩ አላውቅም፡፡ ብቻ ከቦታው ስደርስ ለስራ ፈጠራ ስልጠና ሊሰጠኝ መሆኑን ስሰማ ወዲያውኑ እኔና እናቴ ከችግራችን የምንወጣበት የብርሃን

ጭላንጭል ብሩህ ሆኖ ታየኝ፡፡ ስልጠናውም እንዴት ሰርቶ መለወጥ እንደሚቻል የሚያስተምር ስለነበር ጆሮዬን የኮረኮሩኝ ያህል በንቃት ነበር ስከታተለው የነበረው፡፡ በስልጠናውም በከተማችን ከሚሰሩ የተለያዩ የስራ መስኮች መካከል አንዱ የከተማ ግብርና እንደሆነ ተረዳሁ፡፡

1. ተማሪዎች እስከአሁን ካዳመጣችሁት ታሪክ ምን ተረዳችሁ?
2. ባለታሪኳ ወደፊት ምን ሊያጋጥማት ይችላል ብላችሁ ገምትቱ?

የከተማ ግብርና በአነስተኛ ቦታ፣አቅምና ጉልበት ብዙ ምርት ማስግኘት የሚያስችል፣ በዘመናዊ አሰራር የተደገፈ ውጤታማ ስራ ነው፡፡ በችግር እንድንኖር ያስገደደንን አስከፊ ድህነት ከላያችን ላይ ለማራገፍ በወሰድኩት ስልጠና እና ባገኘሁት አነስተኛ ብድር ባለን የጓሮ መሬት ላይ እንደ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ካሮት፣ ቲማቲም፣ ቀይስር፣ ሙዝ፣ ብርቱካንና ፓፓያ የመሰሳሰሉትን አትክልትና ፍራፍሬዎች ለማምረት ወደ ስራ ገባሁ፡፡ ለማመርታቸው ምርቶች ውጤታማ ሊያደርጉኝ የሚያስችሉ የተለያዩ የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን ማለትም የአፈር ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና ፀረ ተባይ … ወዘተ መጠቀም ጀመርኩ፡፡ በዚህም በትንሽ መሬት ላይ ብዙ ምርት ማግኘት ቻልኩ፡፡ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ገቢ ማስገኛና የምግብ ዋስትናን  በማረጋገጥ የአመጋገብ ስርዓትን በማስተካከልና መሰል ችግሮችን ለማቃለል ያገኘሁትን ልምድ በመጠቀም በአቅራቢያዬ ላሉ ነዋሪዎች ማስተማር ጀመርኩ፡፡

ሰርቼ ከማገኘው ገንዘብ ከእለት ፍጆታ የሚተርፈንን በባንክ ማስቀመጥ ጀመርኩ፡፡ የሚገኘው ምርት እያደገ ሲመጣ  አነስተኛ ሱቅ በመክፈት እናቴ የጉሊት ስራዋን አቁማ ሱቁ ላይ  እንድትሰራ ማድረግ ቻልኩ፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬው ምርት በጣም እያደገ ሲመጣና ከከፈትነው ሱቅ የምናገኘው ገቢ ሲጨምር ባለቤቴ የተሻሻሉ የወተት ምርት የሚሰጡ ላሞችን ገዝቶ መስራት ጀመረ፡፡ የወተት ምርቱም በጣም ተፈላጊነቱ እየጨመረ ስለመጣ በምናገኘው ገቢ የኑሮ ዘይቤያችንም እየተሻሻለ መጣ፡፡ ከራሳችን አልፈን  ለሌሎች የስራ እድልን መፍጠር ቻልን፡፡

በአሁኑ ስዓት ከአከፋፋዮች ተረክበን ጉልት ላይ ከመቸርቸር አልፈን ባስመዘገብነው ውጤት በአካባቢያችን ላሉ አትክልትና ፍራፍሬ መደበሮች ምርታችንን በማቅረብ ቋሚ ደንበኛችን ማፍራት ቻልን፡፡ ከከተማ ግብርና ሌላውና ዋነኛው የስራ ዘርፍ የእንስሳት እርባታ ሲሆን ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል አጭር ሰልጠና ወስዶ ሊሰማራበት የሚችል እና የሥራ ዕድል ለመፍጠርም የሚያስችል መስክ ነው፡፡ በመሆኑም እኔና ባለቤቴ በተከራየነው ትንሽ ቤት ውስጥ እየሰራን ያለነው የወተት ምርቱ መጠን እየጨመረ ሲመጣ  ለሌሎች  የምናከፋፍለውን ከመንግስት ብር ተበድረን በመጨመር

የወተት ተዋፅዖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በመገንባት መስራት ጀመርን፡፡ በዚህም የስራ እድል የፈጠርንላቸው ግለሰቦች ቁጥር በእጅጉ ጨመረ፡፡ በአሁኑ ወቅት የተጋረጠብንን ድህነት አሽቀንጥረን በመጣል ለበርካታ ሰዎች የስራ እድል በመፍጠር እና በከተማው የሚስተዋለውን የወተትና የአትክልት አቅርቦት ለማሻሻል የበኩላችን እየተወጣን እንገኛለን፡፡

- ❖ በመጀመሪያ ማዳመጥ ጊዜ ምን ያህሉን ጥያቄ እንደመለሱ ይጠይቋቸው፡፡ ከዚያም ድጋሜ ማንበብ አስፈላጊ ሆኖ ከታየዎት ድጋሜ ያንብቡላቸው፡፡ በሁለት ጊዜ ማዳመጥ ሙሉ በሙሉ መመለስ ያልቻሉ ተማሪዎች ካሉ ከታች የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸውና ያዳመጡትን በማስታወስ ባዶ ቦታውን እንዲሞሉ ያግዟቸው፡፡

ጥቁር ሰሌዳ ላይ የሚጻፉት ቃላትና ሀረጋት

ጫንቃ ላይ

ከተመዘገብኩበት

የከተማ ግብርና

አቻዎቼ

የተስፋ ጭላንጭል

በባንክ ማስቀመጥ

ማቅረብ

እየጨመረ

- ❖ በመጨረሻም ካዳመጡ ምንባብ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ዓረፍተ ነገሮች እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ መስራታቸውን ለማረጋገጥ እያንዳዳቸው የሰሩትን እንዲናገሩ በማድረግ ይፈትሹና የዕለቱን ትምህርት ያጠናቁ፡፡

- ❖ በመጨረሻም በተግባር አራት ስር የተገለፀውን ጥያቄ ተማሪዎች ከዝቅተኛ

ገቢ እንዴት ወደ ከፍተኛ የገቢ መጠን ማደግ እንደሚቻል በቡድን እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠልም በቡድን የተወያዩትን ሀሳብ በየተራ እየወጡ ንግግር እንዲያደርጉ ይርዷቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ ንግግር አድርገው እንደጨረሱ እርሰዎ የማጠቃለያ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡

## ክፍል ሁለት ንባብ

- መምህር ወደዕለቱ ትምህርት ከመግባትዎ በፊት ከታች የቀረበውን ግጥም ለተማሪዎቹ በማንበብ ያነቃቋቸው፡፡ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ግጥሙን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉና እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

እስኪ ላመስግንህ እንዲህ ልበልና፣

የሀገር ምሶሶ አለይኝታ ነህና፡፡

ደከመኝ ሰለቸኝ ፈፅሞ ማታውቀው፣

የሁሉንም ጎጆ ኩራት ያለበስከው፡፡

ሁሉም ተደስቶ ስቆ ሚቦርቀው፣

አንተነህ ገበሬ መሰረት የሆንከው፡፡

- በመቀጠል የዕለቱን የንባብ ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው፡፡ ከዚያም በቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

- ምንባቡን በግላቸው በለሆሳስ እንዲያነቡና የሚያጋጥማቸውን አዳዲስ ቃል በደብተራቸው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

- ንባባቸውን ሲያጠናቅቁ የጻፏቸውን አዳዲስ ቃላት ይጠይቋቸውና በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ፡፡ ለቀረቡት አዳዲስ ቃላት በራሳቸው ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ ከዚያም ከጓደኞቻቸው ጋር በጋራ እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም ለመመለስ ያዳገታቸው ቃል ካለ ትክክለኛ መልስ ይስጧቸው፡፡

- ከምንባቡ የወጡ ቃላት በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ በምንባቡ ውስጥ እና ከምንባቡ ውጭ ባላቸው ፍቺ ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ይግለጹላቸው፡፡

❖ የቃላትን አገባባዊ እና ከአገባብ ውጪ ያለውን ፍቺ የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር በመጻፍ በምሳሌ አስደግፈው ያስረዷቸው፡፡

ምሳሌ1= በመዘርጋት የሚለው ቃል በምንባቡ ውስጥ ያለው ፍቺ

- ዘነበ ዘመናዊ የግብርና ዘዴ በመዘርጋት ውጤታማ መሆን ችሏል፡፡

ከምንባቡ ውጪ

- ሰናይት ገመድ በመዘርጋት ልብሷን አሰጣች፡፡

ምሳሌ 2= በማሳደግ የሚለው ቃል በምንባቡ ውስጥ ያለው ፍቺ

- እያንዳንዱ ግለሰብ የከተማ ግብርናን በመጠቀም የቀን ገቢውን በማሳደግ ህይወቱን መቀየር ይችላል፡፡
- ሁሉም ማህበረሰብ ወላጅ አልባ ህጻናትን በማሳደግ ተግባር መሳተፍ አለበት፡፡

❖ ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ተጨማሪ ዓረፍተ ነገሮችን በመጻፍ ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
❖ በምርጫ መልክ የቀረበውን ጥያቄ በደብተራቸው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ የሰሩትን ተመልክተው ትክክለኛ መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡ የፈጸሙትን ስህተት ለይተው የማስተካከያ መልስ ይስጧቸው፡፡
❖ በግቢያቸው ወይም በአካባቢያቸው የሚካሄድ የግብርና ሥራ ካለ ምን አይነተ ግብርና እንደሆነ በመጥቀስ አመራረቱንና ያለውን ጠቀሜታ ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቀው በመምጣት በክፍል ውስጥ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ይግለጹላቸው፡፡
❖ የሰበሰቡትን መረጃ አለፍ አለፍ እያሉ የተማሪዎችን ስም በመጥራት በክፍል እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸው፡፡ ላከናወኑት ተግባር የማበረታቻ ቃል በመጠቀም ቀጣይ ልምምድ እንዲያደር ጉድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
❖ የክርክር ርዕሱን በማሳወቅ በተማሪዎች ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ቡድን ይመስርቱና ዳኛ በማስመረጥ በቀጣይ ለክርክር እንዲዘጋጁ ያስረዷቸው፡፡ በዝግጅት ጊዜና በአቀራረብ ጊዜ ምን ምን ተግባር ማከናወን እንዳለባቸው ይጠቁሟቸው፡፡
❖ በተዘጋጁበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ክርክሩን እንዲያካሂዱ ያመቻቹላቸው፡፡ ክርክሩ ሲጠናቀቅ ሲከታተሉ የቆዩትን ታዳሚ ተማሪዎች በክርክሩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ይጋብዟቸው፡፡ በማጠቃለያ የክርክሩን ጠንካራና ደካማ ጎን በማሳወቅ ለቀጣይ የክርክር ጊዜ አሻሽለው እንዲገኙ ያስገንዝቧቸው፡፡

❖ የቀረበውን የክርክር ዝግጅትና አቀራረብ መነሻ አድርገው የክርክር መመሪያ እንዲያዘጋጁ ያበረታቷቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሶስት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል እየመረጣችሁ በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ለ
2. ሀ
3. ሐ
4. ሀ
5. ለ
6. ሐ
7. ሀ
8. ሐ
9. ለ
10. መ

## ክፍል ሶስት ቃላት

### ቃላትን በመገጣጠም ትርጉም መስጠት

❖ በቃላት ትምህርት ሥር የቀረቡትን ተግባራት ከመጀመርዎ በፊት ቃላት ሲመሰረቱ የፊደላት አደራደር ስርዓት መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ያስረዷቸው፡፡ ቃላት ከአደራደር ስርዓት ውጪ ፍቺ መስጠት እንደማይችሉ ከታች የቀረበውን ምሳሌ በመጥቀስ ይግለጹላቸው፡፡

ምሳሌ = ከሆሄ አደራደር ስርዓት ውጪ የተዋቀሩ በስርዓት የተዋቀሩ

| | |
|---|---|
| ሀ. ገራነት | ነገራት |
| ለ. ምዝታ | ዝምታ |
| ሐ. ትከረበ | በረከት |
| መ. ራንችስሁ | ስራችሁ |

❖ መጽሐፍ ውስጥ ተዘበራርቀው የተደረደሩ ሆሄያትን አስተካክለው ፍቺ የሚሰጡ ቃላትን መመስረት እንዲለማመዱ ይግለጹላቸው። የመሰረቱትን ቃል እየወጡ ጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲጽፉ በማድረግ በጓደኞቻቸው እርማት እንዲሰጣጡ ያድርጉ።

❖ ከቀረበላቸው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላት ለይተው እንዲያወጡ በማድረግ ለቃላቱ ፍቺ በመስጠት በቃላቸው መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ።

❖ በተግባር ሶስት ስር ለቀረቡት ቃላት ይበልጥ በፍቺ የሚቀርበውን በመምረጥ በደብተራቸው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው። የሰጡትን መልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ ትክክለኝነታቸውን ይመዝኑ።

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

የሚከተሉትን ትርጉም የማይሰጡ ቃላት በምሳሌው መሰርት ትርጉም በሚሰጥ መንገድ አዋቅራችሁ ፃፉ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ዕውቀት | ሰ. ሳይታክት |
| ለ. የዶሮ ወጥ | ሸ. ፈተና |
| ሐ. ብርሃን | ቀ. መጽሐፍ |
| መ. ይመስሳል | በ. የተደራሲያን |
| ሠ. ለመቀጠል | ተ. ወንበር |
| ረ. አልማዝ | ቸ. ገፀባህርያት |

ተግባር ሁለት

ከዚህ በታች ባለው አንቀፅ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት አውጥታችሁ ትርጉማቸውን በቃላችሁ ተናገሩ።

- ይነቀንቃሉ
- ያወልቃሉ

- ይሰረስራሉ
- ያብላሉ
- ይቆርጣሉ
- እስካልተመነጠሩ
- አሜከላ
- መጎሹ

ተግባር ሶስት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ይሆናሉ ተብለው ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ይበልጥ የሚስማማቸውን ምረጡ፡፡

1. ሐ　　　5.ሀ
2. ለ　　　6.ሀ
3. ሀ　　　7.ሐ
4. መ

## ክፍል አራት　　ጽሕፈት

አመዛዛኝ ጽሑፍ

❖ መምህር በዚህ ክሂል ስር ተማሪዎቹ በተለያየ መንገድ አንቀጽ መጻፍ እንዲችሉ የተለያዩ መለማመጃ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያ የሀሳብ ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቀ ዓረፍተ ነገሮችን ቅደም ተከተል አስተካክለው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ የዓረፍተ ነገሮቹ የሀሳብ ቅደም ተከተል በትክክል መስራታቸውን የእያንዳንዱን ተማሪ ተመልክተው እርማት ይስጧቸው፡፡

❖ የሀሳብ ቅደም ተከተላቸው የተስተካከለውን ዓረፍተ ነገሮቹን አገጣጥመው አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አንቀጽ እንዲገነቡ ይግለጹላቸው፡፡

❖ የጻፉትን አንቀጽ ከጓደኞቻቸው ጋር በመለዋወጥ እንዲተራረሙ ያድርጉ ከጓደኞቻቸው የተሰጣቸውን አስተያየት መልሰው ራሳቸው እንዲገመግሙ ያድርጉና የመጨረሻውን የተስተካከለ አንቀጽ ለሁሉም ተማሪዎች ያንብቡላቸው

- ❖ በሁለተኛ ደረጃ ከቀረቡላቸው መንደርደሪያ አረፍተ ነገሮች አንዱን መርጠው አከራካሪ አንቀጽ እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

- ❖ ስለአከራካሪ አንቀጽ ምንነትና አገነባብ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻና ምሳሌ በደብተራቸው ያጽፏቸውና እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡ በተጨማሪ አጭር ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

ማስታወሻ፡

አመዛዛኝ (አከራካሪ አንቀፅ)

አመዛዛኝ ወይም አከራካሪ ፅሁፍ ብዙውን ጊዜ ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ተቃራኒ ሀሳቦችን በማንሳት አንዱ ከሌላው የሚለይበትን፣የሚመረጥበትን፣ የሚልቅበትንና የሚያንስበትን ወዘተ. በተጨባጭ ምክንያት በመዘርዘር አንባቢን ለማሳመን የሚሞከርበት የጽሑፍ አይነት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ አመዛዛኝ ጽሁፍ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ጉዳዮችን በማንሳት እያመዛዘኑ፣እያወዳደሩ ፣እያከራከሩ፣ የማቅረቢያ መንገድ ነው፡፡ አመዛዛኝ ጽሑፍ አሳማኝ በሆነ ምክንያት አንዱን በመደገፍ ሌላውን በመንቀፍ አንባቢን ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለማሳመን የሚቻልበት ነው፡፡ በንፅፅር የሚቀርቡ ነገሮችን በተለያየ አቅጣጫ እየመረመሩ አንድነትና ልዩነትን፣ጥቅምና ጉዳትን፣ ክፋትና ደግነትን እያወዳደሩ የማቅረቢያ መንገድ ነው፡፡

ምንጭ (አለም እሸቱ፣1999፣76))

ምሳሌ፡- የአከራካሪ አንቀጽ ምሳሌ

ፀጥታና ዝምታ በመዝገበ ቃላት ፍቻቸው ተተካኪ ቢሆኑም መጠነኛ ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል ይገመታል፡፡ ፀጥታ፣ሰላም የሰፈነበትን የአዕምሮ እረፍት ያመለክታል፡፡ ሁከትን ሳይሆን ውስጣዊ እርጋታን ስለሚጠቁም ስሜትን ያዝናናል፡፡ ፀጥታ አጭር ዕድሜ ያለው ብርቅዬ ስሜት ነው፡፡ ዝምታ ግን እፎይታን ላያሳይ ይችላል፡፡ በዝምታ ውስጥ የገዛ ራስ ጉርምርምታ ሊኖር ይችላል፡፡ ዝምታ የአንደበትን ስራ መፍታት እንጂ የህሊናን እረፍት ላያመለክት ይችላል፡፡ በዝምታ ውስጥ የአቅል መበታተንና የስሜት መዶልዶም ሊኖር ስለሚችል ሁለቱን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች አድርጎ መመልከቱ ያስቸግራል፡፡

ምንጭ (ሰለሞን ሐለፎም፣ 1997፣196)

❖ በመጨረሻም ተማሪዎቹ ከላይ በቀረበላቸው ተግባር ጽሕፈትን በተለማመዱት መሰረት አሁን ደግሞ በራሳቸው አከራካሪ ጽሑፍ ለመጻፍ የሚያስችላቸው ርዕስ እንዲመርጡና አከራካሪ በሆነ መንገድ አንቀጽ እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

❖ ጽፈው ያመጡትን አንቀጽ እንዲያነቡ በማድረግ የታለመውን የጽሑፍ ክሂል በትክክለል መሳካቱን ይገምግሙ፡፡

የጽሑፍ ተግባር ሲጠናቀቅ ተማሪዎቹ ባገኙት አጋጣሚ የጽሑፍ ክሂላቸውን ለማሻሻል ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ይግለጹላቸው፡፡

በናሙና የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች አስተካክላችሁ አንድ አንቀጽ አዋቅራችሁ ጻፉ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ሐ | 5. መ |
| 2. ሸ | 6. ለ |
| 3. ረ | 7. ሠ |
| 4. ሰ | 8. ሀ |

ክፍል አምስት ሰዋስው

## የጊዜ ግስ

❖ መምህር በዚህ ክፍል የቀረቡትን ተግባራት ከማሰራትዎ በፊት የቀረበውን ማስታወሻ ለተማሪዎቹ በደብተራቸው ያጽፏቸውና ያስነብቧቸው፡፡ ካነበቡ በኋላ በጥያቄና መልስ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

ማስታወሻ

የጊዜ አይነቶች

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የጊዜ አይነቶችን በሶስት ዋና ዋና መንገድ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም የአሁን ጊዜ፣ የሀላፊ ጊዜና የትንቢት (የወደፊት) ጊዜ ናቸው፡፡

ሀ. የአሁን ጊዜ:- የምንለው አንድ ድርጊት እየተከናወነ ወይም እየተፈፀመ ያለ እና ድርጊቱ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ለመግለፅ የሚያገለግል ነው፡፡

ለምሳሌ:- ልጁ ምሳውን እየበላ ነው፡፡

ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እየተጓዙ ነው፡፡

ለ. የሀላፊ ጊዜ:- ይህ የጊዜ አይነት አንድ ድርጊት ተከናውኖ ወይም ተሰርቶ ያለፈ መሆኑን ለመግለፅ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ:- ባለፈው አመት ለጉብኝት ሀዋሳ ሄደው ነበር፡፡

መምህሩ ትናንት ከባህርዳር ተመልሷል፡፡

ሐ. የትንቢት (የወደፊት) ጊዜ:- ይህ የጊዜ አይነት አንድ ነገር ወይም ድርጊት ወደ ፊት ሊሰራ ወይም ሊፈፀም መሆኑን አስቀድመን የምንተነብይበት መንገድ ነው፡፡

ምሳሌ:- መቅደስ በሚቀጥለው ወር ዘመዶቿን ለመጠየቅ ትሄዳለች፡፡

በተያዘው አመት ሞዴል አርሶ አደሮች ሊሸለሙ ነው፡፡

- በመቀጠል በተግባር አንድ ስር የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች የድርጊት ጊዜ ጽፈው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡ የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡ ስህተት ከፈጸሙ እርማት በመስጠት ማስተካከያ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡

- ከዚያም የአወቃቀር ስህተት የሚታይባቸው ዓረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡ ስህተቱን ፈልገው በማውጣት እንደገና አስተካክለው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

- ከዚህ በፊት ስለ ጊዜ ተውሳከ ግስ የተማሩትን በጥያቄና መልስ ክለሳ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠል በተግባር ሶስት የቀረቡትን የጊዜ ተውሳከ ግሶች ዓረፍተ ነገር ሰርተው እንዲያሳዩ ያስረዷቸው፡፡

- ❖ በመጨረሻም ደብተራቸውን በመሰብሰብ ያርሙላቸውና የፈጸሙት ስህተት ካለ የማስተካከያ መልስ ይስጧቸውና አስተካክለው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

- ❖ በተግባር አራት የቀረቡትን የጊዜ አመልካች ቃላት የአሁን፣ የሀላፊና የወደፊት በማለት ለይተው በሰንጠረዡ እንዲያሰፍሩ ያግዟቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

በተግባር አንድ

በሚከተሉትን ጥያቄዎች ውስጥ ያሉትን የጊዜ አይነቶች ለይታችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. የሀላፊ ጊዜ | መ. የወደፊት ጊዜ |
| ለ. የሀላፊ ጊዜ | ሠ. የወደፊት ጊዜ |
| ሐ. የአሁን ጊዜ | ረ. የሀላፊ ጊዜ |
| ሰ. የአሁን ጊዜ | ሸ. የወደፊት ጊዜ |

ተግባር ሁለት

የሚከተሉትን ሰዋስዋዊ ስህተት የሚታይባቸው ዓረፍተ ነገሮች አስተካክላችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ተማሪዎቹ የክፍል ተወካያቸውን መረጡ፡፡

ለ. ጎበዝ ተማሪዎችን ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

ሐ. ማንኛውም ሰው ድህነትን ለማስወገድ ታጥቆ መነሳት አለበት፡፡

መ. ሄለን በስነ ምግባሯ የተመሰገነች ናት፡፡

ሠ. ሁሉም ሰው የህጻናት ጉልበት ብዝበዛን መከላከል አለበት፡፡

ረ. ትምህርት በሳይንስና ቴክኖሎጂ መደገፍ አለበት፡፡

ሰ. ህብረተሰቡ አጥፊዎችን ለህግ ለማቅረብ መተባበር አለበት፡፤

ሸ. አረጋውያንን መንከባከብ ባህላችን ሊሆን ይገባል፡፡

ተግባር አራት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት የአሁን ጊዜ፣የሀላፊ ጊዜና የወደፊት ጊዜ በማላት በሰንጠረዥ ውስጥ መድቡ።

| የአሁን ጊዜ | የወደፊት ጊዜ | የሀላፊ ጊዜ |
|---|---|---|
| እየተማረ ነው | ያነባል | ሰጥቷል |
| እየሰራ ነው | ሰላም<br>ይሰፍናል | አንብቧል |
| እየመጣ ነው | ይሰጣል | ሰብሯል |
| እየሰጠ ነው | ይመጣል | ሰላም ሰፍኖ ነበር |
| ሰላም እየሰፈነ ነው | ይሰብራል | መጥቷል |
| እያነበበ ነው | | ተምሯል |

መርጃ መሳሪያ

የጊዜ አይነቶችን የሚያሳይ ቻርት

# ምዕራፍ አምስት (5)

## ቱሪዝም

ክፍለ ጊዜ 18

የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች:-

- ✓ ቃላትን በምዕላድ ይከፍላሉ
- ✓ ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ
- ✓ በአላፊ ግዜ አንቀፅ ይፅፋሉ
- ✓ ራስን የመገምገሚያ ስልቶችን ተጠቅመው ሥራቸውን ይመዝናሉ
- ✓ ድህረ ግንድ ቅጥያን ይጠቀማሉ

የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች:-

- ➢ አዳምጦ ምዕላዶችን መከፋፈል
- ➢ አንብቦ የፅሁፉን መልዕክት ማብራራት
- ➢ ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ
- ➢ አንቀፅ መፃፍ
- ➢ ድህረ ግንድ ቅጥያ

ክፍል አንድ ማዳመጥ

ሽርሽር በእንጦጦ

ቅድመ ማዳመጥ

የትምህርቱ አቀራረብ

- መምህር በመጀመሪያ ደረጃ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የምዕራፉ አላማዎች እንረዱ ያድርጉ፡፡
- ከዚያም በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ በጥንድ በጥንድ ሆነው እንዲወያዩና ሀሳባቸውን እንዲገልፁ በማበረታታት ለማዳመጥ ተግባሩ ዝግጁ እንዲሆኑ ያድርጓቸው፡፡ተማሪዎች የሚሰጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ምልሽ ተመልክተው ትክክለኛውን መልስ ከመናገርዎ በፊት የተማሪዎችን ምላሽ ያረጋግጡ፡፡
- ተማሪዎች በሰጡት ምላሽ መነሻነት የሚቀርብላቸው ምንባብ ‹‹ሽርሽር በእንጦጦ›› እንደሆነ በማስተዋወቅ በጥሞና እንዲያዳምጡ ያሳስቧቸው፡፡ ሲያዳምጡ አዳዲስ ቃላትን በደብተራቸው እንዲጽፉ ይግለጹላቸውና ምንባቡን በትክክል ያንብቡላቸው፡፡ ምንባቡን ሲያነቡ ትክክለኛውን የአነባበብ ስርዓት ተከትለው ያንብቡላቸው፡፡

ከአዲስ አበባ በስተሰሜን አቅጣጫ ከባህር ወለል በላይ 3200 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ከአንኮበር ወደ እንጦጦ ቤተ መንግስታቸውን ሲያዛውሩ ያለምክንያት አልነበረም፡፡ ስፍራው ለዘመቻም ሆነ ለአስተዳደር የተመቸ ነው፡፡እንጦጦ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ የተሸፈነ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል የተለያዩ የውስጥና የውጭ ጸሀፍት የአዲስ አበባ ሳንባ ነች ያሏት፡፡ ጥቅጥቅ ያለው ደን ትንፋሹን ቁልቁል ወደ ውቧ ሸገር እፍ ይልባታል፡፡ እናም በዚህ ሁኔታ የከተማችን ንፁህ አየር ምንጭ እንጦጦ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ከጥቅጥቅ ደኑ ጋር አብረው ለማደግ ግብግብ የሚያደርጉት የሳርና የአበባ ሽታ አካባቢውን ገነት አስመስለውት ይመለከታሉ፡፡

እንጦጦን ጫፍ ሆነን አዲስ አበባን ዘቅዝቀን ስትመለከታት ውበቷና ግርማ ሞገሷ ቀልብ ይስባል፡፡ ጎብኚዎች የእንጦጦን ተራራ ለመውጣት አቀበቱን ሲያያዙ እግረ መንገዳቸውን ሽሮ ሜዳን ያገኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ ሌለኛው በባህል አልባሳት የተንቆጠቆጠና አላፊ አግዳሚውን የሚስብ ሌላው የሰው ልጆች የኪነ- ጥበብ ውጤት የቱሪስት መዳረሻ ነው፡፡ ማራኪውን የጦጦ የቱሪስት ስፍራ ለመጎብኘት ጉዞ የጀመረ ሰው ሽሮ ሜዳን መርገጡ አይቀሬ ነው፡፡

1. እስካሁን ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ? ቀሪው የፅሁፍ ክፍል ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?

እንጦጦ አናት ላይ ለመውጣት  በአማካይ  አርባ አምስት ደቂቃ ያክል ይወስዳል፡፡ ከወጡ በኋላ በነፋሻው አየር ይማረካሉ፡፡ ጥቅጥቅ ደኑና የእዋፉ ዝማሬ ሽው ከሚለው ነፋስ ጋር ሲዳመር ተፈጥሮን እንድናደንቅ ያስገድደናል፡፡ ስፍራው ሁከትና ግርግር የሌለበት፣ፈጠራዊ የሆኑ የጥበብ ስራዎችን ለመጻፍ አዕምሮን የሚያነቃቃ ቦታ ነው፡ በስፖርቱ አለም የሀገራቸውን ስምና ዝና ከፍ የሚያደርጉ ብርቅዬ አትሌቶቻች የስልጠና ስፍራም ጭምር ነው፡፡

እንጦጦ አዲስ አበባን  ከዳር እስከዳር  ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡ እንጦጦ  ለጉብኝት ከተገኙ  የእንጦጦ ማሪያም ቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ገዳም፣ የዳግማዊ ምኒልክና የእቴጌ ጣይቱን ታሪክ አይተው ይመለሳሉ፡፡ በምኒሊክ ቤተ መንግስት ውስጥ  በንግስናቸው ወቅት ሲገለገሉባቸው የነበሩ ካባ፣ጫማ፣ የጠፍር አልጋ፣ አልባሳት፣ የተለያዩ የብራና መጽሐፍት ወዘተ ይገኛሉ፡፡ ሙዚየሙ የኢትዮጵያን ታሪክ በመጠኑም ቢሆን ጎብኝዎች አውቀው እንዲመለሱ ያደርጋል፡፡ ጎብኝዎች ጉብኝታቸውን አጠናቀው  ወዲያና ወዲህ ሲዘዋወሩ የአዲስ አበባን ጓዳ ጎድጓዳ  ቁልጭ አድረገው ይመለከታሉ፡፡ እንጦጦ ላይ የተደረገው ሽርሽር በጣም አስደሳች  ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ምንጭ (የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ 2007፡፡ ባህልና ቱሪዝም፡፡ ከገፅ 32-33 ለ6ኛ ክፍል ማስተማሪያ ተሻሽሎ የተወሰደ)

- የቀረበላቸውን ምንባብ ሲያዳምጡ የጻፏቸው አዳዲስ  ቃላት ካሉ ይጠይቋቸው፡፡ በራሳቸው ፍቺ ለመስጠት ሙከራ እንዲያደርጉ እድል ይስጧቸውና በትክክል መልስ   መስጠት መቻላውን   ያረጋግጡና የመለሱትንና የተሳሳጡትን እንዲያነፃጥሩ  ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም እርስዎ  ትክክለኛውን መልስ በመግለፅ እርማት ያድርጉ፡፡
- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ  የወጡትን የእውነት ሀሰት ጥያቄዎች በቃላቸው ያሰሯቸው፡፡ የሚሰጡትን ምላሽ በምክንያት እያስደገፉ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ከምንባቡ የወጡ ቃላትን በምዕላድ ነጣጥለው እንዲጽፉ ያግዟቸው፡
- በትክክል መልስ መስጠታቸውን ለማረጋገጥ  የቃል ጥያቄ በመጠየቅ  መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ በዚህም ያዳመጡትን ምንባብ መልእክት በትክክል መረዳት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- አዳምጠው ለቃላት አውዳዊ ፍች እንዲሰጡ የቀረበላቸውን ጥያቄ በትኩረት በቡድን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ የሰጡትን ምላሽ ከትክክለኛው ምላሽ ጋር በማስተያየት ጥሩ የመለሱትን በማበረታታት የተሳሳቱትን ደግሞ በቀጣይ የተሻለ ስራ መስራት እንደሚችሉ ያበረታቷቸው፡፡

- ❖ በመጨረሻም ለተጨማሪ ተግባር በቴሌቪዥንና ሬዲዮ ስለቱሪዝም የሚቀርብ መርሀ ግብር አዳምጠው መረጃ ሰብስበው በመምጣት በክፍል ውስጥ በቃል እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡ ያቀረቡትም ንግግር ከንግግር መመሪያ አንፃር በመገምገም በቀጣይ የተሻለ ንግግር እንዲያደርጉ መንገዶችን ይተቁሟቸው፡፡

ለናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሶስት

የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት በምዕላድ ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ተፈጥሮ--አዊ

ለ . መስህብ--ኦች

ሐ. ጎብኝ--ኦች--ኣችን

መ. ቅርስ--ኦች--ኣችን

ሠ. ችሎት--ኣቸው--ን

ረ. መንገድ--ኣቸው--ን

ክፍል ሁለት ንባብ

- ❖ መምህር በቅድመ ንባብ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ተወያይተው ሀሳባቸውን እንዲገልጹና በውይይቱ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያሳስቧቸው፡፡ የገለፁትን ሀሳብ ምርምረው ትክክለኛ ምላሽ የሰጡትን በማበረታታት ለተሳሳቱት እርምት በመስጠት ያስተካክሉ፡፡
- ❖ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው፣የአካል ጉዳተኞች፣ አይነ ስውራንና መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ሳይዘነጉ ተማሪዎች እርስ በእርስ እንዲተጋገዙ ያድርጉ፡፡
- ❖ ከቅድመ ንባብ ተግባር በኋላ ተማሪዎቹ በአንቀፅ በአንቀፅ ተከፋፍለው ድምፃቸውን ሳያሰሙ እንዲያነቡ እና ንባቡን በክንያትና ውጤት እያስተሳሰሩ እንዲያነቡ ያስረዷቸው፡፡ የንባብ ሂደታቸው የተሳካ እንዲሆን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በትክክል ዕንዲያጤኑ ያድርጉ፡፡ ይህ ስልት ሁሉም ተማሪ በንባቡ እንዲሳተፍ ያግዛል፡፡

❖ ንባባቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በምንባቡ ውስጥ ያጋጠማቸው አዳዲስ ቃል ካለ መምህራቸውን እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው፡፡

❖ የጠየቁት አዳዲስ ቃል ካለ እራሳቸው ተማሪዎቹ እርስ በእርስ እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡ በትክክል ካልተመለሰ ግን እርስዎ ተገቢውን ፍቺው ይግለፁላቸው፡፡

❖ ያነበቡትን ምንባብ ዋና ሀሳብ በቃል እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ በአንብቦ መረዳት ስር የቀረቡትን የምርጫ ጥያቄዎች በደብተራቸው ያሰሯቸው፡፡

❖ በምንባቡ መሰረት የቀረቡትን የእውነት ሀሰት ጥያቄዎች ደግሞ በቃል እንዲመልሱ ይግለፁላቸው፡፡

❖ የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት

ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በደብተራችሁ ፃፉ

| | |
|---|---|
| 1. መ | 5. መ |
| 2. ለ | 6. ለ |
| 3. ሐ | 7. ሐ |
| 4. መ | |

## ክፍል ሶስት ቃላት

## እምሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

❖ በቃላት ትምህርት የቀረበውን የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ማስታወሻ በደብተራቸው እንዲጽፉና እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡

❖ የቃል እማሬያዊ ፍቺ የቀጥታ ወይም የመዝገበ ቃላዊ ፍቺ እንደሆነና ፍካሬያዊ ፍቺ ደግሞ ከዕማሬያዊ ፍቺ ባሻገር ቃላት የሚኖራቸውን ሚስጥራዊ ወይም ስውር ፍቺ መሆኑን በጥያቄና መልስ በምሳሌ አስደግፈው ያስረዷቸው፡፡ በተለይም የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በዓረፍተ ነገር እያስገቡ እንዲሰሩ

ያግዟቸው፡፡

- ❖ ቀጥሎ በተግባር አንድና ሁለት ስር ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድረግ የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በትክክል መለየት መቻላቸውን ይመዝኑ፡፡
- ❖ በመጨረሻም በራሳቸው አምስት ቃላትን ፈልገው እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች ሰርተው እንዲያሳዩ ይግለፁላቸው፡፡ ከመጀመሪያው ሙከራ ያሳዩትን መሻሻል ተመልክተው እርስዎ አስፈላጊውን እገዛ ያድርጉ፡፡

ለናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት በተሰጠው ምሳሌ መሰረት እማሬያዊ ፍቻቸውን በደብተራችሁ ጽፋችሁ ለመምህራቸውሁ አሳዩ፡፡

ሀ. የአዕዋፍ ዝርያ

ለ. የሚያጣብቅ ፈሳሽ

ሐ. የበርበሬ ዝርያ

መ. በመሬት ውስጥ የሚኖሩ ነፍሳት

ሠ. ማር የምትሰራ ነፍሳት

ረ. የፍራፍሬ አይነት

ሰ. ተንቀሳቃሽ አየር

ሸ. የረጋ ወተት

ተግባር ሁለት

የሚከተሉትን ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ፍካሬያዊ ፍቺ በመስጠት በደብተራችሁ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ፈጣን

ለ. ቀልጣፋ

ሐ. ወሬ የማይቋጥር

መ. ውብ ፣ ሸጋ

ሠ. በጭፍን የሚሄድ

ረ. የማይንቀሳቀስ

## ክፍል አራት ጽሕፈት

### በሃላፊ ጊዜ አንቀፅ መፃፍ

❖ መምህር በተማሪው መፅሀፍ በሃላፊ ጊዜ የቀረበውን አንቀፅ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ካነበቡ በኋላ የሃላፊ ጊዜ ጽሁፍ ምን እንደሆነ ያነበቡትን ጽሁፍ በምሳሌነት በመጥቀስ የአንድ ድረጊት በጊዜ ቅደም ተከተል ትረካ መሆኑን ያስረዷቸው፡፡

❖ ከዚያም በዚሁ መሰረት ባለፈው ሳምንት ያከናወኑትን ተግባር በሀላፊ ጊዜ ጽሁፍ እንዲያመጡ ይግለፁላቸው፡፡

❖ ጽፈው ያመጡትን በየተራ እያቀርቡ እራሳቸውን እንዲገመግሙ ያድረጉ፡፡

❖ በዚህም ጥንካሬና ድክመታቸውን እንዲለዩ ያሳስቧቸው፡፡ በመጨረሻም ያጋጠማቸውን ችግር፣የታየባቸውን ድክመት የሚያሻሽሉበትን ስልት ይጠቁሟቸው፡፡

❖ በመጨረሻም በተሰጣቸው ኃይለ ቃል መነሻነት አንቀጽ ጽፈው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡ ጽፈው የመጡትን ከጓደኞቻቸው ጋር በመቀያየር እንዲያነቡና ያገኙትን ጠንካራና ድክመት እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም የመጨረሻውን ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

## ክፍል አምስት ሰዋሰው

### ድህረ ግንድ ቅጥያ

❖ በዚህ ክፍል የቀረቡትን ተግባራት ለማከናወን በምዕራፍ አንድና ሁለት ላይ ስለምዕላድ የተማሩትን ያስታውሷቸው፡፡ ከዚያም በቀረበላቸው ምሳሌ መሰረት የቀረቡትን ቃላት ዋና ቃሉን ከድህረ ምዕላድ ጋር እንዲያጣምሩና ከዋና ቃሉ ቅድመ አምድ ቅጥያውን ለይተው እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡

❖ የሰጡት ምላሽ ትክክል መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድርግ ይገምግሙ፡፡

❖ በዚያም ትክክለኛ መልስ ላልሰጡት ትክከለኛውን መልስ በመግለፅ እንዲያስተካክሉ

ያግዟቸው፡፡

- ❖ ከዚህ በታች የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን የቅጥያ ተግባራት ለተማሪዎቹ ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡ ለተማሪዎቹ ማስታወሻ በሚሰጡበት ወቅት ሁሉም ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ ማስታወሻውን እየፃፉ መሆናቸውን ይከታተሏቸው፡፡
- ❖ ማስታወሻውን አፅፈው እንደጨረሱ የተወሰነ ደቂቃ ተማሪዎቹ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በጥንድ በጥንድ ሆነው እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ እርሰዎም ተማሪዎች በሚወያዩበት ወቅት በትክክል እየተወያዩ ስለመሆናቸው እያንዳንዱን ተማሪ እየተዟዟሩ በማየት ያረጋግጡ፡፡
- ❖ በመቀጠልም ተማሪዎቹ የተወያዩበትን ሀሳብ በየተራ እየወጡ ፅብረቃ እንዲያደርጉ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ሁሉም ተማሪዎች ፅብረቃ ማድረጋቸውን ካረጋገጡ በኋላ እርስዎ የማጠቃለያ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡
- ❖ ከላይ በቀረበው ማስታወሻ መሰረት ተማሪዎቹ ርዕሰ ጉዳዩን በትክክል መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሁለት ተግባራት የክፍል ስራ ይስጧቸውና እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎቹ ሰርተው እንደጨረሱ በትክክል መስራት አለመስራታቸውን በእርማት ያረጋግጡ፡፡ በትክክል የሰሩትን ተማሪዎች በማበረታታት በትክክል ያልሰሩ ተማሪዎች ካሉ ትክክለኛውነ መልስ እርስዎ ይንገሯቸው፡፡

ሀ.በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚታዩትን መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች ለይተው ያመልክቱ፡፡

1. በቤታቸው
2. ለልጆቻቸው
3. እንደመጣች
4. ስለጠራኝ
5. ከየስራቸው

ለ. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የገቡትን ቅጥያዎች የእርባታ ወይም የምስረታ በማለት ለይተው ያመልክቱ፡፡

1. በሰውነቴ
2. መንገደኛ
3. ወላጆቹ
4. ኮረብታማ
5. ቀልደኛ

የተግባሮቹ መልሶች

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. በ-ቤት -ኣቸው | 1. የእርባታ |
| 2. ለ-ልጅ-ኦች-ኣቸው | 2. መስራች |
| 3. እንደ-መጣ-ች | 3. የእርባታ |
| 4. ስለ-ጠራ-ኝ | 4. መስራች |
| 5. ከ-የ-ሰራ-ኣቸው | 5. መስራች |

የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች

ቅጥያዎች በቃል ላይ ሲታከሉ የተለያየ ሙያ ይኖራቸዋል፡፡ ይህንን ሙያቸውን መሰረት በማድረግ የእርባታ ቅጥያ እና መስራች ቅጥያ በሚል ተለይተው ይታወቃሉ፡፡

ሀ. የእርባታ ቅጥያዎች፡-

የእርባታ ቅጥያዎች በአንድ ቃል ተደርበው የሚገቡ ናቸው፡፡ እነዚህ ቅጥያዎች በቃሉ ላይ ሲታከሉ የቃሉን ሰዋስዋዊ ክፍል አይለዉጡም ወይም ቃሉን ወደ ሌላ የቃል ክፍልነት አይቀይሩትም፡፡

ምሳሌ፡- በር- ኦች- በሮች ልብስ-ኦች-ልብሶች

በር-ኤ- በሬ ልብስ-ኤ--ልብሴ

በር-ኣችሁ- በራችሁ ልብስ-ኣችሁ-ልብሳችሁ

ከፍ ሲል በቀረበው ምሳሌ ላይ ታክለው የሚታዩት ቅጥያዎች የእርባታ ቅጥያዎች ናቸው፡፡ የእርባታ ቅጥያዎች ናቸው የሚባለውም በር ወይም ልብስ የሚሉትን ቃላት ሰዋስዋዊ ክፍል ባለመለወጣቸው ነው፡፡ ቅጥያዎቹ በመታከላቸው ምክንያት ስም የነበሩት በር እና ልብስ የሚሉት ቃላት ወደ ሌላ ሰዋስዋዊ ክፍል አልተቀየሩም፡፡

ለ. የምስረታ ቅጥያዎች፡-

መስራች ቅጥያዎች እንደ የእርባታ ቅጥያ ሁሉ በአንድ ቃል ላይ ተጠግተው የሚገቡ ናቸው፡፡ እነዚህ ቅጥያዎች ግን በቃሉ ላይ ሲታከሉ የቃሉን ሰዋስዋዊ ክፍል ይለውጣሉ፡

ምሳሌ፡- ሀይል- ኛ- ሀይለኛ

ሀብት- ኣም -ሃብታም

ተራራ-አማ- ተራራማ

ጉልበት-ኛ- ጉልበተኛ

ከፍ ሲል በቀረበው ምሳሌ ላይ ታክለው የሚታዩት ቅጥያዎች የምስረታ ቅጥያዎች ናቸው፡፡ መስራች ቅጥያዎች ናቸው የሚባለውም የቀላቱን ሰዋስዋዊ ክፍል ከስምነት ወደ ቅፅልነት በመለወጣቸው ነው፡፡ ከምሳሌው መረዳት እንደሚቻላው ቅጥያዎቹ በመታከላቸው ምክንያት ስም ነበሩት ጉልበት፣ሀይል፣ሀብትና ተራራ የሚሉት ቃላት ወደ ሌላ ሰዋስዋዊ ክፍል ማለትም ከስምነት ወደ ቅፅልነት ተቀይረዋል፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት ላይ ምሳሌውን መሰት በማድረግ በዋና ቃሉ ላይ ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን አጣምራችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ደብተራችሁ

ለ. ገበሬዎች

ሐ. መከራት

መ. ተከሰተች

ሠ. መምህሮች

ረ. ትምህርታችሁ

ሰ. መጽሐፉን

ሸ. ንብረታቸውን

ተግባር ሁለት

ከሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ቅድመ ግንድ ቅጥያዎችን በመነጠል በደብተራችሁ ፃፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. እንደ - ወረደ

ለ. ስለ - ፍቅር

ሐ. የ - መቅደስ

መ. የነ - ጀማል

ሠ. ወደ - መስኮት

ረ. በ - ህብረተሰብ

ሰ. ከ - አዲስ አበባ

ሸ. አስ - ገሳ

መርጃ መሳሪያ

የቅድመ አምድና ድህረ አምድ ቅጥያዎችን የሚያሳይ የተዘጋጀ ቻርት

# ምዕራፍ ስድስት (6)

## ጸረ-አደንዛዥ እጾች

**ክፍለ ጊዜ 18**

የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች:-

- ✓ ተገቢውን የአነባበብ ስልት ተከትለው ያነባሉ፡፡
- ✓ መረጃ ሰጪ ፅሁፎችን ይለያሉ፡፡
- ✓ አአዳዲስ ቃላትን  ከአገባቡ በመነሳት ይገምታሉ፡፡
- ✓ አንድን ሀሳብ ለመግለጽ መሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡

የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች:-

- ➢ ምንባቡን መሰረት ያደረገ ውይይት
- ➢ የፅሁፍና የግል ህይወት ተዛምዶ
- ➢ የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ
- ➢ አንቀፆችን ማጠናቀቅ
- ➢ ስም፣ተውላጠ ስምና ግስን በዓረፍ ተነገር ውስጥ መተቀም

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

‹‹ሰካራሙ ተበጄ››

### የትምህርቱ አቀራረብ

- ❖ መምህር ተማሪዎቹ የምዕራፉን ዓላማዎች አንብበው እንዲረዱ ያድርጉ፡፡
- ❖ በዚህ ምዕራፍ ለማዳመጥ የቀረበውን ‹‹ሰካራሙ ተበጄ›› የሚለውን ታሪክ ከማንበብዎ በፊት ከምንባቡ ለወጡ ቁልፍ ቃላት በቃላቸው ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የሚያነቡላቸውን ምንባብ ርዕስ አስተዋውቀው በጥሞና በማዳመጥ ጥያቄዎችን ለመስራት እንዲዘጋጁ ያሳስቧቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎቹ ለማዳመጥ መዘጋጀታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ምንባቡን ስልቱን ጠብቀው ያንብቡላቸው፡፡

በጉለሌ የነበረው የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማነው ብለው ከገፈርሳ እስከ ደጃዝማች ይገዙ ሰፈር ለጠየቀ ‹‹ሰካራሙ ተበጄ! ዶሮ ነጋዴው ተበጄ ነው!›› ብለው ይነግሯቸዋል፡፡ የህይወት ታሪኩ ፍፁም ገድል ነው፡፡ የራሱን ፀጉር ውሃና መቀስ ነክቶት አያውቅም፡፡ ከጠርሙስ ጋር ካልተገናኘ አይኑ አይገለጥም፤ሰውንም አያናግርም፡፡ በጠርሙስ የሞላውን ከጠጣ በኋላ ሲራገም ወይም ሲሳደብ ሲፎክርና ሲያቅራራ ድምፁ ከፈረንጅ ውሻ ድምጽ ይወፍራል፡፡ቢያውቅም ባያውቅም ካገኘው ጋር ሁሉ ይስቃል፣ይንከተከታል፣ መልሶ ይተክዛል፣ መልሶ ይስቃል፡፡

ቡና በተፈላ ጊዜ በጉለሌ በየምድጃው ስር የሰካራም ተረት የተጫወተው ሰው ሁሉ የተናገረው በሰካራሙ ተበጄ ላይ ነው፡፡ መልኩን አይተው የማያውቁት ባልቴቶች እንኳን ቡናውን ፉት እያሉ የሌሎቹን ስካር ፌዝና ተረት በተበጄ ላይ ነው የሚያላክኩበት፡፡ ከሚያሰክር ሁሉ ለመራቅ ብዙ ጊዜ ሞክሮ ነበር፡፡አድሮ ቃሪያ እንዳሉት አበው ከድጡ ወደ ማጡ ሆነበትና ሰክሮ ያላደረበት ሌሊት አልፎ ብርሃን በሆነ ጊዜ‹‹ከእንግዲህ መጠጥ በዞረበት አልሄድም››እያለ በየቀኑ ምሏል፡፡ የመጠጥ ጠርሙችን ከቤት አውጥቶ የማንም መሳለቂያ አልሆንም ብሎ ጥሏቸዋል፤ መልሶ ሰብሸቧቸዋል፡፡ እሱ አጠገብ የተኛ እንቅልፍ አያይም፡፡ ጠርሙሱን ከከፈተ በኋላ ብርጭቆ ያስፈልገው እንደነበር ትዝ አለው፡፡ ሶስት የሚሆን ደህና ጉንጭ ጠርሙሱን ከአፉ አስጠግቶ ጨለጠው፡፡ብርጭቆ ሊያመጣ ሲያስበው ግማሹን ያክለ ሰርጉጄዋለሁ አለና ከት ብሎ ሳቀ፡፡ የጠርሙሱ መጠጥ እስኪያልቅ ከዛፉ ስር ተቀምጦ ትንባሆውን በላዩ በላዩ ላይ ይለዋል፡፡

ይህን መጠጥና ትንባሆ ህን ካልተውህ ላንተ ንስሃ አባት አልሆንህም›› ብለው የመጀመሪያ የንስሃ አባቱ ብዙ ከመከሩት በኋላ መንፈሳዊ ልጅነቱን ከርግማት ጋር አስወግደውታል፡፡

ሰራተኞቹ ለእርሱ ተቀጥሮ መስራትን ከውርደት ቆጥረውት እያዋረዱት ሄደዋል፡፡ ‹‹መጠጥ ካልተውክ አናገባህም›› ብለው በየጊዜው ጋብቻ ጠይቋቸው የነበሩ ሴቶች ሁሉ በቁመናው አሰናብተውታል፡፡ በሰንበቴም፣ በማህበርም፣ ማህበርተኛ ለመሆን የጠየቃቸው ነፍሱን ሳይቀር ንቀዋታል፡፡ በጉለሌ መንደር ብዙ ጊዜ ሰክሮ አውቶሞቢል ሂዶበታል፡፡ ሰክሮ ሲነጋ እራሱን እስር ቤት ውስጥ አግኝቶታል፡፡ መንገድ ዳር ባሉት በብዙ የውሃ ጉድጓዶች ሰክሮ ገብቶ የጉለሌ ህዝብ አውጥቶታል፡፡ ሰክሮ ከቤት መድረስ እያቃተው ከወደቀበት ባቡር መንገድ ሳይነሳ ብዙ ጊዜ በላዩ ላይ ጎርፍ ሄድበት አድሯል፡፡

ሰዎች መልካም የሰማዕትነት ስራውን ሁሉ ርካሽ አድርገው ይቆጥሩበታል፡፡ በግብረገብ መሰረት አደረኩት ያለውን ሁሉ በስካር እንዳደረገው ያናንቁበታል፡፡‹‹በጎ ስራውን ሁሉ በትኩስ መቃብር ውስጥ አፈር አለበሰው፤አንተ ሰው ሰውሁን፣ ሚስት አግባ፣ ልጆች ይኑርህ›› ይሉና ይዘልፉት ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ውርደትና ርክሰት ነው እንጅ ክብር አይደለም፡፡ በአደንዛዥ እፅ የደነዘዘ ሰው ለምንም አይሆንም፡፡ ሁሌም መጥፎ ሱስ ያለበት ሰው ከሰው በታች ነው፡፡ ሰዎች ይሸሹታል፤ ፍጹም ወዳጅነትና ዝምድናውን አይሹም፡፡ቁም ነገር ቢኖረውም ከሰው አይቆጠርም፡፡ እናም ኑሮው በጨለማ እንደተከበበ፣ ህይወቱ የተመሰቃቀለ፣ ኑሮው የደበዘዘ ይሆናል፡፡

ምንጭ ዘሪሁን አስፋው፣1995፣ከገፅ115-121 ከተመስጌን ገብሬ አጭር ልቦለድ ቀንጭቦ የወሰደውን ታሪክ ለ6ኛ ክፍል ለማስተማር ተሸሽሎ የተወሰደ)፡፡

- ❖ ታሪኩ ተደግሞ እንዲነበብላቸው ፍላጎት እንዳላቸው ይጠይቁና ደግመው ያንብቡላቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም በአዳምጦ መረዳት ስር ያሉትን ጥያቄዎች በወንበር እንዲወያዩ ይግለፁላቸው፡፡ በውይይቱም ያገኙትን ሀሳብ ተማሪዎቹን በስም እየጠሩ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም የምንባቡን መልዕክት ከራሳቸው ህይዎት ጋር እያገኛኙ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ የለቱን ትምህርት ለማጠቃለል ያህል ተማሪዎቹ በሰጡት መልስ ላይ ተመርኩዘው የጥያቄዎቹን የማጠቃለያ መልስ ይግለፁላቸው፡፡

በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሶስት

የሚከተሉትን ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰርት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. የማይለወጥ፣የማይሻሻል፣ከስህተቱ የማይመለስ

ለ. ከችግር ወደ ባሰ ችግር

ሐ. አጋምሸዋለሁ፣ ብዙውን ጠጥቸዋለሁ

መ. አንድ አቋምና ተመሳሳይ አላማ ያላቸው ሰዎች የሚመሰርቱት ድርጅት

ሠ. ምግባረ መልካም፣ ምግባሩ የቀና፣ እውነታኛ

ረ. በግልፅ የማይታይ፣የፈዘዘ

ሰ. ያልተስተካከለ፣የተዘበራረቀ፣ በስርዓቱ ያልተቀመጠ

ሸ. ማሾፊያ፣መቀለጃ

ክፍል ሁለት ንባብ

❖ በቅድሚያ የንባቡን ርዕስ በሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡ በማዳመጥ ክፍለ ጊዜ አዳምጠውት የነበረውን ታሪክ እንዲያስታውሱ በጥያቄ ያነቃቋቸው፡፡ የእለቱን ርዕስ ካዳመጡት ምንባብ ርዕስ ጋር እያዛመዱ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ያበረታቷቸው፡፡ ይህ ተግባር የተማሪዎችን ህሌና ለመሰብሰብ ይረዳል፡፡

❖ በማስከተል የቅድመ ንባብ ጥያቄን በቃላቸው ያሰሯቸው፡፡ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹን ከሰሩ በኋላ ተገቢውን የአነባበብ ስልት ተጠቅመው ምንባቡን እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡ ንባባቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የሚጠይቁት አዳዲስ ቃል ካለ ይጠይቋቸው፡፡ ለጠየቁት አዲስ ቃል በራሳቸው መልሱን እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡ መመለስ ካልቻሉ ግን እርስዎ ያስረዷቸው፡፡

❖ ከዚም የቀረበውን የእውነት ሐሰት ጥያቄ በቃል ያሰሯቸው፡፡ በተግባር ሁለት ስር በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ በደብተራቸው እንዲሰሩ ይግለጹላቸው፡፡ በአዛምድ መልክ የቀረቡትን ቃላት በፍቺ የሚመሳሰሉትን እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡

ለናሙና ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሶስት

በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ጉዳት
2. ያልጠነከረ ግንኙነት
3. ጥሩ ያልሆነ
4. ጦስ፣ችግር
5. መቅጠን፣መኮስመን፣ማነስ
6. ውስብስብ

## ክፍል ሶስት ቃላት

### የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

- በምዕራፍ አምስት ውስጥ የተማሩትን የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በጥያቄና መልስ ይከልሱላቸው፡፡ ከዚያም በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነበር እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድረግ ትክክለኛ መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡ የተሳሳቱት ጥያቄ ካለ ትክክለኛ መልስ በመንገር አስተካክለው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- በመቀጠልም ለቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ፣ ፍቺ በትክክል መስጠት መቻላቸውን ይመዝኑ፡፡ ከዚያም በዓረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው አዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ጽፈው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡

## ክፍል አራት ጽሕፈት

### ማስታወሻ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት

ከዚህ ስር ያለውን ማስታወሻ በደብተራቸው በማጻፍ ያስረዷቸው፡፡

አያያዥ ወይም የመሸጋገሪያ ቃላት ዓረፍተ ነገሮች እርስ በእርስ ተቀናጅተውና ተዋህደው እንዲቀርቡ የሚያግዙ ቃላትና ሀረጋት ናቸው፡፡ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር፣ አንቀፅን ከአንቀፅ በማያያዝ የምናነሳው ሀሳብ ፍሰቱን በጠበቀ መልኩ እንዲተላለፍ ያደርጋሉ፡፡ እያንዳንዳቸው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት የራሳቸው ቦታና አገልግሎት አላቸው፡፡ በመሆኑም አንዱ በገባበት ቦታ ሌላው ቢገባ አረፍተ ነገሩ ሊዛባና ሀሳቡ ሊፋለስ ይችላል፡፡

ምሳሌ፡-ስለዚህ

ነገር ግን

ሀ. በደንብ አጥንቻለሁ፤---------------ጥሩ ውጤት አመጣለሁ፡፡

ለ. ቡና ሲፈላ ደስ ይለኛል፤------------ስጠጣ አይስማማኝም፡፡

በምሳሌ ሀ ስር በቀረበው ዓረፍተ ነገር ውስጥ መግባት ያለበት አያያዥ ቃል ‹‹ስለዚህ›› ነው፡፡ በሱ ቦታ ላይ ነገር ግን የሚለውን ብናስገባ ሀሳቡ የተዛባ ይሆናል፡፡ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም አገልግሎታቸው በርካታ ነው፡፡ አያያዥ ቃላት ከሚባሉት ውስጥ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እንመልከት፡፡

| | |
|---|---|
| ምክንያቱም | በእንዲህ እንዳለ |
| አለበለዚያ | በተመሳሳይ |
| በአንፃሩ | እንጂ |
| ቀጥሎም | በዚህ ሳቢያ |
| እንደገና | ያም ሆነ ይህ |
| ነገር ግን ይልቅ | ስለዚህ |
| ዳሩ ግን | ምንም እንኳ |

በመጨረሻም

❖ መምህር ከቀረበው ፅሁፍ ውስጥ አያያዥ ቃላትን ለይተው በደብተራቸው እንዲጽፉ ያደርጉ፡፡ ከዚያም በቀረበው ያልተሟላ አንቀጽ ውስጥ በክፍት ቦታው ተገቢውን አያያዥ ቃል በመጠቀም እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡ እያንዳንዱን ተማሪ በስም እየጠሩ የሰሩትን እንዲያነቡ ያድርጉና በትክክል መልስ መስጠታቸውን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ በሰጡት ምላሽ ላይ ስህተት ካለ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

❖ በዚህ ክፍል ተማሪዎቹ ያልተጠናቀቁ እንቀፆች አሟልተው እንዲጽፉ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ የቀረበውን አንቀጽ ሀሳቡን እስኪረዱት ደጋግመው እንዲያነቡ ያስረዷቸው፡፡ ካነበቡ በኋላ አንቀጹን ሊያሟላ የሚች ሀሳብ በማስገባት አሟልተው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ አሟልተው የጻፉትን አንቀጽ አንብበው የትኛው መረጃ ሰጪ ጽሁፍ እንደሆነ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

ለናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

## ተግባር አንድ

የሚከተሉትን ተጀምረው ያልተጠናቀቁ አንቀጾች አሟልታችሁ በደብተራችሁ ፃፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ልጅቱ ልቅም ያች ቆንጆ ናት፡፡ ጫማ የላትም ነገር ግን እግሯ እንሶስላ የሞቀች ይመስላል፡፡ ፀጉሯ ሽቶና ዘይት ነክቶት አያውቅም፤ በሳሙና ለመታጠብ እንኳን እድል አላገኘም፤ሆኖም እየተዘናፈለ ወርዶ የተከበረውን ትከሻዋን አጥለቅልቆታል፡፡ መዘናፈሉም መልሰው መላልሰው ያጠፉት ይመስላል፡፡ አይኖቿ ኩል አያውቁም ነገር ግን እንደንጋት ኮከብ ያበራሉ፡፡ ጥርሶቿም ብርሃን ያስተጋባሉ፤የሚፋቁትም አልፎ አልፎ ነው፡፡ ጥፍሮቿ ቀለም አላዩም፤ሆኖም ውበታቸው እፁብ ድንቅ ነው፡፡ድህነትና ውበት በአንድ አካል ላይ እንደዚህ ያለ ፍፁም ህብረት ሲኖራቸው በፀዳል ላይ ብቻ ማየቴ ነው፡፡

ምንጭ (ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፣2008 ገፅ307)

ለ. የሾላ ወተት ፋብሪካ የሚሸጠው ወተት ህዝብ ዘንድ ከመድረሱ በፊት ብዙ ሂደቶችን ማለፍ አለበት፡፡ በመጀመሪያ ወተቱ በፋብሪካው ውስጥ ካሉ ላሞችና በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ካሉ ገበሬዎች ይገዛል፡፡ ይህ የተገዛ ወተት በትላልቅ የብረት ጋኖች ተሞልቶ በተሽከርካሪ ተጭኖ ፋብሪካው ዘንድ ይደርሳል፡፡ ፋብሪካው ተቀብሎ እየመዘነ ወደ ማፍያ ጋን ውስጥ ይገለብጣል፡፡ ጋኑ ወተቱን በ100 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ያፈላና ወደ ሁለተኛው ማሽን በትላልቅ ቱቦ ያስተላልፈዋል፡፡ ሁለተኛው ማሽን በ22 ዲግሪ

ሴንቲ ግሬድ እንደገና ያፈላና ወተቱ ውስጥ ያለውን ክሬም ይለያል፡፡ ክሬሙም ወደ ሌላ ማሽን ሲሄድ ወተቱ ወደ መጨረሻው ማሽን ይላካል፡፡ የመጨረሻው ማሽን ወተቱን ያቀዘቅዝና በቧንቧ አማካኝነት በጠርሙስና በላስቲክ እየለካ ይሞላና ይተሸጋል፡፡ ከዚያም በጉልበት ሰራተኞች አማካኝነት በሳጥን ውስጥ እየተደረገ ተቆጥሮ መኪና ላይ ይጫናል፡፡ በመጨረሻም ለነጋዴዎች ይሰጥና ለገበያ ቀርቦ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ምንጭ (ደረጀ ገብሬ፣1996 ገፅ164)

ተግባር አራት

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አያያዥ ቃላት ቀጥሎ በቀረበው ባዶ ቦታ ውስጥ በማስገባት አንቀፁ የተስተካከለ የሀሳብ ፍሰት እንዲኖረው አድርጉ፡፡

1. ያለምክንያት
2. እና
3. ይሆን ዘንድ
4. ነገር ግን
5. ቢሆንም
6. እርግጥ ነው
7. ስለዚህ

ክፍል አምስት ሰዋሰው

ተውላጠ ስም

❖ በምዕራፍ አንድና ሁለት ስለተጸውዖ እና የወል ስም ተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠል ተውላጠ ስም ስምን ተክቶ እየገባ የሚያገለግል መሆኑን በምሳሌ በማስደገፍ ያስረዷቸው፡፡

❖ ግስ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ድርጊት አመልካች መሆኑን በዓረፍተ ነገር ውስጥ እያስገቡ ምሳሌ በመስጠት ይግለጹላቸው፡፡ በመቀጠል ተቀላቅለው የቀረቡትን ስምና ተውላጠ ስሞች ለይተው በሰንጠረዥ ውስጥ እንዲያሰፍሩ፣ ከዚያም በባዶ ቦታው ውስጥ ተውላጠ ስሞችን በማስገባት ዓረፍተ ነገሮችን አሟልተው እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡

❖ በመጨረሻም የቀረቡላቸውን ግሶች በዓረፍተ ነገር ውስጥ አስገብተው እንዲጠቀሙ ያድርጓቸው፡፡

❖ የሰጡትን መልስ እንዲናገሩ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሶስት

ተስማሚ ታውላጠ ስሞችን በክፍት ቦታው በማስገባት ዓ.\ነገሩን አሟሉ።

ሀ. እሱ እና እሷ

ለ. እሷ

ሐ. እሱ

መ. እነሱ

ሠ. እኔ

ረ. አንተ

ሰ. እናንተ

መርጃ መሳሪያ

ስምና  ተውላጠ ስምን ጎን ለጎን የሚያሳይ የተዘጋጀ ቻርት

# ምዕራፍ ሰባት (7)

## የጥላቻ ንግግር

ክፍለ ጊዜ 18

የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች፡-

- ✓ መስማማትና አለመስማማትን የሚገልፁ ሀሳቦችን ያቀርባሉ
- ✓ ምንባቡን በማንበብ የጥላቻ ንግግር እንዴት እንደሚወገድ ይገልፃሉ
- ✓ ቅፅሎችን በመለየት ይጠቀማሉ
- ✓ የጥላቻ ንግግርን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ይገልፃሉ
- ✓ (እና)ን እና ነገር ግንን ተጠቅመው ነጠላና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች

- ➢ ማዳመጥና ማንፀባረቅ
- ➢ ማንበብና ማፍለቅ
- ➢ የቃላት አውዳዊ ፍቺ
- ➢ ቅፅሎች

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

‹‹የጥላቻ ንግግር የሚያስከትለው ጉዳት ››

የትምህርቱ አቀራረብ

- ❖ መምህር በዚህ ምዕራፍ ስር የቀረቡት ምንባቦች ተማሪዎቹን ከአላስፈላጊ ድርጊቶች ለመጠበቅና የሐሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ተረድተው ከዚህ ተግባር እንዲቆጠቡ በማሰብ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ የእርስዎ ሚና ከፍተኛ መሆኑን አይዘንጉ፡፡ ከቀረቡት ይዘቶች ባሻገር የስነ ምግባር ጉዳይ ይቃኝበታል፡፡ ተማሪዎች ለእያንዳንዱ ነገር ትኩረትና ጥንቃቄ የተሞላ የህይወት ክህሎት ለራስም ሆነ ለሀገር ጠቃሚ መሆኑን ተረድተው እንዲያልፉ ጥረት ማድረግ ይጠበቃል፡፡በተጨማሪም አንዳንድ ውይይቶች ገደብ የለሽ ሆነው ያሉበትን ሰላማዊ ሁኔታ እንዳይበርዘው የውይይቱ ዳራ የተገደበ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡

- ❖ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፡፡ የተወያዩበትን ሀሳብ ከየቡድኑ ተማሪ በመወከል እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በሰጡት ሀሳብ ተጨማሪ ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡ ይህ ደግሞ ቀጥሎ ለሚቀርብላቸው ምንባብ ትኩረት ሰጥተው እንዲያዳምጡ ያነሳሳቸዋል፡፡

- ❖ ተማሪዎቹ ለማዳመጥ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጡና ምንባቡን በዝግታ ያንብቡላቸው፡፡ ንባቡን ገታ አድርገው በማዳመጥ ጊዜ የቀረቡትን ጥያቄዎች ያንብቡላቸውና መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ በዚህ እስካሁን ተማሪዎቹ ምን ያህል በትኩረት እንዳዳመጡ ይገንዘቡበት፡፡ ከዚያም ንባብዎን ይቀጥሉ፡፡

ሩዋንዳ በመካከለኛው አፍሪካ እንደጌጥ ጣል የተደረገች ትንሽ ሀገርነች፡፡ በጣም ማራኪ ውበት ስላላት፣ በለምለም ሸንተረሮቿ፣ ጭጋግ በሸፈናቸው ተራሮቿ፣በአረንጓዴ ሸለቆዎቿና በአንጸባራቂ ሐይቆቿ ተማርኮ ለምስጋና ወደአምላክ አለማንጋጠጥ የማይታሰብ ነው፡፡ከተራሮቿ ቁልቁል የተለያየ ዝርያ ወዳላቸው የጽድ ጫካዎቿ የሚወርደው ነፋሻ አየር በልዩ ልዩ አበቦች መዓዛ የተሞላ ነው፡፡

በቤታችን ዘረኝነትና ምክንያት የለሽ ጥላቻ በፍጹም አይታወቁም። እኛ እንኖርበት በነበረው የሩዋንዳ ክፍል ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ አዕምሯቸው ቅንነትና መልካምነት የሌለው ግን ደግሞ አንደበታቸው ለጥላቻ፣ ለክፋትና ለተንኮል የተፈጠሩ ሰዎችነበሩ። ሁል ጊዜ ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ የጥላቻ ድምፅ እሰማለሁ፡፡ የአር.ቲ. ኤል. ኤም. ሬድዮ የጥላቻ ድምጾች በመኝታ ቤቴ መስኮት ገብተው ህልሞቼ ውስጥ እስኪደነቀሩ ሌሊቱን በሰላም ተኝቼ አሳልፋለሁ፡፡ በትምህርት ቀይታዬ አር. ቲ. ኤል. ኤም. በጽንፈኛ ሁቱዎች ዘንድ አዲሱና በጣም ታዋቂው ሬድዮ ጣቢያ ለመሆን ችሏል፡፡ ጸረ-ቱትሲ መርዝን የሚረጭ የተለያየ ጥላቻ መሣሪያ ወጥቶታል፡፡ሁሌ ‹‹ስለሁቱ የበላይነት›› የሚጮህ አካል-አልባ ክፉ ድምፅ ሆነ፡፡ የሁቱ የበላይነትም ሁቱዎችን በቱትሲ ወዳጆቻቸውና ጎረቤቶቻቸው ላይ እንዲነሱ የሚያደርግ ተናዳፊ ተርብ ለመሆን ቻለ፡፡

‹‹እነዚያ ቱትሲዎች ሊገድሉን ወጥተዋል፡፡ አትመኗቸው… እኛ ሁቱዎች ቀድመናቸው ልንነሳ ይገባናል! መንግሥታችንን ገልብጠው ሊያሳድዱን እየዶለቱብን ነው፡፡ በርዕሰ-

ብሔራችን ላይ አንዳች ነገር ቢከሰት ሁሉንም ቱትሲዎች ወዲያውኑ ማውደም ግድ ይለናል! እያንዳንዱ ሁቱ ሩዋንዳን ከነዚህ ቱትሲ በረሮዎች ለማጽዳት እጅ ለእጅ መያያዝ አለበት! የሁቱ የበላይነት! የሁቱ የበላይነት!›› የሚለውን ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ዜና እንደደህና ነገር በሬዴዎ ጣቢያው ተለቆ ይደመጣል፡፡ ይህን በመሰለ አጉለኛ ሁኔታ ከእንቅልፌ እነቃለሁ፡፡ እነዚያን የልጅ ስድቦችና ልቅ ማስፈራሪያዎች ማንም ሰው ከምር ይቀበላቸዋል ብሎ ማመን አሰቸጋሪ ሲሆን መንግሥቱም የሕዝብ ንብረት የሆነውን የአየር ሰዓት ተጠቅሞ ቱትሲዎችን ለማስፈራሪያ መፍቀዱን ማወቁ ይረብሻል፡፡ በወቅቱ ግን በሀገሪቱ በርካታ ስፍራዎች ቱትሲዎች በጽንፈኞች እየተገደሉ መሆኑን በሚገልጹ ወሬዎች ይበልጡን ተረበሽኩ፡፡ እኛም ሰማይን በድጋሜ አናይም ብለን አሰብን፡፡

ወደ እየ ሰዉ ቤት ገዳዮቹ ለማንም አስቀድመው ሳይናገሩ በቀንም ሆነ በማታ ባስፈለጋቸው ሰዓት እንደፈለጉ ይመላለሳሉ፡፡ ጥቂት ደርዘኖች ወይንም ጥቂት መቶዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በታዘዙበት ወቅት፣ በቁሱ ሬድዮ የሚሰሙት አዳዲሶቹ ዘገባዎች ያሰቅቃሉ፡፡ የመንግሥት አመራሮች እያንዳንዷን የሩዋንዳ የሬዲዮ ጣቢያ ስለግድያ መቀስቀሻ መሣሪያነት ለውጠዋታል፡፡ የሬድዮ ጣቢያው ሰዎች በማናቸውም ስፍራ የሚገኙ ሁቱዎች ቱትሲዎችን ምንም ጥያቄ መጠየቅ ሳያስፈልጋቸው ባገኙበት አጋጣሚ መግደል ግዴታቸው እንደሆነ ያስተጋባሉ፡፡

1. ተማሪዎች እስካሁን ካዳመጣችሁት ታሪክ ምን ተረዳችሁ?

2. የሩዋንዳ የዘር ጭፍጨፋ ምንጩ ምን ነበር?

አንዳንድ ገበሬዎች ሰብላቸው እየተበላሸባቸው እንደሆነ ሲያማርሩበት፤ አንድየመንግሥት ባለሥልጣን በሬድዮ አንድ ሰው ሰብሉን ለመንከባከብ ከግድያው አንድ ቀን እንኳን ቢቀር ሲሠራ ራሱን የሚከላከልበት መሣሪያ መያዝ አለበት ብሎ አሳሰበ፡፡ ‹‹መዘናጋት የለባችሁም! እነዚህ እባብ ቱትሲዎች በየሣርና ቁጥቋጦው ውስጥ ተደብቀዋል››አለ፡፡ ‹‹ስለሆነም እባቦቹን ከሁለት ለመቁረጥ መሳሪያቻሁን ይዛችሁ መዘጋጀታችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ ከተቻለ መሣሪያችሁን አንስታችሁ ተኩሳችሁ ግደሏቸው! ጠመንጃ ከሌላችሁ መንግሥት ይሰጣችኋል፡፡ ማሳችሁ ላይ እየሠራችሁ ሴት ቱትሲ በየጥሻው ልጇን ስታጠባ ካያችሁ ወርቃማ እድሉን እንዳታባክኑት፤ ጠመንጃችሁን አንሱ ፤ ግደሏት፤ እናም ግዴታችሁን እንደተወጣችሁ አውቃችሁ ወደሥራችሁ ተመለሱ፡፡›› በማለት ምንም ሳያመንቱ በሬዲዮው መቀስቀሱን ቀጠሉበት፡፡ ‹‹ ሕፃኑን መግደላችሁን ግን አትርሱ፤የእባብ ልጅ መቼም ቢሆን እባብ ነው፤ስለዚህ እርሱንም ግደሉት!›› የአካባቢው ባለ ስልጣናት በመንደሩ ነዳጅ ማደያ መሳሪያ ሲያድሉ ታጣቂዎቹ በበኩላቸው ከበር በር እየሄዱ ያስተባብራሉ፡፡

በሩዋንዳ ያለ ማናቸውም ሁቱ ጠመንጃ ያለው መስሏል፡፡ ይህ እንግዲህ በቱትሲዎች ላይ እንዲጠቀሙት ከሚያዝ መመሪያ ጋር የመጣ ነው፡፡ ማንም በዓለም ላይ ያለ ሰው ሃይ አላላቸውም፡፡ ከሬድዮ ዘገባዎች በምንሰማው እርዳታ እየመጣ እንዳልሆነ አውቀነዋል፡፡ ግን ሰዎች በዘርና ጎሳ ተለይተው እንዲገደሉ በነጋ በጠባ ሳይታክቱ በጣቢያቸው ያሰራጫሉ፡፡ አንዳንዴ ቁሱ በሬድዮ ዘገባዎች ያልተካተቱትን የመንግሥትን የዘር ፍጅት እቅዶች ይነግሩናል፡፡ ‹‹ሁሉም ቱትሲዎች ሲሞቱ ጭራሽ ያልነበሩ ለማስመሰል ታቅዷል፡፡ማንኛውንም አሻራቸውን ያጠፋሉ›› ሲሉ ምንም ሳይመስላቸው ነገሩን፡፡ ‹‹ በከተማው የማውቃቸው የመንግሥት ባለስልጣናት ሁሉንም ቱትሲ ነክ መዛግብት እንዲያጠፉ ታዘዋል፡፡ አብዛኞቹን የትምህርት ቤትና የሥራ መዛግብት

አቃጥለው ወደልደት፣ ጋብቻና ሞት ምስክር ወረቀቶች ተሽጋግረዋል፡፡ ያው በማንኛውም ከተማና መንደር ተመሳሳይ ነው፡፡ ትዕዛዙ አንድም የቱትሲ አሻራ በሩዋንዳ አፈር ላይ እንዳይቀር የሚል ነው››፡፡

በመካለኛው አፍሪካ በምትገኘው በሩዋንዳ የተካሄደውና አንድ ሚሊዮን ገደማ የሚሆኑ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈው የዘር ማጥፋት ክስተት በንጹሐን ዜጎች ላይ ከተፈጸሙ የተደራጁና መጠነ ሰፊ ዘግናኝ ድርጊቶች አንዱ ነው፡፡ ይህ ሁሉ እልቂትና ፍጅት የተከሰተው ደግሞ በአንድ የሬዲዮ ጣቢያ የጥላቻ ንግግር ወይም ቅስቀሳ ምክንያት ነው፡፡ይህም ጸረ-ቱትሲ የጥላቻ ውትወታ ሁቱዎች ቱትሲዎችን በየወቅቱ የጥቃቶቻቸው ሰለባ እንዲያደርጉ ገፋፍቷቸዋል፡፡ የሩዋንዳው ጭፍጨፋ ተራው ሕዝብ በሰፊው የተሳተፈበትና ‹‹ቱትሲዎች መጤዎች ናቸው›› በሚለው የቆየ የጥላቻ ቅስቀሳ ምክንያትነት በጨፍጫፊዎቹ ዓይን የነባርና የመጤ ግጭት ተደርጎ የሚታይ ነው፡፡ የሩዋንዳ የዘር ፍጅት የሰው ልጅ ጭካኔ ልክ የታየበት ነው፡፡

የጥላቻ ንግግር ሰዎች ባላቸው ማህበራዊ መሰርትና አቋም ወይም ርዕዮታለም ላይ በመመርኮዝ ሰዎችን በቡድን ወይም በተናጠል መገለልና መድሎ እንዲደርስባቸው ማድረግ ነው፡፡ ይህ አይነት መገለልና መድሎ ብሎም እልቂት በሩዋንዳ ብቻ ሳይሆን በአይሁዶች፣ጆፕሲዎችና በአወስትራሊያ ነባር ህዝቦችም ላይ ጭምር የደረሰ ነው፡፡ በተመሳሳይ ፍጅትና ጭካኔ የተፈጸመባቸው የናዚዎችና የአርመኖች እልቂቶች እንደሩዋንዳው መንስኤአቸው የዘር ጥላቻ እንዲፈጠር በተደረገ ከፍተኛ የጥላቻ ንግግር ቅስቃሳ ሳቢያ ነበር፡፡የጥላቻ ንግግር ወይም ዘመቻ መሰረተቢስ በሆነ ምክንያት ላይ ተመስርቶ በሰዎች ላይ አሉታዊ አስተሳሰብን መጫን ነው፡፡ ይህ ሁሉ እልቂትና ጥፋት የተፈጠረው እኛ በጣም ቀላል አድረገን በምናየው የሀሰት መረጃና የጥላቻ ንግግር ዘመቻ ነው፡፡ ውሸት ሀገር ያፈርሳል፣ ሰዎችን ያለስራቸው በማያውቁት ነገር ችግር ውስጥ ይጥላል፡፡ የጥላቻ ንግግር ደግሞ በመገናኛ ብዙሃን ሲታገዝ ችግሩን የበለጠ ያባብሰዋል፡፡

ምንጭ (መምህር ግርማ 2011 ሀቱቱሲ የትርጉም ስራ)

- ምንባቡን ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎቹ ድጋሜ እንዲነበብላቸው ፍላጎት ካላቸው ይጠይቋቸው፡፡ ፍላጎት ካላቸው በመጠነኛ ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡ አለበለዚያ ግን ወደቀጣዩ ተግባር ይለፉ፡፡

- በአዳምጦ መረዳት ስር የቀረቡትን የእውነት ሐሰት ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ሙሉ በሙሉ መመለስ ከቻሉ ጥሩ ካልሆነ ግን ያልመለሱት ጥያቄ የሚገኝበትን አንቀጽ ያስታውሷቸውና ለመመለስ ሙከራ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት በቃል መልሱ፡፡

ሀ. ሐሰት

ለ. እውነት

ሐ. ሐሰት

መ. ሐሰት

ሠ. እውነት

ረ. እውነት

ክፍል ሁለት ንባብ

- ❖ በማዳመጥ ጊዜ የቀረበውን ምንባብ ታሪክ በጥያቄና መልስ ያስታውሷቸው፡፡ የዕለቱን ምንባብ ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸውና ከማዳመጥ ምንባብ ታሪክ ጋር ሊኖረው የሚችለውን ዝምድና እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በመቀጠል በቅድመ ንባብ ስር ያሉትን ጥያቄዎች በቃል ያሰሯቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች እየተሳተፉ መሆኑን ይከታተሉ፡፡ ጥያቄዎቹን ሰርተው ሲጨርሱ ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የሰጡት መልስ ምን ያህል ትክክል እንደሆነ ምንባቡን ሲያነቡ እያረጋገጡ እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ ከዚያም ምንባቡን በጥሞና እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ እነሱ ሲያነቡ እርስዎ እያንዳንዱ ተማሪ እያነበበ መሆኑን ለማረጋገጥ ቅኝት ያድርጉ፡፡ ንባቡን ገታ አድርገው የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ በፊት የሰጡትን ግምትና ከምንባቡ ያገኙት ሀሳብ ተመሳሳይ መሆኑንና አለመሆኑን ከነምክንያቱ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ምንባቡን አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ ከምንባቡ የሚጠይቁት ጥያቄ ካለ የመጠየቅ እድል ይስጧቸው፡፡ላቀረቡት ጥያቄ መላሽ በራሳቸው እንዲሞክሩ ያድርጉና ከመለሱ መልካም ካልሆነ ግን እርስዎ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- ❖ በመቀጠል በአንብቦ መረዳት ስር ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡ በመጀመሪያ በተግባር ሁለት ስር የቀረቡትን የእውነት ሀሰት ጥያቄዎች በምክንት እያስደገፉ በቃላቸው እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በተግባር ሶስት ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ምንባቡን ሲያነቡ ላወቋው ቃልት አገባባዊ ፍች የሚያሳዩ አረፍተ ነገሮች እንዲሰሩ የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህ የቀረቡት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ የሚሳዩ አረፍተ ነገሮች እንዲሰሩባቸው ይግለፁላቸው፡፡
- ❖ በተግባር አራት ስር በቀረቡት ሶስት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ለመወያየትያመች ዘንድ በቡድን እንዲመሰረቱያድርጉ፡፡ በዚያውም አወያይና ፅሀፊ መርጠው በውይይት መመሪያ ጠብቀው እንዲወያዩ ድርጓቸው፡ ውይይቱ ሲካሄድ እየተዘዋወሩ ተማሪሪዎችን ይመልከቷቸው፡፡ የማሳተፉ ተማሪዎች ካሉ እንዲሳተፉ በመንገር ቡድኑን እንዲሳትፋቸው ይግለፁ ላቸው፡፡
- ❖ ውይይቱን ካአጠናቀቁ በኋላ የቡድን ተጠሪዎች በተራ በተራ የውይይቱን ውጤት በንባብ እንዲቀርቡ ድርጉ፡፡ ላደረጉት ተሳትፎ በጣም ጥሩ፣ እጅግ በታም ጥሩ፣ አመሰግናለሁ፣ ጎበዝ፣ ወዘተ ሚሉትን የማበረታቻ ቃል በመጠቀም ድጋፍዎትን ይግለፁላቸው፡፡ ከቡድኑ መካከል ተሸለ ሀሳብ ያቀረበ ካለም በማስጨብጨብ በረተወቷቸው፡፡ የማተቃለያ ሀሳብ ይስቷቸውና የእለቱን ትምህርት ያጠናቁ፡፡

በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት

የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ‹‹እውነት›› ትክክል ካልሆኑ ‹‹ ሐሰት›› በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ መልሱ፡፡

ሀ. እውነት

ለ. እውነት

ሐ. ሐሰት

መ. እውነት

ሠ. ሐሰት

ረ. ሐሰት

ሰ. ሐሰት

ሸ. እውነት

ተግባር ሶስት

በሚከተሉት የተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ሀ. ማፍረሻ

ለ. ቁርኝት

ሐ. መውጣት

መ. መጥፎ አመለካከት

ሠ. ማሳደግ ፣ ማሻሻል

ረ. ብቸኛ ማድረግ

ሰ. እገዳ ፣ ክልከላ

ሸ. ግዴለሽነት

## ክፍል ሶስት ቃላት

## የቃላት አገባባዊ ፍቺ

- በቃላት ትምህርት ስር ተማሪዎች ለቃላት ተመሳሳይ ተቃራኒ እና መዝገበቃላዊ ፍቺ እንዲሰጡ በተለያየ መንገድ ቀርቦላቸዋል፡፡ ስለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ቀደም ሲል ስለተማሩ ምንም ማብራሪያ መስጠት ባያስፈልግም ስለመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ግን የተወሰነ ፍንጭ ይስጧቸው፡፡
- በመጀመሪያ በአዛምድ መልክ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን እየፈለጉ እንዲያዛምዱ፣ ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ እየሰጡ ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ከመዝገበ ቃላት እየፈለጉ እንዲሰጡ ያስርዷቸው፡፡ የሰጡትን ምላሽ እንዲቀርቡ በማድረግ በትክክል መመለሳቸውን ያረጋግጡ፡፡ ማስተካከያ መስጠት የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ ማስተካከያ በመስጠት እርማት እንዲዎስዱ ያበረታቷቸው፡፡

በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

በ‹‹ሀ››ስር ለቀረቡት ቃላት በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩት በፍቺ ተመሳሳይ የሚሆኑትን እየመረጣችሁ አዛምዱ፡፡

1. ሠ
2. ሐ
3. ለ
4. ሀ
5. መ

ተግባር ሶስት

ለሚከተሉት ቃላት ከመዝገበ ቃላት ፍቻቸውን ፈልጋችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ምሳሌ፣ ፍቱን መድሐኒት

ለ. ተንኮል

ሐ. ህልም

መ. ፌዝ፣ ምፀት

ሠ. የስልጣን ብልግና

ረ. ታላቅ ደስታ

ሰ. ወፈረ

ሸ. አገናዘበ

ቀ. ንጋት

በ. ብርሃን

ተግባር ሁለት

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እየሰጣችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ሀ. ውድቀት

ለ. ጀማሪ

ሐ. መዘግየት

መ. መርጋት

ሠ. መታጠፍ

ረ. ሰነፍ

ሰ. ቀጠለ

ሸ. ጠገበ

በ. ተወደደ

ተ. ሰበሰበ

ክፍል አራት ጽሕፈት

አስመስሎ መፃፍ

❖ መምህር ወደ ፅህፈት ተግባር ከመግባትዎ በፊት ከስር የቀረበውን ስለ ሀቅና የግል አስተያት ምንነት በምሳሌ ተደገፈ ማስታወሻ ለተማሪዎቹ ያስረዷቸውና ማስተዋሻ እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

ማሰታወሻ፡

ሀቅና የግል አስተያየት

የግል አስተያየት የተናጋሪዎችን አመለካከትና ስሜት የሚያንፀባርቅ ሲሆን ስለትክክለኛነቱ በመረጃ ሊረጋገጥ የማይችል ሀሳብ ነው፡፡በሌላ አገላለፅ የግል አስተያየት እውነት ይሁን ሀሰት ለማረጋገጥ የሚያስቸግር በአብዛኛው ሰው ተቀባይነት የሌለው ፣በሳይንስ ያልተረጋገጠ፣በይሆናል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በሌላ በኩል ሀቅ የሆነ አስተያየት በእውነት ላይ የተመሰረተና በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል፣ አስተያየቱ ስለ እውነትነቱ በሳይንስ ማረጋገጥ የሚቻልበት ነው፡፡

ምሳሌ፡-

- በዓለም ላይ ያሉ ቋንቋዎች ሁሉ እኩል ናቸው፡፡ በሀቅ ላይ የተመሰረት አስተያየት
- ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ የሚተላለፈው በዋነኛነት ልቅ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው፡፡ በሀቅ ላይ የተመሰረተ አስተያየት
- የአማረኛ መምህሬ የሚወደኝ አይመስለኝም፡፡ በግል አስተያየት ላይ የተመሰረተ
- ሴቶችን ማስተማር ማህበረሰብን ማስተማር ነው፡፡ በሀቅ ላይ የተመሰረተ አስተያየት
- የጤፍ ዋጋ በሚቀጥለው ወር መቀነሱ አይቀርም፡፡ በግል አስተያየት ላይ የተመሰረተ

❖ በመቀጠልም በተግባር አንድ ስር ቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ሀቅና የግል አስተያየት በማለት እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡ የሰጡትን መልስ እንዲቀርቡ በማድረግ ትክክለኝነታቸውን ያረጋግጡ፡፡

❖ በተግባር ሁለት ስር አንድ አንቀፅ ፅሁፍ ቀርቧል፡፡ፅሁፉን ደጋግመው ካነበቡ በኋላ አስመስለው ሌለ ፅሑፍ ፅፈው እንዲሳዩ ይግለፁላቸው፡፡፡

❖ የፃፉትን ፅሑፍ በክፍል ውስጥ ከጓደኞቻቸው ጋር ተቀያይረው እንዲገማገሙ ያድርጉና አስተያየት እንዲሰጣጡ ያድርጉ፡፡

❖ በመጨረሻም በጽሁፋቸው ላይ የእርሰዎን አስተያትና ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በምሳሌው መሰረት ሀቅና የግል አስተያየት በማለት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ሀቅ

ለ. ሀቅ

ሐ. ሀቅ

መ. የግል አስተያየት

ሠ. ሀቅ

ረ. የግል አስተያየት

ሰ. ሀቅ

ሸ. የግልአስተያየት

ቀ. ሀቅ

በ. ሀቅ

## ክፍል አምስት ሰዋስው

### ቅፅሎችን መለየት

- ❖ በክፍል አምስት ተማሪዎቹ የእናን እና ነገር ግን አያያዥ ቃላት ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ፣ቅፅልን፣ ነጠላና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ለይተው እንዲገልፁ ይጠበቃል፡፡
- ❖ በተጨማሪም ስለ አያያዥ ቃላት ቀደም ሲል የተማሩትን በክለሳ መልክ ያስታውሷቸውና  እናን እና ነገር ግን የሚሉ አያዥ ቃላት ተጠቅመው ዓረፍተ ነገሮችን አያይዘው እንዲፅፉ ይግለፁላቸው፡፡
- ❖ አያያዥ ቃላቱን ተጠቅመው የመሰረቱትን ዓረፍተ ነገሮች ይለዩላቸውና በትክክል መስራታቸውን  ይፈትሹ፡፡
- ❖ በመቀጠልም ከቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ግስ የሆኑትን ቃላት እየለዩ እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በተግባር አራት ስር ከቀረቡት ቃላት ቅፅል የሆኑትን ለይተው በቻርት ውስጥ ፅፈው እንዲያሳዩ ይግለፁላቸው፡፡
- ❖ በተግባር አምስት  ደግሞ ተዘረዘሩትን ቅፅሎች የባህሪ፣የአይነትና የመጠን እያሉ በመለየት በሰንጠረዥ እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ከዚህ በታች ስለ ተራና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር  በተመከተ ማስታወሻ ቀርቧል፡፡ የቀረበውን ማስታወሻ ለተማሪዎች በደብተራቸው ያፅፏቸውና  ስለ ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገር  ያስረዷቸው፡፡ነጠላ ዓረፍተ ነገር በውስጡ አንድ ግስ ብቻ ያለው  ሲሆን ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ደግሞ ሁለትና ከሁለት በላይ ግስ የሚይዝ  መሆኑን ይግለፁላቸው፡፡ በተግባር አንድ ላይ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ነጠላና ውስብስብ ብለው እንዲለዩ ይግለፁ ላቸው፡፡

ማስታወሻ፡-

ዓረፍተ ነገር

ዓረፍተ ነገር  ቃላት እና ሀረጋት በስርዓት ተቀናጅተው ሙሉ ስሜት  በሚሰጥ መልኩ የተደራጀ አንዱ የቋንቋ መዋቅር ነው፡፡  አንድ ዓረፍተ ነገር በውስጡ ከሚይዘው ግስ ብዛት አንፃር ነጠላና ውስብስብ  ብሎ መክፈል ይቻላል፡፡

ነጠላ ዓረፍተ ነገር፡-

ይህ የዓረፍተ ነገር አይነት አንድ ግስ ብቻ ያለው ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ከስማዊ ሀረግና ከግሳዊ ሀረግ የሚዋቀር ነው፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ. ፋጡማ የቤቱን ግቢ አፀዳች፡፡

ለ. ያሬድ ወደትምህርት ቤት በጠዋት ሄደ፡፡

ሐ. አስቴር ብርጭቆውን ወለወለች፡፡

መ. ተማሪዎች በትምህር ቤታቸው የሰላም ክበብ መሰረቱ፡፡

2. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

ይህ የዓረፍተ ነገር አይነት ሁለትና ከዚያ በላይ ግስ ያለው ሲሆን በተለያዩ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ተዋህዶ ይቀርባል፡፡ ስለሆነም ውስብስብ ዐረፍተ ነገር ዋና መለያው በውስጡ በያዘው የግስ ብዛት ነው፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ. ናትናኤል ምሳውን በልቶ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

ለ. ልጁ እጁን ታጥቦ ምሳውን በላ፡፡

ሐ. ኢትዮጵያውያን ምርታቸውን ወደ አለም ገበያ ወስደው መሸጥ ጀመሩ፡፡ በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

ቀጥለው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በምሳሌው መሰርት ነጠላ ወይም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር በማለት ለይታችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ነጠላ

ለ. ውስብስብ

ሐ. ነጠላ

መ. ነጠላ

ሠ. ውስብስብ

ረ. ውስብስብ

ሰ. ውስብስብ

ሸ. ነጠላ

ቀ. ውስብስብ

በ. ውስብስብ

ተግባር ሁለት

ቀጥሎ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች በምሳሌው መሰረት ለዩና በደብተራችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ስለመጡ፣ ተቀበለቻቸው

ለ. ፈጥኖ፣ በርግጎ፣ ተነሳ

ሐ. ለብሰዋል

መ. የገዛቸው፣ያምራል

ሠ. ሲመለስ፣ ቀየረ

ረ. ሲያጋጥም፣ ማጽናናት፣ ያስፈልጋል

ተግባር አራት

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቅፅሎች በተሰጠው ምሳሌ መሰረት የአይነት፣ የባህሪና የመጠን አመልካች እያላችሁ በሰንጠረዡ ውስጥ መድቡ፡፡

| ተ/ቁ | አይነት ገላጭ ቅፅል | ባህሪ ገላጭ ቅፅል | መጠን ገላጭ ቀፅል |
|---|---|---|---|
| 1 | ቀያይ | ሰነፍ | አጭር |
| 2 | ሰማያዊ | ንቁ | ደንዳና |
| 3 | አረንጓዴ | ሞኝ | ግዙፍ |
| 4 | ሮዝ | ሆዳም | ረጂም |
| 5 | | በጎ | ጠባብ |
| 6 | | | |

# ምዕራፍ ስምንት(፰)

## ኤች አይ ቪ ኤድስ

ክፍለ ጊዜ 18

የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች

- ✓ ባለብዙ ቅጥያ ምዕላዶችን ይለያሉ
- ✓ የራሳቸውን አመለካከት ይፅፋሉ
- ✓ የፅሁፍ አላባውያንን ይገልፃሉ
- ✓ ለምዕላዶች ትርጉም ይሰጣሉ

የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች

- ➢ ለዋና ሀሳብ ማዳመጥ
- ➢ ማዳመጥና ክርክር
- ➢ ማንበብና ፅብረቃ
- ➢ የፅሁፍ ክፍሎች
- ➢ የቃላት ተቃራኒ
- ➢ ተሻጋሪና ኢ-ተሻጋሪ ግሶች

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

‹‹ ያልጠረጠረ ተመነጠረ››

የትምህርቱ አቀራረብ

- መምህር በዚህ ምዕራፍ ስር የቀረበው ምንባብ ኤች አይ ቪ ኤድስን የተመለከተ ነው፡፡ ምንባቡ ቋንቋን ከማስተማር ባሻገር በሀገራችን ላይ ጉዳት እያደረሰ ስላለው የኤድስ በሽታ ለተማሪዎቹ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያግዛል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ተማሪዎቹ የበሽታውን አስከፊነት ከተለያየ አቅጣጫ እንዲመለከቱት ለማድረግ የእርስዎ ጥረት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ከቋንቋ ክሂል ትምህርት በተጨማሪ ስለበሽታው ግንዛቤ የሚያስጨብጥ አቀራረብን ቢጠቀሙ ተመራጭነት ይኖረዋል፡፡
- በቅድመ ማዳመጥ ተግባር ስር ያሉትን ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ በማድረግ ያነቃቋቸው እያንዳንዱ ጥያቄ ሁሉም ተማሪ መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ለጥያቄዎቹ የሰጡትን መልስ በማመስገን ተቀብለው ወደዋናው የማዳመጥ ተግባር እንዲሸጋገሩ ያግዟቸው፡፡ ከዚያ በፊ ትግን በተግባር አንድና በተግባር ሁለት የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲያነቡ ያስረዷቸው፡፡
- ጥያቄዎቹን አንብበው ሲያጠናቅቁ ምንባቡ ሲነበብላቸው ጥያቄዎቹን እያሰቡ እንዲያዳምጡ ይግለጹላቸው፡፡በመቀጠል ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡

የተወለድኩት አዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡ እረዳት አልነበረኝም፡፡ በዚህ ምክንያት በአንድ ሱቅ ውስጥ በሻጭነት ተቀጠርኩ፡፡ ግማሽ ቀን እየሰራሁ ግማሽ ቀን ደግሞ ትምህርቴን እማር ነበር፡፡ በምሰራው ስራ የተሻለ ገንዘብ በማግኘቴ ገንዘብን ይበልጥ እየተላመድኩ ሄድኩና ስምንተኛ ክፍል እንደደረስኩ ትምህርቴን አቋረጥኩት፡፡ ቀስ በቀስ ስራው በፈጠረልኝ አጋጣሚ ከተለያዩ የንግድ ሰዎች ጋር ተዋወቅኩ፡፡ ለገበያ ተፈላጊ የሆኑ እቃዎችን መለየት ቻልኩ፡፡ አዳዲስ እቃዎችን እየተረከብኩኝ ለሌሎች ባለሱቆች መሸጥ ጀመርኩ፡፡ በዚህም ጠቀም ያለ ትርፍ ወደማግኘቱ ስሸጋገር የሻጭነት ስራዬን ተውኩና በድለላ ስራ ላይ ተሰማራሁ፡፡በሱቅ ውስጥ በምሰራበት ጊዜ ምንም አይነት ትርፍ ጊዜ አልነበረኝም፡፡ በአዲሱ ስራዬ ግን ትርፍ ጊዜ በማግኘቴ ለሱስ ተጋላጭ እየሆንኩ መጣሁ፡፡ጫት የሚቅሙ ጓደኞች ስላፈራሁ ሁልጊዜ ከምሳ ስዓት በኋላ የምውለው በጫት መቃሚያ ቤት ሆነ፡፡ ከጫት በኋላ ደግሞ ወደመጠጥ ቤት እሄዳለሁ፡፡ ከአንድ ቤት መጠጣት እጀምርና በሞቅታ የተለያዩ መጠጥ ቤቶችን በማዳረስ ስጠጣ አመሻለሁ፡፡ በስካር መንፈስ ብዙ ሴተኛ አዳሪዎችን እየጋበዝኩና ከእነሱ ጋር እየተጫዎትኩ አመሽና

ከአንዷ ደበኛዬ ጋር አድራለሁ፡፡ በዚህ ምክንያት በርካታ የቡና ቤት ሴቶች ያውቁኝ ነበር፡፡ ሁኔታዬ ያላማራቸው ብዙ ሰዎች  የባህሪ ለውጥ እንዳመጣ ይመክሩኝ ጀመር በዚህም የመጠጡን ነገር በመጠኑም ቢሆን ልቆጣጠረው ሞከርኩ፡፡ ከዚህ በፊት ከነበሩኝ የቡና ቤት ሴት ደንበኞች ጋር የነበረኝን ግንኙነት ግን ማቆም አልቻልኩም ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ ረጅም ጊዜያትን አሳለፍኩ፡፡ በሂደትም ብርድ ብርድ የሚልና እንደሳል ያሉ የህመም ስሜቶች ይሰሙኝ ጀመር፡፡ ስሜቶቹ ሲደጋገሙብኝ በአካባቢዬ በሚገኘው አንድ ጤና ጣቢያ ሄጄ ተመረመርኩና  የሳንባ ነቀርሳ በሽታ እንዳለብኝ ተነገረኝ፡፡ህክምናውን መከታተል ጀመርኩ፡፡ ጤንነቴ ለውጥ እያሳዬ መጣ፡፡ ነገር ግን እንደበፊቱ ተሯሩጬ መስራት አልቻልኩም፡፡ ከሳንባ ህመሜ ባገግምም የሌሎች በሽታ ስሜቶች  ይታዩብን ጀመር፡፡ ሰውነቴም እየከሳ መጣ፡፡ ይህንን ያስተዋሉ የቅርብ ጓደኞቼ ምንአልባት ኤች አይ ቪ ሊሆን ይችላል በሚል የደም ምርመራ እንዳደርግ መከሩኝ፡፡ እኔም ምክራቸውን ተቀብዬ ወደ ሀኪም ቤት ሄጄ ተመረመርኩ፡፡ ከምርመራው በኋላ ኤች አይቪ በደሜ ውስጥ መኖሩ ተነገረኝ፡፡ ውጤቱን ስሰማ  ያለሁበትን አላውቅም ነበር፡፡ ዶክተሩ መክረውና አረጋግተው እንደማንኛውም ሰው መኖር እንደምችል  ከነገሩኝ በኋላ ቀጠሮ ሰጥተው ሸኙኝ፡፡ በልጅነት እድሜዬ ኑሮየን ለመምራት ሰርቼ ገንዘብ ማግኘት ብችልም ገንዘቤን በአግባቡ መጠቀም አልቻልኩም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ለኤች አይቪ ኤድስ ተጋላጭና ህመምተኛ ሆንኩ፡፡ አሁን የሀኪሜን ምክር እየተከታተልኩና ለኤድስ ህሙማን የሚሰጠውን መድሃኒት እየወሰድኩ ነው፡፡ ባለማወቄ በሽታውን ለበርካታ ሴቶች ማስተላለፌ ስለሚፀፀተኝ የእኔ እጣ ፈንታ በሌሎች እንዳይደርስ እየመከርኩና እያስተማርኩኝ እገኛለሁ፡፡

ምንጭ(አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ስባተኛ ክፍል

2007፣51 ተሻሽሎ የተወሰደ)

- የማዳመጥ ተግባር ሲያበቃ ቀድመው ያነበቧቸውን ጥያቄዎች ደግመው እንዲያነቡ ያድርጉና ባዳመጡት መሰረት ለቃላቱ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- በተግባር ሶስት ስር በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ለመወያየት በሚያስችል መልኩ ይመድቧቸው፡፡ በራሳቸው አወያይና ፀሀፊ እንዲመርጡ ያድርጉ፡፡
- በሁሉም ጥያቄዎች ላይ ማስታወሻ እየያዙ እንዲወያዩ ያስረዷቸው፡፡ በውይይቱ ሂደት እርስዎ እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡

- የማይሳተፉ ተማሪዎች ካሉ እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡ የተወያዩበትን ሀሳብ ለማስቀረብ ለቡድኑ ጥያቄዎቹን ለቡድኑ ከፋፍለው ይስጧቸው፡፡
- የተሰጣቸውን ጥያቄ ብቻ እንዲያቀርቡ በመንገር ጥያቄው የደረሰው ቡድን ሲያቀርብ ሌሎቹ እንዲከታተሉ ያድርጉ፡፡
- በቀረበው ሀሳብ ላይ ተጨማሪ ሀሳብ ያለው ቡድን ካለ እንዲያቀርብ እድል ይስጡ፡፡ ለምሳሌ ጥያቄ ቁጥር አንድ የደረሰው ቡድን ሲያቀርብ ሌላው ቡድን አዳምጦ በጥያቄ ቁጥር አንድ ላይ ተጨማሪ ሀሳብ ያለው ካለ እንዲናገር መስጠት ማለት ነው፡፡ በቀረበው ሀሳብ እርስ በርስ አስተያየት እንዲለዋወጡ ያድርጉ፡፡
- በዚህ መልክ ሁሉም ቡድነን ካቀረበ በኋላ የማጠቃለያ ሀሳብ እርስዎ ይሰጧቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት

የሚከተሉትን ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በጽሁፍ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. አስፈላጊ

ለ. እድል፣ድርሻ

ሐ. ስላገኘሁ

መ. መዳረግ

ሠ. መስከን፣

ረ. በጎ ተግሳጽ

ሰ. በጎ ሆነ፣ ተሻለው

ሸ. ተጨማሪ

ቀ. ማቆም፣ መተው

## ክፍል ሁለት ንባብ

- ❖ ወደቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ከመግባትዎ በፊት ስለ ርዕሱ ጠቅለል ያለ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ለምሳሌ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ የምታውቁትን ግለጹ፡፡ የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡላቸው ተማሪዎቹ ስለ በሽታው ያላቸውን የቀደመ ዕውቀት ስለሚያስገነዝብዎ ለተማሪዎቹ ስለ በሽታው ከምን ተነስተው እስከ ምን መረጃ መስጠት እንዳለብዎ ይጠቁምዎታል፡፡
- ❖ በመቀጠል የቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹን በቃል እንዲመልሱ ይግለጹላቸው፡፡ ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልስ ከሰጡ በኋላ ምንባቡን ተራ በተራ ድምፃቸውን እያሰሙ እንዲያነቡ በማድረግ ሌሎቹ ደግሞ ንባቡን እንዲከታተሉ ያድርጉ፡፡
- ❖ በዚህ ጊዜ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎቹ ካሉ ማገዝ እንዳይረሱ፡፡
- ❖ ማንበባቸውን ሲያጠናቅቁ በንባብ ጊዜ ሀሳቡን ለመረዳት ያስቸገራቸው አዳዲስ ቃል ካለ እንዲጠይቁ እድሉን ይስጧቸው፡፡ የቀረበ ጥያቄ ካለ መልሱን ይስጧቸውና ወደተግባር ሁለት ይለፉ፡፡
- ❖ በተግባር ሁለት ስር የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ፣ በተግባር ሶስት ስር በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ሌላ ሊተካ የሚችል ቃል ፈልገው እንዲተኩ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድረግ ለቃላቱ በትክክል ተመሳሳይ ፍቺ እንደሰጡና ለተሰመረባቸው ቃላት ሌላ አቻ ቃል መተካት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ❖ በዚህ ጊዜ ማስተካከያ መስጠት የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ ማስተካከያውን ይስጧቸውና እርማት እንዲወስዱ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻ በተግባር አራት ስር ያለውን ሰንጠረዥ በምንባቡ ውስጥ ካገኙት ሀሳብ ወጣ ብለው እንዲያሰላስሉ የሚያደርግ በመሆኑ በቡድን እየተወያዩ የኤች አይ ቪ ቫይረስ መተላለፊያ መንገድ የሆኑትንና ያልሆኑትን ለይተው እንዲጽፉ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎቹ እየተወያዩ የሚጽፉትን እየተዘዋወሩ በመመልከት የበሽታውን መተላለፊያ መንገድ የሆኑትንና ያልሆኑትን በትክክል ይግለጹላቸውና በእውነት የተደገፈ መረጃ እነዲኖራቸው ያግዟቸው፡፡

- የቀረበውን ሰንጠረዥ በሚሞሉ ጊዜ ተማሪዎቹ የማሰላሰል፣ሀሳብ የማፍለቅና የመፃፍ ክሂል ያዳብራሉ። እግረ መንገድ ደግሞ ስለበሽታው መተላለፊያ መንገድ በቂ ግንዛቤ ስለሚያገኙ አላስፈላጊ አግላይነት ተግባር እንዳይፈፅሙ ስለሚያደርግ ትኩረት በመስጠት ለተማሪዎቹ እንዲተገብሩት ያበረታቷቸው።

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሁለት

ለሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. መረበሽ

ለ. መለወጥ

ሐ. መሰራጨት

መ. ችግር

ሠ. ድካም፣ውጣውረድ

ረ. አጋዥ፣ረዳት

ተግባር ሶስት

በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በፍቺ የሚተካቸውን ቃላትና ሀረጋት እያስገባችሁ ፃፉ።

ሀ. ቁጥር

ለ. ከሚዛመትባቸው

ሐ. ተጎጂ

መ. አደንዛዥ ንጥረ ነገር

ሠ. ማእከላት

ረ. ረቂቅ

## ክፍል ሶስትቃላት

## የቃላት ተቃራኒ ፍቺ

❖ በዚህ ክፍል ተማሪዎቹ ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ በመስጠት ከተዘረዘሩት ቃላት በፍቺ ልዩ የሆነውን ማውጣትና በአረፍተ ነገር ውስጥ ተገቢውን ቃል እያስገቡ ባዶ ቦታውን እንዲያሟሉ ይጠበቃል፡፡

❖ በተግባር አንድ ስር በአዛምድ የቀረበውን ተግባር በ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ከ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት በፍቺ ተቃራኒ የሆኑትን እየመረጡ እንዲያዛምዱ ያስረዷቸው፡፡

❖ በመቀጠል ከአንድ እስከ አስር ተዘርዝረው ከቀረቡት ቃላት በፍቺ ልዩ የሆነውን ለይተው እንዲፅፉ ይግለፁላቸው፡፡

❖ በመጨረሻም በተግባር ሶስት ስር ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ባዶ ቦታዎች የሚያሟሉ ከላይ ከተዘረዘሩት ቃላት እየመረጡ እንዲሞሉ ይግለፁላቸው፡

❖ በትክክል መልስ መስጠታቸውን ለማወቅ ደብተራቸውን ሰብስበው ያርሙላቸው፡፡ በዚያውም የተሳሳቱት ካለ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

በ‹‹ሀ›› ስርለቀረቡት ቃላትና ሀረጎች በ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት ውስጥ ተቃራኒ የሚሆኑትን በበምረጥ አዛምዱ፡

የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

1. ሠ
2. ሰ
3. በ
4. መ
5. ሀ
6. ሸ
7. ሐ
8. ቀ
9. ረ
10. ለ

ተግባር ሁለት

ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ልዩ የሆነውን ቃል እየመረጣችሁ በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

1. መ
2. ሐ
3. ሀ
4. ሀ
5. መ
6. ሐ
7. ሀ
8. መ
9. ሀ
10. ለ

ተግባር ሶስት

የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት ቀጥለው በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ አስገቡ፡፡

ሀ. ምናቡ

ለ. ዘመም

ሐ. ብርድ ብርድ

መ. ቆረጥ ቆረጥ

ሠ. ወቋጫው

ረ. በተረጋጋ መንፈስ

ሰ. መንገድ

ሸ. ጥንካሬ

ቀ. ጥርግርግ

በ. ጥቅልል

## ክፍል አራት ጽሕፈት

### የጽሑፍ አላባውያን

- ❖ በፅህፈት ስር የቀረበውን የክርክር መመሪያ ማስታወሻ በደብተራቸው ፅፈው እንዲያነቡ ይግለፀፁላቸው፡፡
- ❖ ከዚም ክርክር በማካሄድ ቅድመ ዝግጅት እንደሚስፈልገውና በክርክር ጊዜ ምን መደረግ እንደሚገባ አፅኖት ሰጥተው በጥያቄና መልስ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- ❖ ከዚያም ለክርክር የሚያስችል ቡድን እና ዳኛ በፈቃደኝነት እንዲመርጡ ያድርጉና ከቀረቡላቸው ርዕሶች አንዱን መርጠው እንዲዘጋጁ ይግለፁላቸው፡፡ በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ክርክሩን እንዲካሂዱ ያድርጉ፡፡
- ❖ ክርክሩ ሲካሄድ ከተከራካሪና ከዳኞች ውጭ ያሉት ተማሪዎች እየተከታተሉ ማስታወሻ እንዲዙ ያስረዷቸው፡፡ በዚህ ጊዜ እርስዎ ተከራካሪዎቹ የክርክር መመሪን ተብቀው መከራከራቸውን በመከታተል ማስታወሻ ይያዙ፡፡
- ❖ ክርክሩ ሲጠናቀቅ ቅድሚያ ክርክሩን ሲከታተሉ የነበሩት ተማሪዎች አስተያየታቸውን እንዲገልፁ ይጋብዟቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም ማጠቃለያ ክርክሩን ተንካራ ጎንና መሻሻል የሚገባውን ነጥብ በመጥቀስ ስረዷቸው፡፡
- ❖ ሌላው በፅህፈት ስር ቀረበው ተግባር የፅሁፍ ክፍሎች መለየት ከዚያም የቀረበውን ፅሁፍ አንብበው ባነበቡት ፅሁፍ መሰረት መግቢ፣ሀተታና መደምደሚያያለው ፅሁፍ እንዲያዘጋጁ ያድርጉ፡፡
- ❖ በዚህ መሰረት በመምህሩ መምሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረበውን የፅሁፍ ክፍሎች ማስታወሻ በደብተራቸው ያፅፏቸው፡፡
- ❖ ከዚያም በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በምሳሌነት የቀረበው ፅሁፍ በመጠቀም የፅሁፍ ክፍሎችን ምንነትና በፅሁፍ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ በመቀጠል በምሳሌ የቀረበውን ፅሁፍ በድጋሜ አንብበው በዚሁ መሰረት ከስር ከቀረቡት ርዕሶች አንዱን መርጠው መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚ ለው ፅሁፍ እንዲፅፉ ይግለፁላቸው፡፡

❖ የፃፉትን ፅሁፍ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲለዋወጡ በማድረግ የፅሁፍ ክፍሎችን የያዘ መሆን አለመሆኑን በትክክል መግቢ፣ሀተታና መደምደሚ ላይ መገለፅ ያለባቸው ሀሳቦች መቅረብ መቻላቸውን እንዲፈትሹ ያስገንዝቧቸው።

❖ ከዚያም ያገኙትን ጠንካራና መስተካከል ወይም መሻሻል የሚገባውን ነጥብ እንዲገልፁ ያድርጉ።

❖ ለተሰተው አስተያየት ምስጋና አቅርበው እርስዎ የያዙት ፅሁፍ ካለ ሶስቱን የፅሁፍ ክፍሎች የያዘ ፅሁፍ ለምሳሌነት በማቅረብ ትምህርቱን ያጠናክሩ።

❖ ካልሆነ ግን ከተማሪዎቹ መካከል የተሻለ የሰራውን አስቀርበው የእለቱን ትምህርት ማጠቃለያ መስጠት ይችላሉ።

ማስታወሻ፡-

የድርሰት ክፍሎች

ድርሰት ሰፋ ያለ ሀሳብ የሚቀርብበበት እንደመሆኑ መጠን በሶስት ዋና ዋና ክፍልች ሊደራጅ ይችላል።

ሀ. መግቢያ፡- ወደ ዋናው ጉዳይ እያዋዛ የሚያስገባ ክፍል ነው። ይህ ስራ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰራው የድርሰቱ የመጀመሪያ አንቀፅ ነው። በዚህ አንቀፅ ላይ ዋናው ጉዳይ አይነሳም። መግቢያ አንቀፅ ወደ ወናው መልዕክት የሚወስደን ጥርጊያ ነው። ይህም በመሆኑ አንባቢያንን ወደ ቀጣጡ ክፍል ለማንደርደር መግቢያውን ማራኪና ውበት ለበስ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህን የምናደርገውም መግቢያውን በምሳሊያዊ ንግግሮች በአባባሎች በአጭጨር ሳቢ ጥቅሶች ወዘተ. ከሽነን በማቅረብ ነው። መግቢያ አንቀፅ የራሱ የሆነ ሀሳብ ስለማይኖረው የዋነኛ ዓረፍተነገርና የመዘርዘር ጣጣ ላይ ታይበት ይችላል።

ለ. ሀተታ፡- ይህ ክፍል የድርሰቱ ዋና ሀሳብ የሚተላለፍበት በመሆኑ በርከት ከት ባሉ አንቀፆች ሊገነባ ይችላል። አንቀፆቹም የየራሳቸውን ሀሳብ ያራምዳሉ። ይሁንና የየአንቀፆቹ ሀሳብ ትትስር የሚታይበት ሊሆን ይገባል። ሀሳቦቹን ለማስተሳሰርም አልፎ አልፎ መሸጋገሪያ አንቀፅን በመፅከላዊ ክፍል ውስጥ እንደ ሳጋ ማስገባት የተለመደ ነው። መሸጋገሪያ አንቀፆች የራሳቸው የሆነ የተለየ አሳብ አያነሱም። የሚስፋፋ ሀሳብ ስለማይቀርብባቸውም የሚገነቡት አብዛኛውን ጊዜ በሁለት ወይም በሶስት ዓረፍተ ነገሮች ነው። ማዕከላዊ ክፍል የድርሰቱ እንብርት ነው። ዋናውን ሀሳብ ተሸካሚ በመሆኑም በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን አንቀፆች እንደምናስተላልፈው ሀሳብ ስፋትና ጥበት ሁኔታ እያየን በወጉ መመጠንና ማከናበር ያስፈልጋል።

ሐ. መደምደሚያ፡- የድርሰት ሀሳብ በእንጥልጥል መቅረብ የለበትም፡፡ በማዕከላዊ ክፍል የቀረበው ዝርዝር ጉዳይ በመደምደሚያ ይቋጫል፡፡ እንደመግቢያ አንቀፅ ሁሉ አብዛኛውን ጊዜ በጥቂት ዓረፍተ ነገሮች የተገነባ አንድ አንቀፅ የድርሰት መደምደሚያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚህ አንቀፅ ላይ ቀደም ሲል ያልተወሳ አዲስ ሀሳብ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ይህም በመሆኑ በዋነኛ አረፍተ ነገርና ለመዘርዝር ትስስር ልንጨነቅ አይገባም፡፡ መደምደሚያ አንቀፅ በድርሰቱ ውስጥ የተነሱ አበይት ጉዳዮችን ሊያወሳ፣ ጭምቅ ሀሳብን ሊያቀርብ በአንባቢያን አዕምሮ ውስጥ ጥያቄን የሚያጭሩ ሀሳቦች ሊያስገባ ወዘተ ይችላል፡፡

ምንጭ ሰለሞን ሀለፎም የድርሰት አፃፃፍ ፣1997፣230-231)

## ክፍል አምስት ሰዋስው

### ሳቢና ኢሳቢ ግስ

❖ በዚህ ክፍል የድርጊት ግስችን የሚመለከት ይዘት ቀርቧል፡፡ የድርጊት ግስ ሳቢ ወይም ተሻጋሪ እና ኢሳቢ ወይም ኢተሸጋሪ ግስ ተብሎ እንደሚመደብ ከታች ያለውን ማስታወሻ በደብተራቸው ያፅፏቸው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎቹ የፃፉትን ማስታወሻ እንዲያነቡ ያድረጓቸው፡፡ በመጨረሻም ስለማስታወሻው ተማሪዎች ካነበቡት በተጨማሪ እርስዎ የማጠቃለያ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡

ማስታወሻ፡-

የድርጊት ግሶች

የድርጊት ግስ አንድን ነገር በራሱ ወይም በሌላ ነገር ላይ የሚፈፀመውን ድርጊት ወይም ተግባር የሚገልፅ የግስ አይነት ነው፡፡ የድርጊት ግስ ሳቢ አና ኢሳቢ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

ሀ. ሳቢ ግስ፡- ሳቢ ግስ የሚባለው ከተሳቢ ስም ጋር የሚዋቀር የግስ አይነት ነው፡፡ ሳቢ ግሶች ተሳቢ ይፈልጋሉ፡፡ ተሳቢውም ስም ወይም ተውላጠ ስም ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ግስ እና ስም (ተውላጠ ስም) ሳቢና ተሳቢ እየሆኑ ይዋቀራሉ፡፡

ምሳሌ1፡- በላ የሚለው ግስ ዳቦ ከሚለው ስም ጋር ይዋቀርና ዳቦ በላ ሰፋ ያለ መዋቅር ይፈጥራል፡፡ በዚህ መዋቅር ውስጥ በላ ሚለው ሳቢ ግስ ሲሆን ዳቦ የሚለው ስም የሱ ተሳቢ ነው፡፡ሳቢው ግስና ተሳቢው ስም ተዋቅረው የሚያስገኙት መዋቅር ሀረግ ሆኗል፡፡

ምሳሌ፡-2

ጠጣ የሚለው ግስ ወተት ከሚለው ስም ጋር ተዋቅሮ ወተት ጠጣ የሚል ሰፋ ያለ መዋቅር ፈጥሯል፡፡ በዚህ መዋቅር ውስጥ ጠጣ የሚለው ሳቢ ግስ ሲሆን ወተት የሚለው ስም ደግሞ ተሳቢ ነው፡፡፡

ለ. ኢሳቢ ግስ፡- ኢሳቢ ግስ  የድርጊት ግስ ነው፡፡ ይሁን እንጅ እንደ ሳቢ ግስ ከተሳቢ ስም እና ተውሳጠ ስም ጋር አይዋቀርም፡፡ በአጭሩ ተሳቢ አይፈልግም፡፡ በዚህ ምክንያት ብቻውን ወይም  ስም ካልሆነ ሌላ ቃል ጋር ይገኛል፡፡

ለምሳሌ፡- 1

ተኛ እና ወደቀ የሚሉትን ግሶች ብንመለከት የድርጊት ግሶች ናቸው፡፡ ነገር ግን የሚስቡት ወይም የሚጎትቱት  ስም የላቸውም፡፡ ሊኖራቸውም አይችልም፤ ምክንያቱም ሳቢ አይሉም፡፡ ነገር ግን ስም ካልሆኑ ሌላ ቃል ጋር  ሊገናኙ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ፡- 2.  ተራራ ላይ ወጣ፡፡

መሬት ላይ ወደቀ፡፡

በጥቅሉ ኢሳቢ ግሶች ተደራጊ አቻ የላቸውም፡፡ ስለዚህ ባላ ብለን ተባላ ማላት ስንችል ወጣ፤ ብልን ተወጣ  አንልም፡፡

- በማስከተል ከቀረቡላቸው ቃላት ውስጥ ሳቢ (ተሻጋሪ) ግስ እና ኢሳቢ(ኢተሻጋሪ) ግስ ሆኑትን ለይተው እንዲፅፉ ያግዟቸው፡፡ የሰሩትን እርዕስ በእርስ እርማት እንዲሰጣጡ ያድርጉና በተማሪዎች ዘንድ አከራካሪ የሆነ ነገር ከገጠማቸው በእርስዎ ዳኘነት ትክክለኛውን መልስ ያስረዷቸው፡፡
- በተግባር ሶስት ስር ከቀረቡት ቃላት ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን ነጣጥለው እንዲነቡ ይግለፁላቸው፡፡
- በመጨረሻም  ተነጣጥለው  ቀረቡትን  ምዕላዶች  አጣምረው  በመጻፍ  እንዲነቡ ያብራሩላቸው፡፡

## በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### ተግባር አንድ

ከሚከተሉት ግሶች  መካከል ሳቢ ግስ የሆኑትን ብቻ ለዩ፡፡

| | |
|---|---|
| ሰቀለ | ላከ |
| ሰበረ | ሸጠ |
| በጠሰ | መገበ |
| ቀደደ | ለበሰ |
| ሰጠ | ዓፈ |

### ተግባር ሁለት

ተግባር ሁለት ከሚከተሉት ግሶች መካከል ኢሳቢ ግስ የሆኑትን ብቻ ለዩ፡፡

ፈነዳ

ነደደ

ደከመ

ቀበጠ

ደመቀ

ቀጠነ

አየለ

ወፈረ

አኮረፈ

አለቀሰ

# ምዕራፍ ዘጠኝ (9)

## ባህላዊ ልማዶች

ክፍል ጊዜ 18

የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች

- ✓ የተስማሙበትን ሀሳብ ያቀርባሉ
- ✓ አጫጭር ምንባብ አንብበው ወደ ሰንጠረዥ ይቀይራሉ
- ✓ በቃል የሚነበብላቸውን አስተካክለው ይጽፋሉ
- ✓ ከርዕሱ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ
- ✓ ስርዓተ ነጥቦችን ጠብቀው ያነባሉ

የምዕራፉ አጠቃላይ ዝርዝር ይዘቶች

- ➢ አዳምጦ መመዘን
- ➢ ማንበብና ቃላዊ ዘገባ
- ➢ የማመልከቻ ጽሁፍ
- ➢ ሀላፊ ጊዜ ግስ

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

## ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት

### የትምርቱ አቀራረብ

- ❖ በዚህ ምዕራፍ ስር ያሉትን ተግባራት ከመጀመርዎ በፊት ስለይቅርታ የተጻፈ ግጥም ወይም ተረት ያቅርቡላቸው፡፡
- ❖ ከዚያም ስላዳመጡት ግጥም ወይም ተረት ጭብጥ ወይም መልዕክት ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ በዚህ ተግባር ተማሪዎቹን ካነቃቁ በኋላ የዕለቱን ትምህርት በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያዳመጡት ግጥም ወይም ተረት ከዕለቱ ትምህርት ርዕስ ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲገምቱ በማድረግ ወደ ዋናው ትምህርት ያስገቧቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎቹ ወደማዳመጥ ከመሄዳቸው በፊት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን በቃል ያሰሯቸው፡፡
- ❖ በአካባቢያቸው የሚያውቁት ባህላዊ የግጭት አፈታት ካለ እንዲናገሩ እድሉን ያመቻቹላቸው፡፡
- ❖ በሁለተኛ ደረጃ በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረበውን ምስል ተመልክተው የተረዱትን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በዚህ ሁሉ ተግባር ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠው ለማድመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በተገቢው ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡ በቅድሚያ ግን እያዳመጡ አዳዲስ ቃላትን እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

ሰዎች በጋራ ሲኖሩ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ግጭት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ የግጭቱ መጠን ይለያይ እንጂ፡ ሰዎች ባሉበት ቦታ ሁሉ ግጭት አይቀሬ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ግጭቱን በወቅቱ በማስወገድ ሰላማዊና ጤናማ ህይወት መምራት ተገቢ ነው፡፡ በሀገራችን ለረጅም ዘመናት ሲሰራባቸው የቆዩ ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች አሉ፡፡ ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ዘዴዎች የሚባሉት ቤተሰባዊ እርቅ፣ የዘመድ ዳኝነት፣ ሽምግልና እና አፈርሳታ ናቸው፡፡

በአንድ ቤተሰብ አባላት መካከል የሚፈጠር ግጭት በአብዛኛው በቤተሰብ አማካኝነት መፍትሄ ሊያገኝ ይችላል፡፡ በልጆች፣ በልጆችና በወላጆች፣በባልና በሚስት፣ በጎረቤት መካከል አለመግባባቶች ሲከሰቱ ቤተሰባዊ እርቅ ይካሄዳል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የአስታራቂነትና የአስማሚነት ሚና የሚኖራቸው እናት፣አባት፣ ወይም በዕድሜ ከፍ

ያሉ ልጆች ናቸው፡፡ ግጭቱ በባልና በሚስት መካከል ሲሆን ደግሞ በቅርብ የሚኖሩ የስጋ ዘመዶች ሊጠሩ ይችላሉ፡፡ ጎረቤቶቹም የሽምግልና ስራ ይሰራሉ፡፡ በዘመድና በጎረቤት ሊፈታ ካልቻለ የዘመድ ዳኛ ወይም ሽማግሌዎች እንዲያዩት ይደረጋል፡፡

ግጭቶች በዘመድ ዳኞች አማካኝነት ይረግባሉ፤ መፍትሄም ያገኛሉ፡፡ የዘመድ ዳኞች ለሁሉም ወገኖች የስጋ ዝምድና ያላቸው እድሜ ጠገብ አስታራቂ ናቸው፡፡ የዘመድ ዳኛ በጠበኞቹ ስምምነት ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ ከዚያም የሁለቱን ጠበኞች ቃል ተራ በተራ ያዳምጣሉ፡፡ ማብራሪያና ማስረጃም ይጠይቃሉ፡፡ ጉዳዩን በአግባቡ ከመረመሩ በኋላ ውሳኔ ይሰጣሉ፤ ለጉዳዩ ክብደትና እንደ ቅራኔው ክረት የዘመድ ዳኞች ሌሎች ዘመዶችን በመጨመር አብረው እንዲሽመግሉ ያደርጋሉ፡፡ ከመካከላቸውም አንድ ሰው መርጠው ጉዳዩን እንዲያስተናብር ያደርጋሉ፡፡

1. **ተማሪዎች እስካሁን ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ? የሽምግልና እና የአፈርሳታ የግጭት አፈታት እንዴት የሚከወን ይመስላችኋል?**

ሽምግልና ሌላው የግጭት ማስወገጃ ዘዴ ነው፡፡ ሽምግልና በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ግምትና ተቀባይነት ይሰጠዋል፡፡ የሽማግሌዎች አባላት በስነ-ምግባራቸውና በሚዛናዊነታቸው በአካባቢው ሰው ዘንድ አክብሮት ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ፡፡ ሽምግልና ብዙ ጊዜ በዕድሜ የገፉ ወይም በመካከለኛ ዕድሜ የሚገኙ ሰዎች ይወከሉበታል፡፡ ይሁን እንጂ ከዕድሜ ይልቅ ማህበራዊ ተቀባይነትን፣ችሎታና ተደማጭነትን ተመራጭ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ሽምግልና ግጭቱ ከሚመለከታቸው ወገኖች ገለልተኛነትን ስለሚጠይቅ ከዘመድ ዳኛ ይለያል፡፡ አንድን ግጭት ለመዳኘት ለሽምግልና የሚላኩ ሰዎች እንደጉዳዩ ክብደትና አስቸጋሪነት ሶስትና ከዚያ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሽምግልና ሂደት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጠበኞች በአንዳቸው አሳሳቢነት ሊጀመር ይችላል፤ ወይም ከጉዳዩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት በሌላቸው ገለልተኛ ሰዎች በሚቀርብ ጥያቄም ሊጀመር ይችላል፡፡ ሽምግልና አጥፊዎችን ይቀጣል፤ተበዳዮች እንዲካሱ ያደርጋል፤ እርቅንና ሰላምን ያመጣል፡፡

ሌላው ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ዘዴ አፈርሳታ ነው፡፡ አፈርሳታ ወይም አውጫጪኝ ማህበረሰብ በነቂስ ወጥቶ ወንጀለኛን የሚያውጣጣበት ሂደት ነው፡፡ አንድ ወንጀል ሲፈፀም የአካባቢው ነዋሪዎች ወንጀሉን አለመስማታቸው ወይም በሌላ ሰው ሲፈፀም አለማየታቸውን በመሀላ ያረጋግጣሉ፡፡ ዘመናዊ የወንጀል ምርመራ ባልነበረበት ወቅት ወንጀል ሲፈፀም አፈርሳታ የሚመሩ ሰዎች የአካባቢውን ኗሪዎች ይሰበስባሉ፡፡ ከተሰበሰበው ህዝብ ፈንጠር ብለውም ይቀመጣሉ፡፡ ከዚያም የአካባቢው ነዋሪዎች በተናጠል እየተነሱ ወንጀል የፈፀመውን አካል በሚስጢር ይጠቁማሉ፡፡ አፈርሳታውን የሚመሩት ሰዎችም የሚሰጣቸውን መረጃና ጥቆማ ትክክለኛነት በመስቀልኛ ጥያቄዎች

ያረጋግጣሉ። በመጨረሻም የጠቋሚዎችን ማንነት ሳይገልፁ ‹‹ ወንጀለኞችን ወፍ ነገረችን፤ ወንጀሉን የፈፀሙት እነገሌ ናቸው›› በማለት በህዝብ ፊት ያጋልጣሉ። ወንጀለኞቹ ይመከራሉ፤ይቀጣሉ።

በአጠቃላይ ቤተሰባዊ እርቅ፣ የዘመድ ዳኝነት፣ሽምግልና እና አፈርሳታ ሰዎች ግጭቶችን የሚፈቱባቸው ዘዴዎች ናቸው።ዘዴዎቹም ለረጅም ዘመናት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ብዙዎቹም አሁን እያገለገሉ ይገኛሉ። የተጣሉትን ለማስታረቅ፣የተበደሉትን እንዲካሱ ለማድረግ፣ በማህበረሰብ ውስጥ ሰላምና ፍቅር ለማስፈን ዘዴዎቹ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አላቸው። ስለሆነም በሳይንሳዊ መንገድ እየታገዙ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

ምንጭ አ.በ.ከ.መ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ። 2001 ዓ.ም የባህል ልማት መሰናክሎች ቅኝት ገፅ ከ80-82 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

- ❖ የማዳመጥ ተግባር ሲጠናቀቅ ለጻፉት አዳዲስ ቃላት ከራሳቸው መልስ እንዲሰጡ ያድርጉና መመለስ ያልቻሉትን እርስዎ ያስረዷቸው።
- ❖ በመቀጠል በተግባር ሁለት ስር የቀረበቡትን ጥያቄዎች በቃላቸው መልስ እንዲሰጡ በማድረግ በሰጡት መልስ ላይ ተጨማሪ ሀሳብ የሚያስፈልገው ጥያቄ ላይ እርስዎ ማብራሪያ ይስጡበት።
- ❖ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት በምንባቡ መሰረት ባላቸው ፍቺ በጽሁፍ እንዲሰጡ ይግለጹላቸው።
- ❖ የሰጡትን ፍቺ እንዲናገሩ በማድረግ በትክክል መመለስ መቻላቸውን ያረጋግጡ።መመለስ ያልቻሉት ጥያቄ ካለ መልሱን ያስረዷቸው።
- ❖ በሚማሩበት ትምህርት ቤት የሚያጋጥሙ ችግሮችን እንዴት እንደሚፈቱ የስነ ዜጋና ስነምግባር ክበብ ተጠሪዎችን አነጋግረው ማስታወሻ በመጻፍ በክፍል እንዲያቀርቡ ይግለጹላቸው።
- ❖ ጽፈው ያመጡትን የችግር አፈታት ሂደት በክፍል እንዲያነቡ ያድርጉን ለሙከራቸው የማበረታቻ ቃል በመጠቀም ያበረታቷቸው።
- ❖ በመጨረሻም ከዚህ ስር ተዘበራርቀው የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት አስተካክለው ዓረፍተ ነገር እንዲፅፉ ያንብቡላቸውና በትክክል መፃፍ አለመፃፋቸውን ይከታተሏቸው። ከዚያም እርሰዎ ትክክለኛውን መልስ ይንገሯቸው።

ሀ. ስርዓት መዳበር አለበት የዳኝነት በሀገራችን፡፡

ለ. በአግባቡ ነው የኮሮና እየተሰጠ ክትባት፡፡

ሐ. ውጤታማ ያጠና ተማሪ በአግባቡ ይሆናል፡፡

መ. ክህሎት ስልጠና ተሰጣቸው ለወጣቶች የህይወት፡፡

ሠ. ልዩ ድጋፍ ያስፈልጋል ለአካል ጉዳተኞች መስጠት፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሶስት

ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ተመሳሳይ ፍቺ ፃፉ፡፡

ሀ. ማስተባበር

ለ. አለመስማማት( ግጭት ውስጥ መግባት)

ሐ. ስምምነት

መ. ግጭቱ ይቀንሳል

ሠ. ውጥረት ( መባባስ)

ረ. ፍትሃዊነት

ሰ. ተሰሚነት

ሸ. ራቅ ብለው፣ነጠል ብለው

ቀ. ባህላዊ የወንጀለኛ መፈለጊያ

## ክፍል ሁለት ንባብ

- ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት በጥያቄና መልስ ያስታዉሷቸው፡፡
- የዕለቱን ትምህርት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው፡፡
- ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በማሰራት በቤተሰባቸው በየትኛው አጋጣሚ የድግስ መርሀ ግብር እንደሚዘጋጅ ይጠይቋቸው፡፡

- በቤተሰባቸው ወይም በአካባቢያቸው በድግስ ሰበብ ያጋጠመ ችግር ካለና ችግሩን ለማቃለል ምን ተግባር እንደተከናወነና በችግሩ ምክንያት የተከሰተውን ጉዳት ወይም ኪሳራ ምን እንደነበረ ይጠይቋቸው፡፡

- ተማሪዎቹ ካቀረቡት አጋጣሚ ምን ትምህርት እንዳገኙ እንዲናገሩ በማድረግ በማንኛውም የህይወት አጋጣሚ ልምድ ወይም ዕውቀት ማግኘት እንደሚቻል ያስገንዝቧቸው፡፡

- ድግስ ከማሰባቸው በፊት ምን ምን ጉዳይ ታሳቢ ማድረግ እንደሚገባ እንዲናገሩ ካደረጉ በኂላ በሶስቱም ጥያቄዎች የበለጠ ከምንባቡ መልስ ሊያገኙ እንደሚችሉ በመጠቆም ንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡

- ንባባቸውን ሲያጠናቅቁ በድህረ ንባብ ተግባር ሁለት ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል ያሰሯቸው፡፡

- በተግባር ሶስት ለቀረቡት ቃላት በ‹‹ ሀ›› ስር ላሉት በ‹‹ ለ ›› ከተዘረዘሩት በፍቺ የሚመሳሰሉትን እንዲያዛምዱ ይግለፁላቸው፡፡

- በተግባር አራት ስር የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል መልስ የሚሆነውን በመምረጥ እንዲመልሱ ያስረዷቸው፡፡

- ለጥያቄዎቹ የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ በዚህም በትክክል የመለሱትንና መመለስ ያልቻሉትን ይለዩ፡፡

- ለመለሱት ያበረታቷቸውና መመለስ ላልቻሉት ጥያቄ ምንባቡን መለስ ብለው እንዲቃኙ ያድርጉና ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ሙከራ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡ ካልሆ ግን እርስዎ ትክክለኛውን መልስ ያስረዷቸው፡፡

- በመጨረሻም ከላይ ከነበቡት ምንባብ ጋር ተያያዥነት ያለው ጽሑፍ እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

- የጻፉትን በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጉና ሙከራቸውን በማበረታታት ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ መሰጠት ያለበትን አስተያየት ይስጧቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሶስት

በ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት በፍቺ የሚስማሙትን ከ‹‹ለ›› ስር በመምረጥ አዛምዱ፡፡

1. መ
2. ረ
3. ለ
4. ሠ
5. ሀ
6. ሐ

ተግባር አራት

በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊድል በመምረጥ መልሱ፡፡

1. ሐ
2. ሀ
3. መ
4. መ
5. መ
6. መ
7. ሀ
8. ሐ

ክፍል ሶስት ቃላት

የቃላት መጥበቅና መላላት

- በቃል ትምህርት ስር ተማሪዎቹ ለፈሊጣዊ አነጋገር ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ፣ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚኖራቸውን ፍቺ የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር እንዲጽፉና ለቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡
- ፈሊጣዊ አነጋገር አንዱ ንግግርን ተደማጪነት እንዲኖረው ከሚያደርጉ ስልቶች አንዱ መሆኑን ይግለጹላቸው፡፡
- ፈሊጣዊ አነጋገር የተለያየ ፍቺ ካላቸው ሁለት ቃላት የሚፈጠር ሲሆን ቃላቱ በፊት ከነበራቸው ፍቺ ውጪ ሌላ ፍቺ እንዲሰጡ የሚደረግበት የአነጋገር ስልት መሆኑን ያስረዷቸው፡፡

ምሳሌ፡- ‹‹ ቅቤ ጠባሽ ››የሚለውን የሁለት ቃላት ቅንጅት ብንመለከት ስለ ቅቤ መጥበስ የሚናገር ሳይሆን እወደድ ባይነት ባህሪን የሚገልጽ ነው፡፡

❖ በዚህ መሰረት ስለ ፈሊጣዊ ንግግር ያስረዷቸው፡፡

❖ ፈሊጣዊ ሁል ጊዜ ጥምር ቃል ሊሆን እንደማይችልም አያይዘው ይግለጹላቸው፡፡

❖ አንድ ቃል ፈሊጥ ሊሆን እንደሚችል ቀጥሎ ባለው ምሳሌ መሰረት ይግለጹላቸው፡፡ ምሳሌ፡- ለዋሳ የሚለው ቃል ፈሊጥ ሲሆን አቅመ ቢስ የሚል ፍቺ ይኖረዋል፡፡

❖ በተግባር አንድ ስር ባሉት ፈሊጣዊ አነጋገር ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ይግለጹላቸው፡፡

❖ አንድ ቃል ሲጠብቅ ወይም ሲላላ የተለያየ ፍቺ እንደሚሰጥ በምሳሌ ያስረዷቸው፡፡

ምሳሌ፡- ሳታልሙ የሚለው ቃል ሲጠብቅ ኢላማ ሳታስገቡ

ሲላላ ሳታደቁ

❖ በተግባር ሁለት ስር ያሉትን ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ ሊኖራቸው የሚችለውን ፍቺ የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ሰርተው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡

❖ በመቀጠልም በተግባር ሶስት ያሉትን ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ሰርተው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡

❖ በመጨረሻም የሰሩትን የተማሪዎቹን ደብተር በማረም በትክክል መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡

❖ መመለስ ያልቻሉትን ማስተካከያ መልስ ይስጧቸውና እርማት እንዲወስዱ ያበረታቷቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች በምሳሌው መሰረት ፍቻቸውን በደብተራችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ሚስጥሩን ገልጦ አወያየ

ለ. ተረጋጋ

ሐ. ተቆጣ

መ. መሰከረ

ሠ. ሰማኝ፣አደመጠኝ

ረ. ወላዋይ፣በውሳኔው የማይፀና

ተግባር ሁለት

የሚከተሉትን ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚኖራቸውን ፍቺ በአረፍተ ነገር ውስጥ አሳዩ፡፡

ሀ. ወተት ሲጠብቅ መንከራተት

ሲላላ ከእንስሳ የሚገኝ የሚጠጣ

ለ. መዳር ሲጠብቅ ማግባት

ሲላላ ማጋባት

ሐ. መማር ሲጠብቅ ማወቅ፣ ዕውቀት ማግኘት

ሲላላ ይቅርታ ማድረግ

መ. ለጋ ሲጠብቅ መታ

ሲላላ ያልደረሰ

ሠ. ሳለ ሲጠብቅ እያለ

ሲላላ ስዕል መሳል፣ለጉንፋን መሳል

ረ. አያት ሲጠብቅ ተመለከታት

ሲላላ የአባት ወይም የእናት አባት እና እናት

## ክፍል አራት ጽሕፈት

ማመልከቻ

❖ መምህር በጽሕፈት ስር የቀረቡትን ተግባራት ከማከናወንዎ በፊት በመምህሩ መምሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረበውን የስርዓተ ነጥብ ማስታወሻ በደብተራቸው ያጽፏቸው፡፡

❖ ጽፈው ሲጨርሱ እያንዳንዱን ስርዓተ ነጥብ በምሳሌ እያስደገፉ በቂ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡

ማስታወሻ

የስርዓተ ነጥብ ምንነትና አይነቶች

የስርዓተ ነጥብ ምንነት

ስርዓተ ነጥብ ሀሳብን በፅሁፍ ለመግለፅ ያለው ድርሻ ከፍ ያለ ነው፡፡ በፅሁፍ ውስጥ መልዕክቱን በትክክል ለመረዳት እና የጽሁፍን አነባበብ ለመጠቆም ያገለግላል፡፡

የስርዓተ ነጥብ አይነቶች

በአማርኛ ቋንቋ በርካታ የስርዓተ ነጥብ አይነቶች ቢኖሩም የተወሰኑትን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

1. ነጠላ ሰረዝ(፣)፡- ነጠላ ሰረዝ ከሌሎቹ የስርዓተ ነጥብ አንፃር ሲተሳይ በርካታ አገልግሎት አለው፡፡

ሀ. በዓረፍተ ነገር ውስጥ ተመሳሳ ይሙያ የላቸው ድርድር ቃላት

ለያይቶ ለማስቀመጥ ያገለግላል፡፡

- ምሳሌ፡-በገበያ ውስጥሙዝ፣ብርቱካን፣ፓፓዬ፣መንደሪንና አናናስ ይሸጣሉ፡፡

ለ. በአረፍተ ነገር ውስጥ ተመሳሳይ ሙያ ወይም አቻዊነት የሚታይባቸውን ሀረጋት ለያይቶ ለማስቀመጥ ያገለግላል፡፡

- ምሳሌ፡-አሰፋአሮጌ ሱሪውን ታጥቆ፣በጥቁር ቀለም የተነከረ ነጠላአጣፍቶ፣የጠፍር ጫማ ተጫምቶ፣የሰሌን ኮፍያ አድርጎ፣ሚዶውን ከፀጉሩ ላይ ሰክቶና መፋቂያውን በጥርሱ ነከስ አድርጎይጓዝ ነበር፡፡

ሐ. በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ  የንባብ  ቆምታ መኖሩን ለመጠቆምይረዳል፡፡

- ምሳሌ፡- ቋንቋ፣የአንድ ማህበረሰብ የመግባቢያ መሳሪያ  ነው፡፡
- ባህል፣በአጭሩና በቀላሉ ሊገለፅ የሚችል ፅንስ ሀሳብ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

2. ድርብ ሰረዝ(፤)፡- ድርብ ሰረዝ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑና እራሳቸውን ችለው ሊቆሙ የሚችሉ ዓረፍተ ነገሮችን  አጣምሮ ለማቅረብ  የሚያገግል ነጥብ ነው፡፡

- ምሳሌ፡- በርቀት እንደተቀመጠ አያት፤ እሷም አይታው ነበር፡፡
- ቤቱ ቆርቆሮ ለብሷል፤ግርግዳው ተለስኗል፤ወለሉ ተነጥፏል፤ የቀረው ነገር አለ ማለት አይቻልም፡፡

3. ትምህርተ አንክሮ (!)፡-ትምህርተ አንክሮ ብዙ ጊዜ የአግራሞት፣ የቁጣ፣ የትዕዛዝግዴታ፣የደስታ ቃና ባዘሉ ስሜቶች ሀሳብን ለመግለፅ ሲፈለግ ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡፡

- ምሳሌ፡-ደግሞ ተነሳባቸው!
- ድህነት ቀንደኛ ጠላታችንነው!
- ወይ ጉድ! ምን አይነት ጣጣ ነው!

4. ትምህርተ ስላቅ( ¡ )፡- አንድን ሀሳብ በቀልድ፣በፌዝ፣በተሳልቆ ወይም በምፀት መግለፅ ሲያስፈልግ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

- ምሳሌ፡- አይ ቆመና እንዲህም ቆመና የለ¡
- የፅጉሯን ነገር አታንሳብኝ¡

5. ድርብ ትምህርተ ጥቅስ (‹‹ ››)፡- ይህ ስርዓተ ነጥብ በልቦለዳዊ ፅሁፎች ላይ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ እንግዳ ቃላትን ለመጠቆም፣ የሌሎች ሰዎችን መረጃ በጥቅስነት ሲወሰድ፣ የገፀባህሪትን ንግግር ለማስቀመጥ ያገለግላል፡፡

ሀ. አዳዲስ ቃላትንና የተውሶ ቃላትን ለማመልከት

- ምሳሌ፡- በሀመር ብሄረሰብ ዘንድ‹‹ኢቫንጋዲ›› የተሰኘ የወጣቶች የመዝናኛ ምሽት ዘወትር ይሄዳል፡፡

ለ. የገፀባህሪያትን ንግግር ለማሳየት

- ምሳሌ፡-‹‹ከቤታችን ያለው ካሴት  ይሄ ብቻ ነው››
- ‹‹ያልከውን አደረኩልህ እኮ››
- ‹‹ሌላ ቀይርልኝ ነው እምልህ››

ሐ. የሌላ ሰው ሀሳብን ወስደን ስንጠቀም ሀሳቡ የሌላ ሰው መሆኑን ለማሳየት፣

- ምሳሌ፡- ‹‹ከመጠምጠም መማር ይቅደም›› አሉ አበው፡፡

6. ነጠላ ትምህርተ ጥቅስ(‹ ›)፡- አንድ ሰው የተናገረውንሀሳብ ሶስተኛ ወገን ሲናገረው በነጠላ ትምህረተ ጥቅስ ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡

- ምሳሌ፡-የትምህርትቤታችን እርዕሰ መምህር ‹‹ወጣቶች! ትምህርት የችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ነው፤ሌኒን ‹መማርመማር አሁንም መማር› እንዳለው ሳትዘናጉ በርትታችሁ መማር ይኖሩባችኋል›› በማለት ለተማሪዎች አስገነዘቡ፡፡

❖ ማስታወሻውን በደንብ ከተረዱት በኋላ በተማሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን አንቀጽ እንዲያነቡ፣ ሲያነቡ የስርዓተ ነጥቦችን አነባበብ ጠብቀው በለሆሳስ እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡

❖ አንድ ጊዜ አንብበው ሲጨርሱ በድጋሜ በተራ በተራ ድምጻቸውን እያሰሙ እንዲያነቡ በማድረግ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅመው ማንበብ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

❖ ስርዓተ ነጥቡን ጠብቀው ማንበብ ካልቻሉ እርስዎ አንድ ጊዜ የአነባበብ ስልቱን ጠብቀው ያንብቡላቸው፡፡

❖ በድጋሜ የእርስዎን አነባበብ ስልት ተከትለው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

❖ በዚህ መልኩ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅመው ጽሁፍን እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ከተለማመዱ በኋላ በተግባረር ሁለት ስር ላለው አንቀጽ በባዶ ቦታው ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ እንዲያስገቡ ይግለጹላቸው፡፡

❖ በተግባር ሶስት ስር የቀረበውን የአዛምድ ጥያቄ ስርዓተ ነጥቦችን ከአገልግሎታቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያስረዷቸው፡፡

❖ ከዚያም የሰሩትን እንዲያቀርቡ ያድርጉና በትክክል መስራት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

❖ ማስተካከያ ለሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ይንገሯቸውና እርማት እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

❖ በመቀጠል የቀረበላቸውን ጽሁፍ ወደሰንጠረዥ እንዲቀይሩ ያስረዷቸው፡፡ ይህን ተግባር ሲተገብሩ በዓመተ ምህረት እና በቁጥር የቀረቡትን እንዴት መፃፍ እንዳለባቸው ምሳሌ ይስጧቸው፡፡

❖ የጻፉትን የእያንዳንዱን ተማሪ ተግባር ተመልክተው በትክክል መስራታቸውን ይፈትሹ፡፡

❖ በመጨረሻም በመምህሩ መምሪያ ላይ ያለውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ለይ ይጻፉላቸውና እነሱ ከሰሩት ጋር እንዲያስተያዩ ያድርጉ፡፡

❖ ሲያስተያዩ የሰሩትን ስህተት ለይተው እንዲያወጡ ይግለጹላቸው፡፡ ስህተታቸውን ከለዩ በኋላ ማስተካከያ እንዲወስዱ ያበረታቷቸው፡፡

❖ ስለ ደብዳቤ የቀረበውን ማስታወሻ በደብተራቸው ያጽፏቸውና በጥያቄና መልስ ያስረዷቸው፡፡

የደብዳቤ አይነቶች

ደብዳቤ እንደይዘቱና አላማው በርካታ ቢሆኑም የመስሪያ ቤትና የግለሰብ ደብዳቤ ተብሎ ሊከፈል ይችላል፡፡፡ የግለሰብ ደብዳቤ የሚባለው ግለሰብ ለግለሰብ፣ወዳጅ ለወዳጁ፣ ጓደኛ ለጓደኛው ናፍቆታቸውን ለመግለፅ መረጃ ለመለዋወጥና ጥሪ ለማድረግ ሲባል የሚፃፍ ነው ፡፡ የመስሪያ ቤት ደብዳቤ የምንለው ደግሞ በስራ ዓለም ውስጥ ስራ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ለመፈፀምና ለማስፈፅም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና መሰሪያ ቤቶች በተጨማሪ ድርጅቶች ርእስ በእርስ ሀሳብ፣መመሪያና ትዕዛዝ የሚለዋወጡበት ነው፡፡ በዚህ የደብዳቤ አይነት መስሪያ ቤት ከመስሪያ ቤት፣ድርጅት ለድርጅት፣መስሪያ ቤት ለግለሰብ፣ እንዲሁም ግለሰብ ለመስሪያ ቤት ከላይ ወደታች ወይም ከታች ወደላይ ሊፃፍ ይችላል፡፡

የመስሪያ ቤት ደብዳቤና የግለሰብ ደብዳቤ አንድነትና ልዩነት

| የመስሪያ ቤት ደብዳቤ | የግለሰብ (የወዳጅዘመድ ደብዳቤ) |
|---|---|
| • በመደበኛ ቋንቋ አጠቃቀም መፃፍ አለበት፡፡<br>• በፊደላት፣በቃላት፣በሀረጋት ግድፈት ምክንያት ችግር ወይም አለመግባባት ስለሚከሰት ከፍተኛ ጥኝቃቄን ያስፈልጋል፡፡<br>• ቁጥር፣ ቀን፣ ማህተም፣ የባለስለጣኑ፣ ፊርማ እና የስራ ሃላፊነት መፃፍ አለበት፡፡<br>• የላኪ አድራሻ፣ የተቀባት አድራሻ፣ መግቢያ ሀተታና መደምደሚያ አይቀሬ ናቸው፡፡<br>• እንደሁኔታው ደብዳቤው በፖስታ ቤት አልያም በሰው ሊላክ ይኖራል፡፡<br>• ህጋዊነቱን ለማረጋገጥ ቴንበር የራስጌ ማህተም፣ የግርጌ ማህተም፣ ግልባጭ ይኖራል፡፡ | • እንደ ግለሰቦቹ ቀረቤታ በኢመደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ሊፃፍ ይችላል፡፡<br>• በፊደላትና በቃላት አጠቃቀም ችግር ምክንያት የከፋ ችግር አይከሰትም፡፡<br>• እንደአስፈላጊነቱ ቀን እና ፊርማ ሊቀመጥ ይችላል ነገር ፣ግን ቁጥር፣ማህተምና የስራ ሀላፊነት ላያስፈልግ ይችላል፡፡<br>• የላኪ፣ የተቀባይ አድራሻ፣ መግቢያ ሀተታና መደምደሚያ እንደአስፈላጊነቱ ሊገባ ይችላል፡፡ በግለሰብ ወይም በፖስታ ሊላክ ይችላል፡፡<br>• ግልባጭም፣ቴንብርም ሆነ ማህተም አያስፈልግም፡፡ |

- ❖ ስለደብዳቤ የቀረበውን ማስታወሻ መረዳት መቻላቸውን በቃል ጥያቄ በመጠየቅ ያረጋግጡ፡፡
- ❖ በተማሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የማመልከቻ ደብዳቤ ምሳሌ በደንብ አንብበው እንዲረዱት ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ስለሚያጋጥሙ ችግሮችና ችግሩን ለማቃለል ወይም ለማስቀረት የተደረገውን ጥረት ከስነ ዜጋና ስነ ምግባር ክበብ ተጠሪዎች ጠይቀው ማስታወሻ በመጻፍ በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡ያለባቸውን አስተያየት ይስጧቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር ሶስት

ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀፅ በትክልል በማንበብ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በባዶ ቦታው ውስጥ አስገብታቸሁ ፃፉ፡፡

1. አራት ነጥብ
2. ነጠላ ሰርዝ
3. ነጠላ ሰረዝ
4. ነጠላ ሰረዝ
5. አራት ነጥብ
6. አራት ነጥብ
7. ቅንፍ
8. አራት ነጥብ
9. አራት ነጥብ
10. ትዕምርተ ጥቅስ

ተግባር አራት

በ‹‹ሀ›› ስር የቀረቡትን የስርዓተ ነጥብ አይነቶች በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘተሩት የስርዓተ ነጥብ አገልግሎት ጋር የሚስማሙትን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

1. ሐ
2. ሠ
3. ለ
4. ረ
5. መ
6. ሀ

ተግባር አምስት

ከዚህ በታች ያለውን ምንባብ በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ወደ ሰንጠረዥ ቀይራችሁ ፃፉ፡፡

| የደን ስርጭት በኢትዮጵያ በስኩየር ኪሎ ሜትር 1973 -1990ዓ.ም | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የደን አይነቶች | ከ1973 — 1976 ዓ.ም | | 1986 — 1990 ዓ.ም | |
| | ስደት ስ.ኪ.ሜ | የደን ስፋት በመቶኛ | ስፋት ስ.ኪ.ሜ. | የደን ሽፋን በመቶኛ |
| ጠቅጥቅ ደን | 30243 | 2.64 | 2346 | 0.2 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በከፍተኛ ደረጃ የተመናመነ ደን | 10009 | 0.87 | 35243 | 3.08 |
| ጠቅላላ | 54410 | 4.75 | 45055 | 3.93 |

## ክፍል አምስት ሰዋስው

የሃላፊ ጊዜ

- ❖ ከዚህ በፊት ስለሀላፊ ጊዜ የተማሩትን በጥያቄና መልስ ክልሳ ያድርጉላቸው፡፡ በተግባር አንድ ላይ ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በሀላፊ ጊዜ የተጻፉትን ለይተው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም በተግባር ሁለት ስር በቀረቡት የሀላፊ ጊዜ ግሶች ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻ የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል የሀላፊ ጊዜ ድርጊትን ከአሁን እና ከወደፊት ጊዜ መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ❖ ማስተካከያ መስጠት የሚያስፈልገው ካለ ያስረዷቸውና አስተካክለው እነዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባት አንድ

ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በሃላፊ ጊዜ የተመሰረቱትን ለይተችሁ አውጡ፡፡

ሀ. ልጁ የተዋሰውን መጽሐፍ ባለፈው ሳምንት መለሰ፡፡

መ. ባለፈው ዓመት የቆሸሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ተቆፍሮ ነበር፡፡

ሠ. እንግዳው ትናንት ማታ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

ሰ. ባለፈው ዓመት ውድድሩን ያሸነፈው የኔ ፈረስ ነበር፡፡

# ምዕራፍ አስር(10)

## ሴቶችን ማብቃት

ክፍለ ጊዜ 18

የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች

- ✓ የተሰማቸውን ምክንያታዊ ሆነው ይገልፃሉ
- ✓ አስተካክለው ያነባሉ
- ✓ የሰው ህይወት ታሪክ ይጽፋሉ
- ✓ ስርዓተ ነጥቦች ያላቸውን አገልግሎት ተረድተው ያነባሉ
- ✓ ርዕቱና ኢርቱዕ ዓረፍተ ነገሮችን ይጠቀማሉ

አጠቃላይ ይዘቶች

- ➢ ማዳመጥና ፅብረቃ
- ➢ የህይወት ታሪክ ማንበብና መፃፍ
- ➢ ቅጥያዎችን ማጣመር
- ➢ ርቱዕና ኢርቱዕ

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

‹‹ሀልመኛዋ ወጣት››

### የትምህርቱ አቀራረብ

❖ እባክዎ መምህር በዕለቱ የሚደመጠውን ምንባብ ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው፡፡ ከዚያም በቅድመ ማዳመጥ ስር ያሉትን ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲሰሩ ይግለጹላቸው፡፡

❖ በመጀመሪያ እጃቸውን እያወጡ የሚመልሱ ካሉ እድሉን ይስጧቸውና እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም እጃቸውን ያላወጡ ተማሪዎችን በስም እየጠሩ ለጥያቄዎቹ መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

❖ ጥያቄ ‹‹ሀ››ን ሲሰሩ ስዕሉ ስለምን እንደሚገልጽ እንዲገምቱ ይጠይቋቸውና ለሚሰጡት የተለያየ መልስ ምክንያት እንዲሰጡ ይጠይቋቸው፡፡

❖ ወደጥያቄ ‹‹ ለ ›› ሲሄዱ ርዕሱንና ምስሉን እያነፃፀሩ ያላቸውን ግንኙነት እንዲገምቱና የተረዱትን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

❖ ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያለው ታሪክ በአካባቢያቸው ወይም በቤተሰባቸው የሚያውቋቸው ስኬታማ ሴቶች ካሉ የስኬታማነታቸው ምስጢር ምን እንደሆነ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያድርጉና ለሰጡት ምላሽ አመስግነው ወደምንባቡ ያምሩ፡፡

❖ በማዳመጥ ጊዜ የሚያዳምጡትን ታሪክ የድርጊት ቅደም ተከተል እየለዩ በማዳመጥ በመማሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ባዶ ቦታ እንዲሞሉ ያስረዷቸው፡፡

❖ ለማዳመጥ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጡና ለማድመጥ የቀረበውን ምንባብ ያንብቡላቸው፡፡

❖ መሀል ላይ ንባበዎትን ገታ ያድርጉና የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን እስካሁን ካዳመጡት ታሪክ ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው፡፡

❖ በመቀጠል ባለታሪኳ በመጨረሻ ምን ደረጃ ላይ እንደምትደርስ እንዲገምቱ ያበረታቷቸው፡፡

ወርቅነሽ ትባላለች፤ ተወልዳ ያደገችው በሀገራችን ካሉት የገጠር መንደሮች መካከል በአንዱ ውስጥ ነው። ባደገችበት ማህበርሰብ ዘንድ ሴትን ልጅ ማስተማር የማይታሰብ ስለነበር እሷም የዚሁ እጣ ፈንታ ተቋዳሽ ነበረች። ሰባት ልጆችን ለወለዱት ቤተሰቦቿ ሶስተኛ ልጅ ስትሆን የቤቱን ስራ በመስራት የሴትነት ግዴታዋን ትወጣለች።ሁለቱ ታላላቆቿ ወንዶች በመሆናቸው ሁሉንም የቤት ስራ ጠቅልላ ስለምተሰራ ከፍተኛ የስራ ጫና ነበረባት። ወንድሞቿ እህታቸውን የሚወዷት ቢሆኑም የቤቱን ስራ እንዳያግዟት ባህላቸው አይፈቅድላቸውም ነበር።

ወርቅነሽ እንደወትሮዋ ቤተሰቦቿንም ሆነ እህት ወንድሞቿን ዘወትር ታደርገው እንደነበረው ከማገልገል ይልቅ ለብቻዋ ሆና ማሰብ ጀመረች። ሁኔታዋ ያላማራቸው ቤተሰቦቿ ምን እንደሆነች በተራ ጠየቋት። እሷ ግን ታስብ የነበረው ከወር በፊት የእናቷ ታናሽ እህት ዘመድ ጥየቃ መጥታ ስለመከረቻት ነገር ስለነበር ምን እያሷት እንደነበር እንኳ አላዳመጠቻቸውም ነበር። የት ሄድሽ ልጄ! ሲላት አባቷ እንደመባነን ብላ ወደ አክስቴ መሄድ እፈልጋለሁ። ዘመናዊ ትምህርት አስተምርሻለሁ ብላኛለች፤እናንተ የማትፈቅዱልኝ ከሆነ ግን ጠፍቼ መሄዴ አይቀርም አለቻቸው። ቤተሰቦቿም በሰሙት ነገር ቢደነግጡም ጥያቄዋን ግን ወደ ጎን ማለት አልፈለጉም። እናቷም ከእህቷ ጋር በስልክ ከተነጋገረች በኋላ ወደ አዲስ አበባ ከሚመጣ ሰው ጋር ላከቻት።

ወርቅነሽ አዲስ አበባ ከአክስቷ ቤት እንደደረሰች ከተማውን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትመለከተው በቀላሉ የምትለምደው ስላልመሰላት ፍራት ፍራት ብሏት ነበር። አክስቷም ሁሉንም ነገር ስታሳያት ሰንብታ ትምህርት ቤት ሲከፈት አንደኛ ክፍል አስመዘገበቻት። ዕድሜዋ ተላልፏት ስለነበር በክፍል ካሉት ተማሪዎች ትልቋ እሷ ብቻ ነበረች። ትምህርት እንደተጀመረ አካባቢ አርፍዳ ወደ ክፍል ስትገባ የክፍሏ ተማሪዎች አስተማሪ እየመሰለቻቸው ከመቀመጫቸው ይነሱላት ነበር። እንደነሱ ተማሪ መሆኗን ሲያውቁ ይስቁባት ነበር። እሷ ግን በማን እንደሚስቁ ስለማትረዳቸው ዝም ትላቸዋለች።

ወርቅነሽ የተለያዩ መሰናክሎች ቢያጋጥሟትም ሁሉንም ነግር እንዳመጣጣቸው ተቋቁማ በጥሩ ውጤት እየታጀበች አስረኛ ክፍል ደረሰች። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን በምትከታተልበት ወቅት ሁሌም አንደኛ ስለምትወጣ ሁሉንም ሰው ታስደስት ነበር። በሚኒሚዲያ ክበብ አማካኝነት ድራማ፣ ጭውውት፣ ግጥምና መነባንብ በማቅረብ ምርጥ ብቃቷን ማስመስከር ችላለች። በተለይ ያደገችበትን ማህበረሰብ አለባበስና አነጋገር በመወከል ድራማ ስታቀርብ ሁሉም ተማሪዎች በአድናቆት ይከታተሏት ነበር። በዚህም በአስተማሪዎቿ ዘንድ የምትወደድ ልጅ ነበረች። በጥንካሪዋ፣በውጤቷና በስነምግባሯ ለሌሎች ሴት እህቶቿ እንደምሳሌ የምትጠቀስ ነበረች። ወደፊት ትምህርቷን ስትጨርስ ምን መሆን እንዳለባት የወሰነችውም ገና የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እያላች

ነበር። ያደገችበትም ማህበረሰብ እንዴት መርዳት እንደምትችል ዕቅድ አውጥታ ነበር።

1. እስካሁን ካዳመጣችሁት ፅሁፍ ምን ተረዳችሁ?
2. ወርቅነሽ ወደፊት ትምህርቷን ስትጨርስ ምን የምትሆን ይመስላችኋል?

ወርቅነሽ የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናዋን ወስዳ በትምህርት ቤቱ ከሁሉም የተሻለ ውጤት አስመዘገበች። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ስለደረሳት በጣም ተደሰተች። ዩንቨርሲቲ እንደገባች የተመኘችውን የጋዜጠኝነት ትምህርት በማጥናቷ በራስ መተማመኗን ጨመረላት። ከሁለት ወር በኋላ በእሷ አስተባባሪነት በዩንቨርሲቲው ውስጥ ሳምንታዊ የስነ-ፅሁፍ ምሽት እንዲመሰርት አደረገች። በተቋቋመው ክበብም በርካታ ሴቶችና ወንዶች እውቀታቸውን ማዳበር ጀመሩ። በምታቀርባቸው ግጥሞች መነባንቦች፣ ወጎች ስለሴቶች ብቃት ታቀርብ ስለነበር በርካታ ሴቶች የእሷን መንገድ መከተል መጀመራቸው የበለጠ እንድትሰራ ያድርጋት ነበር። ወርቅነሽ በግቢ ቆይታዋ በትምህርቷ ከሁሉም ተማሪዎች ጋር እየተወዳደረች በጥሩ ውጤት በዋንጫ ተመረቀች። ያሳደገቻት አክስቷም ኮራችባት።

በመጨረሻም ሀገሪቱ ውስጥ ካሉት ስመጥር የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በአንደኛው ተወዳድራ የጋዜጠኝነት ስራዋን በመስራት ጀመረች። በአጭር ጊዜ በስራዋ እውቅናን እያገኘች መጣች። ያገኘችውን እውቅና በመጠቀም መንግስትንና ባለሀብቶችን አቀናጅታ ተወልዳ ባደገችብት አካባቢ ደረጃውን የጠበቀ አንድ ትምህርት ቤት ማስገንባት ቻለች። የእሷ እኩያዎች ያጡትን የትምህርት እድል ታናናሾቿ እንዲያገኙ ማድረግ ቻለች። ሌሎች ተጨማሪ ትምህርት ቤቶችን ለማስገንባት እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች።

- የማዳመጥ ጊዜ ሲጠናቀቅ እያዳመጡ የሞሉትን ጥያቄ ምን ያህሉ ተማሪ አጠናቆ እንደሞላ፣ምንያ ህሉ ደግሞ በከፊል ወይም ደግሞ ያልሞሉትን ጥያቄ እንዲናገሩ ያድርጉ።
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡ በድጋሜ መነበብ እንዳለበትና እንደሌለበት እርስዎ ይወስኑ።
- ማለትም አብላጫው ተማሪ ባዶ ቦታውን መሙላት ከቻለ በድጋሜ ሳያነቡ በባዶ ቦታው የሚገቡትን ቃላትና ሐረጋት ከመምህሩ መምሪያ መጽሐፍ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያላሟሉት ተማሪዎች እየመረጡ እንዲያሟሉ፣ አሟልተው የጻፉት ደግሞ የሰሩትን እንደገና ተመልሰው እንዲያዩት በማድረግ ሁሉንም ተማሪዎች በሚያሳትፍ መልኩ ተግባሩን ያከናውኑ።

❖ አብዛኛው ተማሪ ባዶ ቦታውን አሟልቶ ካልጻፈ ግን ምንባቡን በድጋጋሚ ማንበቡ የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡

❖ በተግባር ሶስት ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በቅድሚያ እንዲወያዩባቸው ጊዜ ይስጧቸው፡፡

❖ በመቀጠል የተወያዩበትን ሀሳብ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

❖ በመጨረሻም ከቀረበላቸው ምንባብ ምን ቁም ነገር እንዳገኙ ተወያይተው በክፍል ውስጥ በተራ በተራ ንግግር እንዲያደርጉ ያስረዷቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ፡፡

መምህራችሁ‹‹ህልመኛዋ ወጣት›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ የድርጊት ቅደም ተከተሉን በጥሞና በማዳመጥ ባዶ ቦታውን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. የሴትነት ግዴታዋን

ለ. እንደወትሮዋ

ሐ. እንደመባነን

መ. ተላልፏት

ሠ. መሰናክል

ረ. አቀናጅታ

## ክፍል ሁለት ንባብ

❖ በክፍል ሁለት ንባብ ክሂልን ለማስተማር የቀረበውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት በርዕሱ ስር ያሉትን ፎቶግራፎች ተመልክተው በስዕሉ የቀረቡት ሴቶች በምን ተግባር እንደሚታወቁ ይጠይቋቸው፡፡

❖ የተማሪዎቹን ግምት መነሻ በማድረግ ሎሬት የትነበርሽ ንጉሴ የህግ ባለሙያ እና የአካል ጉዳተኛ መብቶች ተሟጋች እንደሆነች፣ እ.ኤ.አ. 2017 የአካል ጉዳተኞች መብቶች እና ማካቶችን በማስተዋወቅ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የአእምሮ ውቅርን መለወጥ በሚያበረታታ ስራዋ ‹‹ራይት ላይቭሊሁድ አዋርድን›› ሽልማት ያገኘች አይነስውር ጀግና ሴት መሆኗን፣

❖ ክብርት ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ሴት ፕሬዝዳንት እና ለሀገራቸው ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ የሰሩ እንደሆኑ፣

❖ ፓይለት አምሳለ ጓሉ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ሴት አውሮፕላን አብራሪ መሆናቸውን ያብራሩላቸው፡፡

- ❖ በመቀጠልም በሀገራችን ስኬታማ የሆኑ ሴቶች ቁጥር አናሳ የሆነበትን ምክንያት እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በተግባር ሁለት ስር የቀረቡትን ቃላት አጣምረውና ነጥለው እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ በመነጠልና በማጣመር አንብበው ሲያጠናቅቁ ምንባቡን ጥንድ ጥንድ ሆነው ድምፃቸውን ሳያሰሙ እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ ሲያነቡ ዋናና ዝርዝር ሀሳቡን እየለዩ እንዲያነቡ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ የማንበብ ተግባሩን ሲያጠናቅቁ በተግባር ሶስት ስር የቀረበውን የእውነት ሐሰት ጥያቄ መልስ እንዲሰጡና ለመልሳቸው ምክንያት እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በተግባር አራት ስር ለቀረቡት ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ የሰጡትን መልስ በተራ እየወጡ በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲጽፉ ያድርጉና እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያበረታተዋቻ፡፡
- ❖ በመጨረሻም ማስተካከያ መልስ የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ እርስዎ ያስረዷቸውና የተሰጣቸውን እርማት እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አራት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቻቸውን ጽፋችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. እንዲረጋገጥ

ለ. ሰነዶች

ሐ. ቁርኝት

መ. አስተዋጽዖ

ሠ. ምሳሌ

ረ. ማበልፀግ

ሰ. ተቋማት

## ክፍል ሶስት ቃላት

### ቃላትን በምዕላድ መከፋፈል

- ❖ ከዚህ በፊት የቃላት ተቃራኒና ተመሳሳይ ፍቺ መማራቸውን ያስታውሷቸው፡፡
- ❖ ምን ያህል እንደሚያስታውሱ በጥያቄ ይፈትሹና በተግባር አንድ ስር ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ የሰጡትን ምላሽ እንዲናገሩ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ❖ ማስተካከያ የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ መልስ ይንገሯቸውና ትክክለኛ መልስ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ❖ በተግባር ሁለት ጥምር ቃል ለመመስረት የቀረቡትን ተጠቅመው ጥምር ቃል እንዲመሰርቱ ከማድረግዎ በፊት ስለ ጥምር ቃል ምንነት ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- ❖ ጥምር ቃል የተለያየ ፍቺ ካላቸው ሁለት ቃላት የሚመሰረት ሲሆን ጥምር ቃሉ ከተመሰረተ በኋላ የሚኖረው ፍቺ ሁለቱ ቃላት ቀድሞ ከነበራቸው ፍቺ ውጪ እንደሆነ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ ጥምር ቃል ቀደም ብሎ ከተማሩት ከፈሊጣዊ ንግግር ጋር ያለውን ግንኙነትና ልዩነት ይንገሯቸው፡፡ ጥምር ቃል የሚኖረው ፍቺ ፊት ለፊት ሲሆን የፈሊጣዊ አነጋገር ቃል ፍቺ ግን ከፊት ለፊት ፍቺ ያለፈ እንደሚሆን፣
- ❖ ጥምር ቃል ሁል ጊዜ የሁለት ቃል ውጤት ሲሆን ፈሊጥ ግን ጥምር ቃል ብቻ እንዳልሆነ፣ በቃል ደረጃ ሊገኝ እንደሚችል ባለፈው ስለፈሊጣዊ አነጋገር የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ስለጥምር ቃል ከተረዱ በኋላ በተግባር ሁለት በቀረበው ጥምር ቃል እንዲመሰርቱ፣ ለመሰረቱት ጥምር ቃል ፍቺ እንዲሰጡ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ የመሰረቱትን ጥምር ቃልና የሰጡትን ፍቺ እየወጡ በጥቁር ሰሌዳ እንዲጽፉ ያድርጉና እርስ በርሳቸው እንዲተራረሙ ያግዟቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም ማስተካከያ የሚያስፈልገውን ይለዩና ትክክለኛ መልስ ይስጧቸውና እንደገና አስተካክለው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ለተሰመረባቸው ቃላት ትክክለኛ ፍቺ የያዘውን ፊደል እየመረጡ መልስ እንዲሰጡ ያስረዷቸው፡፡

- ❖ በተግባራቱ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሰጡትን መልስ እንዲናገሩ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ።
- ❖ በትክክል ያልተመለሰ ጥያቄ ካለ ትክክለኛውን መልስ ይጻፉላቸውና አስተካክለው እንደገና እንዲጽፉ ያድርጉ።
- ❖ በተግባር አራት ስር የቀረቡትን ቃላት ከዚህ በፊት በተማሩት መሰረት ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይተው እንዲጽፉ ያስረዷቸው።
- ❖ የሰሩትን በተራ በተራ እየወጡ በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲጽፉ በማድረግ እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያግዟቸው።
- ❖ በመጨረሻም በተማሪዎች ያልተመለሰ ጥያቄ ካለ እርስዎ ያስረዷቸውና እንዲያስተካክሉ ያበረታቷቸው።

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ተግባር አንድ

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ሚዛናዊ

ለ. ምናብ

ሐ. መቃረን

መ. ጉስቁልና

ሠ. ውርደት

ረ. አደባባይ

ሰ. ብዙ፣ በርካታ

ተግባር ሶስት

የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1. ሀ
2. ሐ
3. ሐ
4. መ
5. ሀ
6. መ

ክፍል አራት ጽሕፈት

የህይወት ታሪክ

❖ በዚህ ትምህርት ክፍል ስር በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ በደብተራቸው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

❖ ጽፈው ሲያጠናቅቁ በጥያቄና መልስ ያስረዷቸው፡፡ ያልገባቸው ካለ እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው፡፡ ላቀረቡት ጥያቄ በቂ ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡

❖ በተማሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የጳውሎስ ኞኞ የህይወት ታሪክ ደቂቃ ይያዙላቸው፣

❖ ሲያነቡ የስርዓተ ነጥቦችን አነባበብ ስልት ጠብቀው እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡

❖ አንብበው ሲያጠናቅቁ የቀረበውን ምንባብ በተያዘላቸው ደቂቃ አንብበው ማጠናቀቃቸውን ይፈተሹ፡፡

❖ በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን ስርዓተ ነጥቦች ተከትለው በትክክል ማንበብ መቻላቸውን ለመፈተሽ በድጋሜ በተራ በተራ ድምጻቸውን እያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

❖ በዚህም ስርዓተ ነጥቦቹን በትክክል ማንበብ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

❖ ተማሪዎቹ በትክክል ማንበብ ከቻሉ ጥሩ ካልሆነ ግን እርስዎ በአርአያነት ያንብቡላቸውና የእርስዎን ስልት ተከትለው ማንበብ እንዲለማመዱ ያበረታቷቸው፡፡

- በመቀጠል በቡድን ይመድቧቸውና በቡድናቸው ከላይ ያነበቡትን የህይወት ታሪክ አወንታዊና አሉታዊ ጎን ላይእንዲወያዩ ይግለጹላቸው፡፡
- ተወያይተው ያገኙትን አወንታዊና አሉታዊ ጎን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ባቀረቡት ሀሳብ ላይ በመነሳት ተማሪዎቹ የጽሑፉን አወንታዊና አሉታዊ ጎን መለየት መቻላቸውን ይፈትሹ፡፡
- ላቀረቡት ሀሳብ ማበረታቻ ቃል በመጠቀም ያበረታቷቸውና ተጨማሪ ወይም መስተካከል ያለበት ሀሳብ ካለ በአስተያየት መልክ ያብራሩላቸው፡፡
- እስካሁን በተማሩት የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ መሰረት የግለሰብ የህይወት ታሪክ ሲጻፍ ሊካተቱ የሚገባቸውን ነጥቦች በቢጋር መልክ እንዲያዘጋጁ ያስረዷቸው፡፡
- ያዘጋጁትን ቢጋር በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጉና ማስተካከል ያለባቸውን ነጥብ እንዲያስተካክሉ ያግዟቸው፡፡
- ባዘጋጁት ቢጋር አንድ ሰው የህይወት ታሪክ መጻፍ እንዲለማመዱ ይግለጹላቸው፡፡
- በመለማመጃነት የጻፉትን የህይወት ታሪክ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉና ለሙከራቸው ማበረታቻ ቃል በጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠል ማስተካከል ያለባቸውን አስተያየት ይስጧቸው፡፡
- በቀጣይ የሚያውቁትን አንድ ሰው የህይወት ታሪክ ጽፈው እንዲመጡ ይግለጹላቸው፡፡
- የጻፉትን የህይወት ታሪክ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ በማድረግ ተማሪዎቹ የህይወት ታሪክ መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በጻፉት የህይወት ታሪክ ያሳዩትን ጠንካራ ጎን እና መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች ያስረዷቸው፡፡
- መምህር ተማሪዎቹ የህይወት ታሪክ አፃፃፍ ልምምዳቸውን አጠናክረው እንዲሄዱ በድጋሜ የራሳቸውን የህወት ታሪክ እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

## ክፍል አምስት ሰዋስው

### ርቱዕና ኢርቱዕ

- ❖ በዚህ ስር ተማሪዎች ርቱዕና ኢርቱዕ ግስን እንዲለዩ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ በተግባር አንድ ስር ከተዘረዘሩት ግሶች ውስጥ ርቱዕና ኢርቱዕ በማለት ለይተው በሰንጠረዥ ውስጥ እንዲጽፉ በምሳሌ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ የጥያቄውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ እነሱ ከሰሩት ጋር አነፃፅረው ስህተታቸውን እንዲለዩ ያግዟቸው፡፡
- ❖ ለፈጸሙት ስህተት ማስተካከያ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡
- ❖ በርቱዕ የቀረቡትን ግሶች ወደኢርቱዕ እንዲለውጡ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ በተግባር ሶስት በቀረቡት ግሶች ርቱዕና ኢርቱዕ ተግባርን የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች እንዲሰሩ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ የተማሪዎቹን ደብተር በመሰብሰብ ያርሙና በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡ እርማት የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ እርማት ይስጧቸውና አስተካክለው እንዲጽፉ ያበበረታቷቸው፡፡

ተግባር አንድ

- ❖ የሚከተሉትን ተቀላቅለው የቀረቡትን ቃላት ርቱዕ ወይም ኢርቱዕ በማት ለይታችሁ በሰንጠረዡ ውስጥ ፃፉ፡፡

| ተ/ቁ | ርቱዕ | ኢርቱዕ |
|---|---|---|
| ምሳሌ | ላጠ | ተመታ |
| | ፈላ | ተሰበረ |
| 1 | በላ | ተሰራ |
| 2 | ሳለ | ተደበደበ |
| 3 | መታ | ተለወጠ |
| 4 | ሰበረ | ተሰወረ |
| 5 | ሸለመ | ተቀየረ |
| 6 | ፃፈ | ተሰነጠቀ |
| 7 | ጠጣ | ተወዳደረ |

መረጃ መሳሪያ

ርቱዕና ኢርቱዕ ግሶችን በንጽጽር የሚያሳይ ቻርት

## ዋቢ መፅሀፍት

ሀዲስ አለማየሁ፡፡ (1996 ዓ.ም)፡፡ ፍቅር እስከ መቃብር፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሔኖክ ያሬድ፡፡ (2005 ዓ.ም) ፡፡አበበ ቢቂላ የተወለደው መቼ ነው፡፡ ሪፖርተር ጋዜጣ

መዘመር ግርማ (2011 ዓ.ም)፡፡ ሁቱትሲ የወጣቷ ልብ አንጠልጣ ትውስታዎች የትርጉም ስራ፡፡

ማርታ እሸቱና ነፃነት ጌትነት፡፡ (2004 ዓ.ም) ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ 10ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣በት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ሜሪ ጆን ግሌይና ሳባ ገ/መድህን ፡፡ (2007 ዓ.ም)፡፡ ተምሳሌት፡፡ ፅሀይ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራዊ ቅንጅት አሳታሚ ድርጅት፡፡

ሰለሞን ሐለፎም፡፡(1997 ዓ.ም) ፡፡ የድርሰት አፃፃፍ፡፡አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድጅት፡፡

ሳሙኤል አየለና ታሪኳ መላኩ፡፡ (1997 ዓ.ም)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ 7ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሳባ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ (2005 ዓ.ም) ፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስትቲትዩት፡፡ (1995 ዓ.ም)፡፡ የኤች አይ ቪ ኤድስ ትምህርት፡፡አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሪፖርተር ጋዜጣ፡፡ (2009 ዓ.ም) ፡፡ ኪንና ባህል፣ታትሞ ከወጣው ለማስተማሪያነት ተሸሽሎ የተወሰደ፡፡

ባየ ይማም፡፡ (2010 ዓ.ም) ፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ታለጌታ ይመር፡፡ (2007 ዓ.ም)፡ ፡ ሁለገብ የአማርኛ ቋንቋ ማሪያ አጋዥ መፅሀፍ፡፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

ትምህርት ሚኒስተር፣ሴቭ ዘ ችልድረን እና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በጋራ ትብብር፡፡ (2008 ዓ.ም)፡፡ ለምግብነት የሚውሉ የጓሮ አትክልቶች በሚል የተዘጋጀ አጋዥ መፅሀፍ፡፡

አለም እሸቱ፡፡ (1999 ዓ.ም) ፡፡ ተግባራዊ የአማርኛ ትምህርት ማጠናከሪያ ከ7-10ኛ ክፍል፡፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

አለቃ ደስታ ተ/ክለወልድ፡፡ (1962ዓ.ም) ፡፡ አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣በአርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አምሳለ አክሊሉ፡፡ (1981 ዓ.ም) ፡፡ በአለም የታወቁ አጫጨር ልቦለዶች፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፤

ዘሪሁን አስፋው ፡፡ (2004 ዓ.ም)፡፡ የስነ-ፅሑፍ መሰረታውያን፡፡ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ (2001 ዓ.ም)፡፡ የባህል ልማት መሰናክሎች ቅኝት፡፡ ባህርዳር፣(ያልታተመ)፡፡

የአዲስ አበባ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ (2007 ዓ.ም) ፡፡ ባህል ቱሪዝም፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ፡፡ (2007ዓ.ም)፡፡ የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ 7ኛ ክፍል፡ ፡አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ። (2012 ዓ.ም) ። የጥላቻ ንግርርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ።ሀያ ስድተኛ አመት ቁጥር 26 ገፅ 12339። አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም መተሚያ ድርጅት።

ደረጀ ገብሬ። (1996 ዓ.ም) ።ተግባራዊ የፅህፈት መማሪያ።አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚ ድርጅት።

ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ። (2008 ዓ.ም)። ኮሜት አጋዥ መፅሃፍ ከ9-10ኛ ክፍል። አዲስ አበባ፣ አስቴት ነጋ አሳታሚ ድርጅት።

ጌታሁን አማረ። (2009 ዓ.ም)። ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ ። አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ ድርጅት።

ፋንታሁን እንግዳ። (2000 ዓ.ም) ። ታሪካዊ መዝገበ ሰብ ከጥንት እስከ ዛሬ። አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

# የአማርኛ ፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | 1 | ፪ | 2 | ፫ | 3 | ፬ | 4 | ፭ | 5 | ፮ | 6 | ፯ | 7 | ፰ | 8 | ፱ | 9 | ፲ | 10 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፪፻ | 200 | ፫፻ | 300 | ፬፻ | 400 | ፭፻ | 500 | ፮፻ | 600 |
| ፯፻ | 700 | ፰፻ | 800 | ፱፻ | 900 | ፲፻ | 1000 | ፳፻ | 2000 |
| ፴፻ | 3000 | ፵፻ | 4000 | ፶፻ | 5000 | ፷፻ | 6000 | ፸፻ | 7000 |
| ፹፻ | 8000 | ፺፻ | 9000 | ፻፻ | 10000 | | | | |

# አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ስድስተኛ ክፍል አንደኛ መንፈቅ አመት መርሃ ትምህርት

ምዕራፍ አንድ ፡-ባህላዊ አለባበስ(18 ክ/ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የቃላት አገባብ ስርዓትን ተከትለው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- አስተካክለው ያነባሉ፡፡
- ለውስብስብ ቃላት ትርጉም ይሰጣሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ ያሉትን ስርዓተ ነጥቦች በተገቢው መንገድ ይጠቀማሉ፡፡
- ቃላትን እየነጣጠሉ ያነባሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-<br>➢ አዳምጠው የምንባቡን መልዕክት ይገልጻሉ፡፡<br>➢ በትክክል ያነባሉ፡፡<br>➢ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡የተሰጣቸውን አረፍተ ነገርተጠቅመው አንቀጽ ይመሰርታሉ፡፡<br>➢ የወልና የተጸውኦ ስሞችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ ቃላት<br>➢ መጻፍ<br>➢ ሰዋሰው | ተማሪዎች የቃል ቅርጽንና የፊደል አሰዳደርን እንዲያወዳድሩ ማድረግ፡፡<br>ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል<br>የተለመዱና ያልተለመዱ ቃላትን እንዲያወዳድሩ ማድረግ፡፡<br>ቃላትን ቅርጻቸውን መሰረት በማድረግ እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡<br>ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸውን የቃላት ቅርጾች አንድ ላይ እንዲመድቡ ማድረግ<br>ግልጽ መመሪያ በመስጠትና ምእላዶችን በማብራራት መልመጃ ሰጥቶ እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ | ➢ ከተማሪዎች መልስና ሀሳብ በመነሳት መምህሩ የትኛው ይዘት ላይ ማተኮር እንዳለበትና እንደሌለበት ይወስናል፡፡<br>➢ ከተማሪዎች አቀራረብ በመነሳት የሚያሳዩትን መሻሻልመገምገም<br>➢ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠታቸውን በመከታተል የቃላት እውቀታችውን መመዘን፡፡ |

ምዕራፍ ሁለት፡-ታዋቂ አትሌቶች (18 ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ከቅጥያዎች ውስጥ ዋና ቃል ይለያሉ፡፡
- ቅጥዎችን በማጣመር ቃላት ይመሰርታሉ፡፡
- የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ ዋናውን ሃሳብ ይገልጻሉ፡፡
- የስርአተ ነጥቦችን ትርጉም ተረድተው የሚነሱና የሚወድቁ ድምጾችን ይለያሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ ታሪኩን አዳምጠው ድጋሚ ይገልጻሉ፡፡<br>➢ ውስብስብቃላትንበማጣመርና በመነጠል ያነባሉ፡፡<br>➢ አንቀጽ ይመሰርታሉ<br>➢ ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ ተመሳሳይ ቃላትን ይለያሉ፡፡<br>➢ የጥቅል ስሞችን ይለያሉ፡፤ | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | ያዳመጡትን ምንባብ ደጋግመው በቃል እንዲናገሩ ማድረግ፡፡<br>በቃል ያቀረቡትን ንባብ በተመለከተ ግብረ መልስ ከመምህሩ ከተማሪና ከቤተሰብ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡<br>ያልተለመዱ ቃላትን ማንበብ እንዲችሉ የምእላድ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡<br>መምህሩ ምልክቶችን በማየት የስርዓተ ነጥቦችን ጥቅም እንዲረዱ ማድረግና ስርዓተ ነጥቦች በአገላለጽ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ እንዲረዱ ማድረግ፡፡ | ➢ ተማሪዎች የተጠየቁትን ጥያቄ በምልክት ይመልሳሉ፡፡<br>➢ ኢርቱ ክትትል፡- በዚህ ወቅት መምህሩ ስራ ለተማሪዎች በመስጠት በክፍል ውስጥ በመዘዋወር ያለውን መሻሻል ይከታተላል፡፡ |

ምዕራፍ ሶስት፡-ቃላዊ ግጥም (18 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ከዚህምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ያወቁትን አዳዲስ ቃላት ይጠቀማሉ፡፡
- ግጥም ጽፈውያነባሉ፡፡
- ቅንፍን በአረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡
- ገላጭ ጽሁፎችን ተራኪ ጽሁፎችንና የቃል ግጥሞችን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያነባሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው ተመሳሳ የቃል ግጥም ያቀርባሉ፡፡<br>➢ ግጥምን በትክክል ያነባሉ፡፡<br>➢ በአረፍተ ነገር ውስጥ ቅንፍና አዝባርን ይጠቀማሉ፡፡<br>➢ ለተዘረዘሩ ቃላት ተቃራኒ ይሰጣሉ፡፡<br>➢ በአረፍተ ነገር ውስጥ የጊዜ ተውሳክ ግስን ይለያሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | መምህሩ ለተማሪዎች<br>ምር ጽሁፍ ለተማሪዎች ምሳሌ የሚሆኑ የደብዳቤ ጽሁፎችንና የተለያዩ የጽሁፍ ቅረጾችን በማምጣት እንዲጽፉ ማድረግ፡፡<br>ምሳሌ አድርገው የሚጽፏቸው ጽሁፎችን በመስጠትያንን ተከትለው እንዲጽፉ ማበረታታት<br>ለምሳሌ የአረፍተ ነገር መጀመሪያ ቃላት የቃላት ቅርጽ፡፡<br>ተማሪዎች እንደ ምርጫቸው እነዲጽፉ እድል መስጠት፡፡<br>➢ ተማሪዎች እንደ ጸሃፊ እንዲሳትፉ ማድረግ<br>➢ ተማሪዎች እርስበርሳቸው ግብረ መልስ እንዲሰጡና እንዲቀበሉ ማበረታታት | ➢ አንዱ ተማሪ ለሌላኛው እንዲያነብ በማድረግ ፍጥነታቸውንና የአነባበብ ትክክለኛነታቸውን እንዲተራረሙ በማድረግ ለጽህፈት እንዲዘጋጁ ማድረግ፡፡<br>➢ ለተማሪዎች የመጻፊያ መስፈርት በማውጣት እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ |

ምዕራፍ አራት፡-ዘመናዊ እርሻ (18ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- አዳምጠው በቃል ይመልሳሉ፡፡
- አከራካሪ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ቃላትን በመገጣጠም ትርጉምይሰጣሉ፡፡
- የጊዜ ግስን ተጠቅመው ዓ.ነገር ይመሰርታሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልትና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዘህ ትምህረት በኋላተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው መልከቱን በቃል ይገልጻሉ፡፡<br>➢ አዳዲስ ቃላትንያፈልቃሉ፡፡<br>➢ ለቃላት ፍቺ ለመስጠት ተቀራራቢነት ያላቸውን ቃላት ይጠቀማሉ፡፡<br>➢ አከራካሪ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡<br>➢ የጊዜ ተውሳክ ግስን ተጠቅመው አረፍተነገርይመሰርታሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | በንባብ ጊዜ እንግዳ የሆኑባቸውን ቃላት ማስታወሻ በመያዝ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>ለተማሪዎችየተለያዩ ስነጽሁፋዊ ዘውጎችን በማቅረብ የኋላ እውቀታቸውን እየተጠቀሙ የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ፡፡<br>የቅድመ ንባብ ጥያቄ በመስጠት በጥንድና በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>ምንባቡን በዝምታ ንባብ አንብበው ጥያቄዎችን እንዲመሰርቱ ማድረግ፡፡<br>ምንባቡንበለሆሳስ ንባብ አንብበው ጥያቄዎችን እራሳቸውን ችለው በመመለስ መልሶቻቸውን በራሳቸው እንዲያርሙ ማድረግ፡፡ | ➢ የተጠየቁትን ጥያቄ መመለሳቸውን ማረጋገጥ፡፡<br>➢ ከተማሪዎቹ መለስ በመነሳት የትኛው ይዘት ላይ መተኮር እንዳለበት መምህሩ ይወስናል፡፡<br>➢ ባለቀለም ካርድ በመጠቀም መልስ መስጠታቸውን መከታተል፡፡<br>➢ ዓረፍተ ነገሮችን በትክክል መጻፋቸውን ማረጋገጥ፡፡<br>➢ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ጭብጡን እንዲገምቱ ማድረግ፡፡ |

ምዕራፍ አምስት፡-ቱሪዝም (18 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ቃላትን በምእላድ ይከፋፍላሉ።
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ይሰጣሉ።
- በሀላፊጊዜ አንቀጽ ይጽፋሉ።
- ቅድመ ግንድ ቀጥያዎችን ይጠቀማሉ።
- ራስን የመገምገሚያ ስልቶችን ተጠቅመው ራሳቸውን ይገመግማሉ።

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልትና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው ቃላትን ወደ ምእላድይከፋፍላሉ።<br>➢ አንብበው መልከቱን ይገልጻሉ።<br>➢ ለቃላት አመሬያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ ይሰጣሉ።<br>➢ ሃላፊ ጊዜን ተጠቅመው አንቀጽ ይጽፋሉ።<br>➢ ድህረግንድ ቅጥያዎችን ያጣምራሉ። | ➢ ማዳመጥና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰወሰው | መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጽሁፍ መሰረት በማድግ በጋራ እንዲጽፉ ማድረግ።<br>ድምጽን ከፍ አድርገው የሚያነቡትን ከጽሁፉ ጋር እንዲያያይዙ ማድረግ።ድምጽን ከፍ አድርገው ካነበቡት ውስጥ የራሳቸውን ሃሳብ በማፍለቅ ሪፖረት እንዲያቀርቡ ማድረግ።<br>በጽሁፍ ስራ ውስጥ በመሳተፍ እርስበእርስ ግብረመልሰ እነዲሰጡና እንዲቀበሉ ማድረግ።<br>ሲያነቡ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ነገር ካጋጠማቸው እንዲጠይቁ ማበርታታት።<br>በጽሁፍ ስራ ላይ የሚሳተፍ ማህበረስብ መፍጠር | ➢ አጫጭር ማስታዎሻዎችን እንዲጽፉ ማድረግ።<br>➢ በክፊል የተማሩትን ተረድተው ማቅረባቸውን መከታተል።<br>➢ የተማሩትንና የተረዱትን መሰረት አድርገው ማጠቃያ እንዲሰጡ ማድረግ። |

# አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ስድስተኛ ክፍል ሁለተኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት

# ምዕራፍ ስድስት፡-ጸረ-አደንዛዥ እጽና ቁሳቁሶች (18 ክፍለጊዜ)

## የሚጠበቀው ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ተገቢውን የአነባበብ ስልት ተከትለው ያነባሉ፡፡
- መረጃ ሰጪ ጽሁፎችን ይለያሉ፡፡
- አዳዲስ ቃላትን ከአገባቡ በመነሳትይገምታሉ፡፡
- አንድን ሀሳብ ለመግለጽ መሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ ጽሁፉን አዳምጠው ስለጭብጡ ይወያያሉ፡፡<br>➢ ጽሁፉን አዳመጠው መልከቱን ከግል ህይወታቸው ጋር አያዘመዱ ይመልሳሉ፡፡<br>➢ ለቃላት አማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡<br>➢ ጅምር አንቀጾችን ይጨርሳሉ፡፡<br>➢ ተውላጠ ስሞችን ተጠቀመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡ | ➢ ማ ዳ መ ጥ ና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ ቃላት<br>➢ መጻፍ<br>➢ ሰዋሰው | ግልጽ ማድረግ<br>ግለጽ ያልሆነላቸውን እንዲጠይቁ ማበረታታት፡፡<br>ጥያቄና መልስ<br>የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ፡፡<br>ማሰስ<br>ጥያቄዎችን ከጸሁፉ እያሰሱ እንዲመልሱ ማድረግ፡፡ | ➢ ምልከታ፡- የተሰጣቸውን ማስታወሻ በትክክል መጻፋቸውን ማረጋገጥ፡፡<br>➢ አቅርቦት፡- ስራቸውን እንዲያቀረቡ በማድረግ ምን ያህል እንደተረዱ መከታተል፡፡<br>➢ ማጠቃለል ያዳመጡትን ያነበቡትንና የሰሙትን በማጠቃለያ መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡<br>➢ ስለሌላ ሰው ያዳመጡትን እንዲገልጹ ማድረግ፡፡ |

# ምዕራፍ ሰባት የጥላቻ ንግግር(18ክፍለ ጊዜ)

## የሚጠበቀው ውጤት

የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፡-

- መስማማትንና አለመስማማትን የሚገለጹ ሀሳቦችን ያቀርባሉ፡፡
- ምንባቡን በማንበብ የጥላቻ ንግግር እንዴት እንደሚወገድ ይገልጻሉ፡፡
- ቅጽሎችን በመለየት ይጠቀማሉ፡፡
- የጥላቻ ንግግርን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡
- ‹እና›ንና ‹ነገረግን›ን ተጠቅመው ድብልቅ አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው ይመልሳሉ፡፡<br>➢ አንብበው ተመሳሳይ ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡<br>➢ ለቃላት አገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡<br>➢ ቅጽሎችን ለይተው ይጠቀማሉ፡<br>: | ➢ ማዳመጥ<br>እና<br>መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | በቅድመንባብ ጊዜ በንባብና በድህረ ንባብ ወቅት ቻርቶችን እነዲጠቀሙ ማድረግ፡፡<br>መረጃዎችን አቀናበርው ማቅረብ የሚያስችሉ የተለያዩ ትልሞችን ማቅረብ፡፡<br>ኢ-ልቦለዶችንና ሌሎች ታሪኮችን እንዲያነቡ በማድረግ ስለገጸባህሪዎቹ የተረዱትን እንዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>ዋናዋና ዲርጊቶችን የሚገልጽ ቻርት እንዲያዘጋጁ ማድረግ፡፡<br>ሁነቶችን መረዳት ይችሉ ዘንድ ማን ፤ምን፤መቼ፤የት፤ለምን፤የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችሉ ዋናዋና ዲርጊቶችን የሚገልጽ ቻርት እንዲያዘጋጁ ማድረግ፡፡ | ➢ መልሳቸውን አጠገባቸው ካሉት ጋር እንዲናበቡ በማድረግ እንዲተራረሙ እድል መስጠት ፡፡<br>➢ ቃላትንና ምስልን ተጠቅመው የተረዱትን ማቅረባቸውን መከታተል፡፡ |

:-

# ምእራፍ ስምንት፡- ኤች/አይቪ ኤድስ በኢትዮጵያ(18 ክፍለ ጊዜ)

## የሚጠበቀው ውጤት

የዚህ ምእራፍ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፡-

- በሂደት ባለብዙ ቀጥያ ምእላዶችን ያነባሉ፡፡
- የራሳቸውን አመለካከት ይጽፋሉ፡፡
- የጽሁፍ አላባውያንን ይገልጻሉ፡፡
- ለምእላዶች ትርጉም ይሰጣሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህረት በኋላ ተማሪዎች፡ -<br>➢ የጽሁፉን ዋና መልዕክት ተረድተው ይከራከራሉ፡፡<br>➢ የራሳቸውን አመለካከት ይጽፋሉ፡፡<br>➢ የጽሁፍ አላባውያንን ይገልጻሉ፡፡<br>➢ ለቃላት ተቃራኒ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡<br>➢ በተሸጋሪና የመይሻገሩ ግሶች አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | መለየት(ማወዳደር) ተማሪዎች የተሰጣቸውን የሆሄያት መዋቅር መሰረት በማድረግ እንዲያወዳድሩ ማድረግ ይህንንም በሚከተለው መንገድ ማከናወን የተለመዱና ያልተለመዱ ቃላትን<br>የተሰጣቸውን የቃላት ቅረጽ መሰረት በማድረግ አንድ ላይ በመመደብ ሌሎች ቃላትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡<br>በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት የቅጥያ ቅርጾችን እንዲለዩ ማድረግ፡፡ | ➢ ክለሳ፡- ባለፈው የተማሩትን ለክፍሉ እንዲያከፍሉ ማድረግ ፡፡<br>➢ አቅርቦት፡- ያወቁትንና የተረዱትን እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡<br>➢ የብጤ እርማት፡-የሰሩትን ወረቀት በመለዋወጥ አርስ በርስ እንዲተራረሙ ማድረግ፡፡ |

## ምዕራፍ ዘጠኝ ፡-ባህላዊ ልማዶች (18 ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የተስማሙበትን ሃሰብ ያቀርባሉ፡፡
- አጭር ምንባብ አንብበው ወደ ሰንጠረዥ ይቀይራሉ፡፡
- በቃል የሚነበብላቸውን አስተካክለው ይጽፋሉ፡፡
- ከርዕሱ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ስረዓተ ነጥቦችን ጠብቀው ያነባሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው ጽሁፉን ይገመግማሉ፡፡<br>➢ የጽሁፉን ሃሳብ በቃል ይገልጻሉ፡፡<br>➢ ማመልከቻ ይጽፋሉ፡፡<br>➢ የሃላፊ ጊዜን ተጠቅመው አረፍተነገር ይመሰርታሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ<br>እና<br>መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | የቃል ጽህፈት፡- ተማሪዎች ቃል እያዳመጡ (ታላሚውን የቋንቋ መዋቅር መሰረት ያደረጉ) ቃላትን በመጥራት በቃል እንዲጽፉ ማለማመድ፡፡<br>ዓረፍተ ነገር፡-መምህሩ አረፍተ ነገር በመናገር እንዲጽፉ ማድረግ ፡፡<br>ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል ፡-አዳዲስ ቃላት የያዙ አረፍተ ነገሮች ቀደም ሲል የተማሩዋቸው ቃላት ተማሪዎች በዚህ ሰአት ተዘውታሪ ቃላት ላይ እያሰመሩ ይሄዳሉ፡፡<br>አብነት፡- የተሻለ የማንበብ ችሎታ ያለውንተማሪ በማቅረብ በምሳሌው መሰረት እንዲያነቡ ማድረግ፡፡<br>የተደጋገመ የቃል ንበት ደጋግመው በቃል እንዲያነቡ በማድረግ እርስበርስ የሚተራረሙበትን አድል መፍጠር፡፡ | ➢ አካለዊ ምላሽ ዘዴ፡- የተጠየቁትን በምልክት እንዲመልሱማድረግ፡፡<br>➢ ኢ-ርቱ ክትትል ፡-አንድ ግጥም ሰጥቶ እንዲያነቡ በማድረግ አነባበባቸውን እየተዘዋወሩ መከታተል፡፡ |

## ምዕራፍአስር፡-ሴቶችን ማብቃት (18 ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የተሰማቸውን ምክኒያታዊ ሆነው ይገልጻሉ፡፡
- አስተካክለው ያነባሉ፡፡
- የሰው ህይወት ታሪክ ይጽፋሉ፡፡
- ስርአተ ነጥቦች ያላቸውን አገልግሎት ተረድተው ያነባሉ፡፡
- ርቱዕና ኢ-ርቱዕ ዓረፍተ ነገሮችን ይጠቀማሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ ንግግር አዳምጠው ያንጸባርቃሉ፡፡<br>➢ የሰው ህይወት ታሪክ ይጽፋሉ፡፡<br>➢ ቃላትን በምአሳድ ይከፋፍላሉ፡፡<br>➢ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ አገላለጾችን በአረፍተ ነገር ምሰረታ ወቀት ይጠቀማሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥእና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | ➢ በቡድን ወይም በተናጠል እየሆኑ ጸሁፉን ተለማምደው ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማደረግ ይህም ተማሪዎችን ጥሩ ተናገሪና አንባቢ እንደሚያድረጋቸው መገንዘብ፡፡<br>➢ ደቂቃ እየያዙ አጫጭር ታሪኮችን በተደጋጋሚ እንዲያነቡ ማድረግ መሻሻሎችን መመዝገቢያ ቻርት ማዘጋጀት ይህንንም በግራፍ ማስደገፍ፡፡<br>➢ ቅድመ ጽህፈት ተግባራትን ማለማመድ ይህ ጽህፈት ከመጀመራቸው በፊት የሚከናወን ተግባር ነው በዚህ ስር የታሪክ መዋቅር የቃላት ድር ወዘተ መጠቀም ፡፡ | ➢ አቅርቦት፡- ተግባራቸውን ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ በማድረግ መከታተል፡፡<br>➢ የብጤእርማት፡-ስራቸውን አየተለዋወጡእንዲተራረሙ ከተደረገ በኋላ ሰበስቦ አርማት መስጠት፡፡<br>➢ የቡድን ስራ፡-የቡድን ስራ በመስጠት ሁሉም መሳተፋቸውን መከታተል፡፡ |

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ
## የመምህር መምሪያ
## (፮) ስድስተኛ ክፍል